# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

81ኛ ዓመት ቁጥር 328 ሐምሌ 28 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ




## በማክሮ ኢኮኖሚው ዘርፍ አመርቂ ውጤት መመዝገቡን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ባለፈው በጀት ዓመት በማክሮ ኢኮኖሚው ዘርፍ አመርቂ ውጤት መመዝገቡን የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው ላይ ባሰፈሩት መልዕክት እንደገለጹት የማክሮ ኢኮኖሚ ኮሚቴው በትላንትናው እለት ስብሰባ አካሂዷል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደገለጹት፤ ባለፈው ዓመት የሚያበረታታ የወጪ ንግድ አፈጻጸም እና ቀጥተኛ የውጭ መዋዕለ ንዋይ ፍሰት ታይቷል።

ባለፉት ሁለት ወራት የዋጋ ግሽበት መቀነስ፣ ከፍተኛ የአረንጓዴ አሻራ ክንውን፣ የበጎ ፈቃደኝነት ተግባራት፣ የሬሚታንስ ጭማሪ እና በቴክኖሎጂ የታገዘ የሥራ ክንውን የተመዘገቡበት እንደሆነም መረጋገጡን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጠቅሰዋል።

በዚህ ዓመት የተገኙ ስኬቶችን አጠናክሮ መቀጠል በእጅጉ አስፈላጊ እንደሆነም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገልጸዋል።



ፎቶ ፡- ገበበ ገብሬ

## “ሕወሓት ለሰላማዊ ንግግሩ ቅድመ ሁኔታ በማስቀመጡ ዲፕሎማሲያዊ ኪሳራ ደርሶበታል”

### - አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ

ፀጋዬ ጥላሁን

አዲስ አበባ፡- ሕወሓት ለሰላማዊ ንግግሩ ቅድመ ሁኔታ በማስቀመጡ ዲፕሎማሲያዊ ኪሳራ ደርሶበታል ሲሉ አንጋፋው ፖለቲከኛ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ገለፁ።

አንጋፋው ፖለቲከኛ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ሕወሓት በተፈጥሮው ለመተባበርና ሀገር ለማሻገር ፍላጎት የሌለው ቡድን በመሆኑ የሰላማዊ ንግግሩ ውጤት ላይሳካ ይችላል። ቡድኑ ጉዳዩን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ያለቅድመ ሁኔታ ቢመጣ እንኳን ችግሩን መፍታት የሚያስችል ነባራዊ ሁኔታ ላይኖር ይችላል።

ለአብነትም ወልቃይትን ወደ ትግራይ ይመለስ የሚለው ነገር በሁለቱም ወገን በምንም አይነት መንገድ የሚሆን ጉዳይ አይደለም። ይህ ለአማራ ክልል ብቻ ተብሎ ሳይሆን ለኢትዮጵያ መንግሥትም ቀይ መስመር ነው።

አሁንም ሕወሓት ለሌላ ጦርነት ዝግጅት ሲያደርግ ቆይቷል ያሉት አቶ አንዳርጋቸው፤ ቡድኑ ፍላጎቱን በጉልበት ለማስፈጸም

“ሕወሓት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








ዶክተር ኢስማኤል ሸምሰዲን

## አለርት ሆስፒታል ሦስት የልዩ ቀዶ ሕክምና ክፍሎችን አስመረቀ

### - የላንቃና የከንፈር መሰንጠቅ ያለባቸው ሕፃናትን ያለወረፋ እንዲታከሙ ያስችላል

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- አለርት ኮንፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በትላንትናው እለት የሕፃናት የላንቃና የከንፈር መሰንጠቅ ማከሚያ የቀዶ ሕክምና ክፍል እና ሌሎች የሕክምና አገልግሎቶችን የሚሰጡ ሦስት የልዩ ቀዶ ሕክምና ክፍሎችን አስመረቀ፡፡ ክፍሎቹ የላንቃና የከንፈር መሰንጠቅ ያለባቸውን ሕፃናት ወረፋ ሳይጠብቁ የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ እንደሚያስችልም ተገልጿል፡፡

የሆስፒታሉ ዋና ሥራ አስኪያጅ ዶክተር ኢስማኤል ሸምሰዲን በትናንትናው ዕለት በተካሄደው የምረቃ ሥነሥርዓት ላይ እንደተናገሩት፤ በኢትዮጵያ በላንቃና ከንፈር መሰንጠቅ (ክፍተት) የተጎዱ በርካታ ሕፃናት

አለርት ሆስፒታል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






## በነሐሴ ወር የነዳጅ ምርቶች መሸጫ ዋጋ ባለበት እንደሚቀጥል ተገለጸ



ገጽ 4

# ማዕከሉ ከሦስት ሺህ ለሚበልጡ ሕጻናት ነጻ ሕክምና መስጠቱን አስታወቀ

## - ከአምስት ሺህ በላይ ሕጻናት ወረፋ በመጠበቅ ላይ ናቸው

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- የኪዩር ኢትዮጵያ የልጆች ሕክምና ማዕከል በዚህ ዓመት ከሦስት ሺህ ለሚልቁ ሕፃናት ነጻ የቀዶ ጥገና ሕክምና አገልግሎት መስጠቱን አስታወቀ፡፡ ከአምስት ሺህ በላይ ሕፃናትም ወረፋ በመጠባበቅ ላይ እንደሚገኙም ጠቁሟል፡፡

የማዕከሉ ዋና ሥራ አስኪያጅ አደይ አባተ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሕክምና ማዕከሉ ለአንድ ልጅ በትንሹ 50 ሺህ ብር የሚያስወጣውን ሕክምና በነፃ እየሰጠ ይገኛል፡፡

ከአስራ ስምንት ዓመት በታች ለሆኑ እንዲሁም የአካል ጉዳት ሰለባ ለሆኑ ልጆች የፕላስቲክ ሰርጀሪና ሙሉ ቀዶ ጥገና አገልግሎት የሚሰጠው የሕክምና ማዕከሉ የማስፋፊያ ሥራዎችን በመከወን ላይ እንደሚገኝም ዋና ሥራ አስከያጇ ጠቁመው ከተለያዩ የሀገሪቷ ክፍሎች ለሚመጡ ታካሚዎች አገልግሎት እንደሚሰጥም ተናግረዋል፡፡

ወደ ሕክምና ማዕከሉ የሚመጡ ታማሚዎች ምንም አይነት ወጪ እንደማይጠየቁና ሙሉ በሙሉ የነፃ አገልግሎት እንደሚያገኙ የገለፁት ዋና ሥራ አስኪያጇ፤ ከሕክምናው በተጨማሪም ለታማሚና ለአስታማሚ ማረፊያና ምግብ በመቻል እንዲሁም ከሕክምና ማዕከሉ ውጪ የሚገኙ መድኃኒትና የሕክምና ግልጋሎቶችንም ጭምር እየሰጠ እንደሚገኝ ነው የገለጹት፡፡

ማዕከሉ በዚህ ዓመት ከሶስት ሺህ ለሚልቁ ሕፃናት የቀዶ ጥገና ሕክምና አገልግሎት የሰጠ ሲሆን ከአምስት ሺህ በላይ ሕፃናትም በሕክምና ማዕከሉ ለመታከም ወረፋ በመጠባበቅ ላይ እንደሚገኙ እንዲሁም በቀጣይ ዓመት አገልግሎት ማዕከሉ የቀዶ ጥገና አገልግሎት ሕክምና የሚሰጣቸውን ሕፃናት ቁጥር አራት ሺህ ለማድረስ እየሠራ እንደሚገኝም ዋና ሥራ አስኪያጇ ተናግረዋል፡፡

የሕክምና ማዕከሉ በመላው አገሪቱ የሚገኙትን ሕፃናቶች ተደራሽ መሆን ስለማይችል በተወሰኑ ሆስፒታሎች ውስጥ የሚገኙ የሕክምና ባለሙያዎችን በቅጥር ግቢው ለአንድ ዓመት ያህል በማሠራትና በማሰልጠን የማብቃት ሥራዎችን በተለያዩ ጊዜያት መከወኑንም ነው የገለጹት፡፡

ከተቋቋመ ከአስራ ሦስት ዓመታት በላይ ያስቆጠረው የኪዩር ኢትዮጵያ የልጆች ሕክምና ማዕከል እስከዛሬ ድረስ ከ30 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ሕፃናት የቀዶ ጥገና አገልግሎት መስጠት መቻሉንም ነው ዋና ሥራ አስኪያጇ ያመለከቱት፡፡

የኪዩር ኢትዮጵያ የልጆች ሕክምና ማዕከል የመኪና አደጋ የደረሰባቸው፣ በተፈጥሮ እግርና እጃቸው ተዟዙሮ የተወለዱ፣ የእሳትና ፈንጂ ጉዳት የደረሰባቸው እንዲሁም የላንቃ እና የከንፈር መሰንጠቅ የደረሰባቸውን ሕፃናት የቀዶ ሕክምና አገልግሎት ሲሰጥ የቆየ የሕክምና ተቋም ነው፡፡



ፎቶ - በገባቦ ገብሬ

አደይ አባተ

# ክልሉ አራት ዋና ከተሞች እንደሚኖሩት ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- አዲሱ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል እኩል ደረጃ ያላቸው አራት ዋና ከተሞች እንደሚኖሩት የክልሉ ምክር ቤት አስታውቋል።

ምክር ቤቱ ይህን ያስታወቀው የብዝኃ ዋና ከተሞች ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ ላይ ከክልሉ ስድስቱም ዞኖች ከተውጣጡ የኅብረተሰብ ተወካዮች ጋር ውይይት ባደረገበት ወቅት ነው።

የብዝኃ ከተሞች ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ ቦንጋ፣ ተርጫ፣ ሚዛን አማን እና ቴፒ እኩል ደረጃ ያላቸው የክልሉ ዋና ከተሞች ይሆናሉ ይላል።

ቦንጋ ከተማ የፖለቲካ እና የርዕሰ መስተዳደሩ መቀመጫ፣ ተርጫ የክልሉ ምክር ቤት መቀመጫ፣ ሚዛን አማን የዳኝነት አካል መቀመጫ እንዲሁም ቴፒ የብሔረሰቦች ምክር ቤት መቀመጫ እንደሚሆኑም በረቂቅ አዋጁ ላይ ተቀምጧል።

የክልሉ ዋና ከተሞች አራት እንዲሆኑ የተደረገው ፍትሐዊ የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማረጋገጥ እንደሆነም የብዝኃ ከተሞች ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጁ ይጠቅሳል።

ረቂቅ አዋጁ በቀጣይ በክልሉ ምክር ቤት ፀድቆ የሚተገበር ከሆነ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል እኩል ደረጃ ያላቸው አራት ዋና ከተሞች ያሉት የመጀመሪያው ክልል ይሆናል።

የውይይቱ ተሳታፊዎች የክልሉ ዋና ከተሞች አራት እንዲሆኑ በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ በሁሉም የክልሉ ማኅበረሰብ ዘንድ እኩል የሆነ ስምምነት ባለመኖሩ ተጨማሪ ውይይቶች ሊደረጉ እንደሚገባ ሐሳባቸውን መስጠታቸውን ኢቢሲ ዘግቧል።

በተጨማሪም የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አቶ ወንድሙ ኩርታ በመሩት መድረክ የክልሉ የብሔረሰቦች ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር ለመዘርዘር የተዘጋጀው ረቂቅ አዋጅም ውይይት ተደርጎበታል።

# ኢትዮጵያ ለዓለምና ለቀጠናው ሰላምና መረጋጋት የምታደርገውን ጥረት አጠናክራ እንደምትቀጥል ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ ለዓለምና ለቀጠናው ሰላምና መረጋጋት የምታደርገውን ጥረት አጠናክራ ትቀጥ ላለች ሲሉ የኢፌዴሪ መከላከያ ሚኒስትር ዶክተር አብርሃም በላይ ገለጹ፡፡ በሌላ በኩልም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ለቻይና የመከላከያ ሠራዊት የምስረታ በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

ዶክተር አብርሃም በቻይና አዘጋጅነት በተካሄደው የቻይና-አፍሪካ የሚኒስትሮች የሰላምና የፀጥታ ፎረም ላይ ተሳትፈዋል፡፡ ሚኒስትሩ በፎረሙ ባስተላለፉት መልዕክት፣ወቅቱ በዓለማችን ሆነ በአካባቢያችን የሚታዩ የጸጥታ ችግሮችን ለመቅረፍ ከሰላም ኃይሎች ጋር በትብብር መሥራት የሚያስፈልግበት ጊዜ ነው ብለዋል፡፡

የቀደምት ስልጣኔ ባለቤት የሆነችው ኢትዮጵያም በፓን-አፍሪካን መንፈስ አፍሪካዊ ችግሮችን በአፍሪካ ውያን ለመፍታት እንዲቻል በጽናት እየሠራች መሆኗን አስረድተዋል፡፡

ዶ/ር አብርሃም የቻይና ሪፐብሊክ መንግሥት አካታችና ሚዛናዊ አካሄድን በመከተል ለዓለም ሰላምና መረጋጋት እያደረገ ላለው ሚና ያላቸውን ክብርና አድናቆት ገልጸዋል፡፡

በተመሳሳይ ዜና የኢፌዴሪ የመከላከያ ሠራዊት ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ የቻይና የመከላከያ ሠራዊት የተመሠረተበትን 95ኛ ዓመት ክብረ በዓል በማስመልከት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

ጠቅላይ ኤታማዦር ሹሙ በመልዕክታቸው÷ የቻይና የመከላከያ ሠራዊት የሀገሩን ሉዓላዊነት፣ ጸጥታና ጥቅም ከማስከበር አልፎ ለዓለማችን ሰላምና መረጋጋት እያደረገ ላለው በጎ ሚና ያላቸውን አድናቆት ገልጸዋል፡፡

ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ፣ቻይና እና ኢትዮጵያ ለረጅም ዘመናት የዘለቀ ታሪካዊ ወዳጅነት ያላቸው ሀገራት መሆናቸውን አውስተዋል፡፡

በጋራ ተጠቃሚነት ላይ በመመሥረት በሀገራቱ መካከል ያለው ግንኙነት በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በባህል፣ በትምህርት እና በጤና መስኮች ከፍተኛ ዕድገት እያሳየ እንደመጣ መግለጻቸውንም ከመከላከያ ሠራዊት ያገኘነው መረጃ ያመለከታል፡፡

ጠቅላይ ኤታማዦር ሹሙ ሁለቱ ወዳጅ ሀገራት በወታደራዊ ዲፕሎማሲና ትብብር ላይ ከፍተኛ ዕድገት ላይ እንደደረሱ ጠቁመው ፤ያላቸውን ትብብር ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ እየተሠራ እንደሚገኝ አረጋግጠዋል፡፡

# በሐዋሳ በ220 ሚሊዮን ብር እድሳት የተደረገለት የእንግዳ ማረፊያ ለአገልግሎት መብቃቱ ተነገረ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



ሀዋሳ፡- በረቀቀ የስዕል እና የጥበብ ሥራዎቻቸው የሚታወቁት እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ መኖሪያ ቤት የነበረውና በአሁኑ ወቅት አቶ ጥላሁን ሽፈራው በተባሉ የግል ባለሀብት ባለቤትነት በግዢ የተዛወረው የቪላ አልፋ እንግዳ ማረፊያ በ220 ሚሊዮን ብር ወጪ እድሳት ተከናውኖለት አገልግሎት መስጠት መጀመሩ ተገለጸ፡፡

የሐዋሳ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ረ/ፕሮፌሰር ፀጋዬ ቱኬ በከተማዋ በግሉ ዘርፍ በመከናወን ላይ ያሉ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎችን ተዟዙረው ከተመለከቱ በኋላ እንደገለጹት፤በግሉ ዘርፍ እንቅስቃሴዎች የቱሪዝምና የኢንቨስትመንት መነቃቃት በከፍተኛ ደረጃ እያደገ ይገኛል፡፡

በግሉ ዘርፍ እንቅስቃሴዎች የቱሪዝምና የኢንቨስትመንት መነቃቃት እንደ ከተማ በከፍተኛ ደረጃ እያደገ እንደሚገኝ የገለፁት ረ/ፕሮፌሰር ፀጋዬ ቱኬ ከተማ አስተዳደሩ ለኢንቨስተሮች ምቹ ሁኔታዎችን የመፍጠር የመደገፍና የመከታተል ስራውን ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ እንደሚገኝ ጨምረው ገልፀዋል፡፡

ይህ ታሪካዊ ስፍራ በተገቢው ሁኔታ ታድሶ እና ተገንብቶ አገልግሎት መስጠት መጀመሩ ለሐዋሳ ከተማ ኢንቨስትመንት እና የቱሪዝም እንቅስቃሴ ተጨማሪ አቅም የሚፈጥር መሆኑን ወ/ሮ ደርጊቱ ጫሊ የሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ ቱሪዝምና ስፖርት መምሪያ ኃላፊ ገልፀዋል፡፡

ቪላ አልፋ እንግዳ ማረፊያ ታሪካዊ ይዘቱን ሳይለቅ በተዋቡ እና የተገለጋይ ፍላጎትን ማዕከል ባደረጉ እንዲሁም ደረጃቸውን በጠበቁ ቁሳቁሶች የተገነባ መሆኑን የገለፁት የእንግዳ ማረፊያው ባለቤት አቶ ጥላሁን ሽፈራው በእንግዳ ማረፊያው ግንባታና እድሳት ሂደት እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ ታሪክና ስም ማስቀጠል የሚያስችሉ ሥራዎችን ለማከናወን እቅድ ተይዞ በትኩረት እየተሠራ እንደሚገኝም ጨምረው ገልፀዋል፡፡

ለእንግዳ ማረፊያው ግንባታ ከ220 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ መደረጉን የገለፁት አቶ ጥላሁን እንግዳ ማረፊያው ሙሉ በሙሉ ወደ ሥራ ሳይገባ ከ80 በላይ ቋሚ እና ጊዜያዊ የሥራ እድል ከመፍጠሩም በተጨማሪ በሚሰጠው አገልግሎት ለሐዋሳ ከተማ ተጨማሪ ውበት የሚፈጥር የቱሪዝም መዳረሻ እንደሆነም መግለጻቸውን የዘገበው የሃዋሳ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች መምሪያ ነው።

# ለአማራ እና አፋር ክልሎች ከ9 ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጣ የላቦራቶሪ መሣሪያዎች ድጋፍ ተደረገ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የኦሃዮ ስቴት ግሎባል ዋን ሄልዝ ፕሮግራም በአማራና አፋር ክልሎች በጦርነቱ ጉዳት ለደረሰባቸው 11 ሆስፒታሎች ከ9 ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጣ የላቦራቶሪ መሣሪያዎች ድጋፍ አደረገ።

የጤና ሚኒስትሯ ዶክተር ሊያ ታደሰ፤ በመጀመሪያው ዙር ድጋፍ ስድስት ሚሊዮን ብር የሚጠጋ የሕክምና መሣሪያዎች ድጋፍ መደረጉን አስታውሰዋል።

በሁለተኛ ዙር ደግሞ በአማራና አፋር ክልሎች በጦርነቱ ጉዳት ለደረሰባቸው 11 ሆስፒታሎች ከ9 ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጣ የላቦራቶሪ መሣሪያ ድጋፍ መደረጉን ጠቅሰዋል።

በጦርነቱ ምክንያት ውድመት የደረሰባቸውን የጤና ተቋማት መልሶ ለማቋቋም ሰፊ ርብርብ ቢደረግም እስካሁን በታሰበው ልክ ችግሩን መፍታት አልተቻለም ያሉት ሚኒስትሯ የአጋር አካላት እገዛ ወሳኝ መሆኑን ገልጸዋል።

በኦሃዮ ስቴት ግሎባል ዋን ሄልዝ ፕሮግራም በዛሬው እለት የተደረገው ድጋፍም በጦርነቱ ጉዳት የደረሰባቸው ሆስፒታሎችን ወደ ቀደመ ሥራቸው ለመመለስ ትልቅ ትርጉም አለው ብለዋል።

የኦሃዮ ስቴት ግሎባል ዋን ሄልዝ ፕሮግራም የኢትዮጵያ ዳይሬክተር ዶክተር ኤባ አባተ፤ ጦርነቱን ተከትሎ በሰሜኑ የአገሪቷ ክፍል በርካታ ሰብዓዊና ቁሳዊ ውድመት በመድረሱ መልሶ ለማቋቋም ሰፊ ርብርብ እንደሚጠይቅ ተናግረዋል።

ከዚህ ቀደም በሁለቱም ክልሎች ለሚገኙ አምስት ሆስፒታሎች ድጋፍ ማድረጉን አስታውሰው ድጋፉ ለሁለተኛ ዙር መደረጉን ኢዜአ ዘግቧል።

የተደረገው ድጋፍ ክፍተቶችን መሠረት ያደረገ መሆኑን በመግለጽ መሣሪያዎቹ አገልግሎት ሲጀምሩ ለአካባቢው ማኅበረሰብ ሰፊ አገልግሎት መስጠት




የሚያስችል ነው ብለዋል።

በተመሳሳይ፣ የኮሪያ መንግሥትና ኤግዚም ባንክ ለኮቪድ 19 ምርመራ የሚያገለግል የላቦራቶሪ መመርመሪያ ኪት ድጋፍ አበርክተዋል።

# ለሀገርና ለልጅ የተሰገሰ ወጣትነት

**ዳግማዊት ግርማ**

በሀገር ጉዳይ ከመጡበት ወደኋላ የማያውቅ፣ ሕይወቱን ለመስጠት የማይሰስት፣ በነፍሱ ተወራርዶ ሀገርን ለትውልድ የሚያስቀጥል ጀግና ለመውለድ የማይሰንፍ ለምለም ማህፀን ባለቤት ነች፤ በውዶች ውድ ደም ታፍራና ተከብራ የምትኖር፤ የብዙኃን እናት መጠጊያ ተብላ የምትጠራ... ኢትዮጵያ፡፡

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ በብዙዎች ዋጋ ቆመው በሚኖሩ እንዲሁም የነገ ዕጣ ፈንታቸው በዛሬ ተማሪዎቻቸው ላይ ለተፃፉላቸው ሀገራት ልጅን አስተምሮ ለወግ ማብቃት ትልቁ ሥራ ነው፡፡ ልጅን አስተምሮ ለማስመረቅ የሚደረግ ሥራ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ቤት ይቁጠረው፡፡

በአባቱ መስዋዕትነት በእናቱ ብርታት ዛሬን ማየት የቻለ የአንድ ምሩቅ ታሪክ ልናጋራችሁ ወደድን፤ ስሙ ቸርነት ኢያሱ ይባላል፡፡ ትውልድና እድገቱ ከወላይታ ሶዶ 17 ኪሎሜትሮችን በምትርቀው ጉኑኖ የምትባል ስፍራ ነው። ከ1997 ጀምሮ የመከላከያ ሠራዊትን ለ15 ዓመታት ያገለገሉት አባቱ ሃምሳ አለቃ ኢያሱ ቦቶሬ ይባላሉ። የእናቱ ስም ደግሞ ስንቅነሽ ሲሳዬ ነው።

ሃምሳ አለቃ ኢያሱ ለሀገሩ የማይነጥፍ ፍቅር የማያልቅ ውለታ አለበት፡፡ በነፍሱ ተወራርዶ ለሚያኖራት ሀገሩ ሲል የሀገር መከላከያ ሠራዊትን የተቀላቀለው ሃምሳ አለቃ ኢያሱ፤ ከነበረበት የኑሮ ገደል እሱንና ልጁንም ጭምር ለማውጣት ብዙ ጥረት አድርጓል፡፡ ኑሮውን ለመለወጥ ልጁን አስተምሮ ሰው ለማድረግ ብዙ ለፍቷል፡፡


አምስት ልጆች ባሉበት ቤተሰብ ውስጥ ብቸኛ ወንድ ልጅ ሆኖ የተወለደው ልጁ ቸርነት አባቱ የመከላከያ ሠራዊት አባል ሆኖ ሲመለመል የስድስት ዓመት ሕፃን ነበር። ሙሉ ሕይወቱ የብዙ ገጾች መጽሐፍ የሚወጣ ታሪክ አለው፤ በተለይ አባቱ በማይደውልበት ወቅት ከእናቱ ጋር ያሳለፉት ጊዜያት ብዙ ትዝታዎችን ጥለውበት አልፈዋል።

ቤተሰቦቹ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አስተምህሮ መሠረት 1989 በተክሊል ነው የተጋቡት። ለሃያ አምስት ዓመታት በፍቅርና በመተሳሰብ ኖረዋል። የአባቱን ጉድለት እናቱ የእናቱን ጉድለት አባቱ እያሟሉ ነው ዛሬ ላይ የደረሱት። ቸርነት ስለ እናቱ ሲናገር አባቱ ቤት ባልነበረባቸው 15 ዓመታት ሁልጊዜ ስለ አባቱ በሰላም መመለስ ስትጸልይ ነው የኖረችው በማለት ምስክርነቱን ይሰጣል፡፡

የሃምሳ አለቃ ኢያሱ ደሞዝ አነስተኛ ቢሆንም ከራሱ ይልቅ ልጆቹንና ቤተሰቡን ያስቀድም ነበርና ለራሱ ከሚያስቀራት አንድ መቶ ብር ውጭ የሚያገኛትን ሁሉ ይልክላቸው ነበር፡፡

ቸርነት ኢያሱ አባቱ በቤት ባልነበረባቸው ጊዜያት ከእናቱ ጋር ብዙ የሕይወትን ብዙ ክፉ ገፅታዎችን ተመልክቷል፡፡ እናቱ እህቶቹንና እሱን አባቱ ደግሞ ሀገሩን እየጠበቁ ነው ያሳደጉት። ብዙ ወጥተው እልፍ ወርደዋል።

የሆነ ጊዜ ላይ አባቱ ስልክ ሳይደውል የበላው ጅብ ለሁለት ዓመታት ሳይጮህ ከርሞ ያውቅ ነበር፡፡ በዚህ



ወቅት ቸርነትና እናቱ በናፍቆት ክፉ ጅራፍ ሲገረፉ ቆዩ። እናቱም ካገኘችው ገንዘብ ከልጆቿ ተለይታ አንድ ቀን እንኳን ብቻዋን ሻይ ጠጥታ አታውቅም። ልጆች እንዳይቸገሩ ስትል እርሷ ብዙ ሕመምና ችግር አይታለች። ለአይን ሙሉ የነበረችው ድንቡሽቡሿ እናቱ በችግር ክሳት አጥንቷ እስኪታይ ሆናለች።

ሌላም ጊዜ አባቱ ስምንት ወር ሳይደውል ቆየና ደወለላቸው፤ ከዚያ ምን ሆነህ ነው ብለው ሲጠይቁት ጓደኛዬ ተመቶ ጦር ኃይሎች ሆስፒታል መጥተን ነው አለ። ከጊዜያት በኋላ ግን እውነቱ ሲታወቅ የተመታው ጓደኛው ሳይሆን እሱ ራሱ ነበር።

ልጁ ቸርነት ከጓደኞቹ አንሶ እንዳይታይ ብዙ ዋጋ ከፍሏል። ምሥራቅ እዝ ጅግጅጋ በነበረ ግዜ ጠርቶ የሚኖሩበትን ቦታ ሕይወታቸውን በሙሉም ለልጁ አሳይቶትም ነበር፡፡ ያኔ ጅግጅጋ ተጠርቶ በሄደባቸው ጊዜያት ስለ አባቱ የቤተሰብ ፍቅር ነው ሲሰማ የነበረው። የአባቱ ጓደኞች አሁን አብዛኛዎቹ በሰሜኑ ጦርነት ተሰውተዋል፡፡

በመጨረሻም ሃምሳ አለቃ ኢያሱ ሱማሌ ሞቃዲሾ ግዳጅ እያለ ቆስሎ መጣና ጦር ኃይሎች ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በደረትህ ላይ ያለው ጥይት ከወጣ ልትሞት ትችላለህ ስላሉት እስካሁን ጥይቱን በደረቱ ተሸክሞ እየኖረ ነው።

መከላከያ ውስጥ እያለ ደሞዙ 2500 በነበረበት ጊዜ ልጁ ከሰው በታች እንዳይሆን ከሰው እንዳያንስ ስማርት ስልክ እንዲሁም ላፕቶፕ ገዝቶ ነው ያስተማረው። ለራሱ አንድ እንኳን መቀየሪያ ጫማ የሌለው አባት ኢያሱ ለልጁ ቸርነት ግን እየቀያየረ እንዲለብስ አድርጎታል። ልጁ በተመረቀበት ወቅት ቸርነትን የአምባሳደር ሙሉ ልብስ አልብሶ አባት ግን ጫማና ልብስ ከሰው ተበድሮ ነው ለማስመረቅ የሄደው።

ለወጣቱ ቸርነት አባቱን በሕይወት ማየቱ ብቻ ያስደስተዋል፤ ደረቱን በጥይት በተመታ ግዜ ቢሞት ለዚህ አልደርስም ነበርም ይላል። ሁል ጊዜ እግዚአብሔር እንደ እነሱ አይነት አባትና እናት ስለሰጠኝ ፈጣሪዬን አመሰግነዋለሁ ይላል የሃምሳ አለቃው ልጅ ቸርነት እያሱ።

ምንም እንኳን በተለያዩ ምክንያቶች አባቱ እንደጠበቀው ተሸላሚ መሆን ባይችልም ሰኔ 25 ቀን 2014 ዓ.ም ከዋቸሞ ዩኒቨርስቲ በሶስት ነጥብ ሁለት ሰባት ውጤት መመረቅ ችሏል፡፡

# በነሐሴ ወር የነዳጅ ምርቶች መሸጫ ዋጋ ባለበት እንደሚቀጥል ተገለጸ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ከአውሮፕላን ነዳጅ በስተቀር በነሐሴ ወር የነዳጅ ምርቶች መሸጫ ዋጋ ባለበት እንደሚቀጥል የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር አስታወቀ።

ከሐምሌ 23 ቀን 2014 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስ ተግባራዊ የሚሆን የነዳጅ ምርቶች የችርቻሮ ዋጋ ክለሳን አስመልክቶ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳስታወቀው ከሰኔ 29 ቀን ጀምሮ ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የታለመለት የነዳጅ ድጎማ በነሐሴ ወር በነበረበት ይቀጥላል። የአውሮፕላን ነዳጅን በሚመለከት ግን በወቅታዊ የዓለም አቀፍ ዋጋ ተሰልቶ በመጣው አዲስ አበባ ላይ በሊትር 84 ብር ከ42 ሳንቲም እንዲሸጥ መወሰኑንም አስታውቋል።

እንደ መግለጫው ማብራሪያ ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የታለመለት የነዳጅ ድጎማ የአሠራር ሥርዓት በነሐሴ ወር በተመሳሳይ ይቀጥላል። አሠራሩ አንዳንድ ሊስተካከሉ የሚገባቸው ክፍተቶች ቢኖሩትም ከጅምሩ መልካም ውጤት እየተመዘገበበት ነው። አሠራሩ ከታለመለት ድጎማ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚገባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎችን ቀድሞ ከነበረው የጥቅል ድጎማ አሠራር በተሻለ ሁኔታ ተጠቃሚ እያደረገ እንደሚገኝም አስታውቋል።

በየጊዜው ተለዋዋጭ በሆነው የዓለም አቀፍ የነዳጅ ምርት ዋጋ መሠረት በሚታየው ጭማሪ ልክ መንግሥት የኅብረተሰቡን የኑሮ ሁኔታ ታሳቢ በማድረግ በጨመረው ልክ ማስተካከያ ባለማድረጉ በነዳጅ ማረጋጊያ ፈንድ ላይ በወር በአማካይ ወደ ተጠቃሚው መተላለፍ የነበረበት 10 ቢሊዮን ብር ጉድለት ወደ መንግሥት እየተመዘገበ መጥቷል። በዚህም በአሁኑ ወቅት አገሪቱ ከፍተኛ ዕዳ ለመሸከም መገደዷን መግለጫው ያስረዳል።

የተከሰተውን ከፍተኛ የዕዳ ጫና በሂደት ማስተካከል ተገቢ ነው ያለው መግለጫው፣ የዕዳ ጫናውን ደረጃ በደረጃ ለማስቀረት እንዲቻል የሚኒስትሮች ምክር ቤት የነዳጅ ውጤቶች መሸጫ ዋጋ ማስተካከያና የታለመ ድጎማ እንዲተገበር አድርጓል። በተላለፈው ውሳኔ መሠረት ዝቅተኛ ገቢ ያለው የኅብረተሰብ ክፍል ላይ ተጽዕኖ በማያስከትል ሁኔታ የሕዝብ ማጓጓዣ ትራንስፖርት ተሽከርካሪዎችን በመለየት የተወሰነውን የድጎማ መጠን ተጠቃሚ ለማድረግ የነዳጅ ዋጋ የታለመለት ድጎማ ትግበራ ከሰኔ 29 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እየተደረገ እንደሚገኝ ገልጿል።

# በነሐሴ ወር ቅጽበታዊ ጎርፍና የመሬት መንሸራተት ሊከሰት ስለሚችል ኅብረተሰቡ ጥንቃቄ እንዲያደርግ ኢንስቲትዩቱ አሳሰበ

**ፋንታነሽ ክንዴ**



አዲስ አበባ፡- በነሐሴ የሚኖረውን የተጠናከረና ተከታታይነት ያለው ከባድ ዝናብ ተከትሎ በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ፣ የወንዞች ሙላት እና የመሬት መንሸራተት ሊኖር ስለሚችል ኅብረተሰቡ ጥንቃቄ እንዲያደርግ የብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አሳሰበ፡፡

የብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ በመጭው ነሐሴ ወር በሰሜን ምስራቅ፣ በሰሜን፣ በሰሜን ምዕራብ እና በመካከለኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የተሻለ ጥንካሬ እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ጠቁመዋል፡፡ የሚኖረውን የተጠናከረና ተከታታይነት ያለው ከባድ ዝናብ ተከትሎ በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ፣ የወንዞች ሙላት እና የመሬት መንሸራተት ሊከሰት ስለሚችል ኅብረተሰቡና የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ አሳስቧል፡፡

በቀጣዩ ወር የምዕራብ፣ የምስራቅ እና የሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ጂማ፣ አዲስ አበባ ዙሪያ፣ አዲስ አበባ፣ ሁሉም የአማራ ክልል እና የትግራይ ዞኖች እንዲሁም የአፋር ክልል ዞኖች በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበና በአንዳንድ ቦታዎቻቸው ላይ ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚያገኙ የኢንስቲትዩቱ ለዝግጅት ክፍላችን ያደረሰው መግለጫ ያመለክታል፡፡

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሁሉም አካባቢዎች፣ የሀድያ፣ የጉራጌ፣ የስልጤ፣ የወላይታ፣ ጌዲዮ ዞኖች እንዲሁም የሲዳማ ክልል እና የደቡብ ምዕራብ ክልል ዞኖች፣ ቄለም ወለጋ፣ ኢሉአባቦራ፣ ቡኖ በደሌ፣ አርሲ እና የምዕራብ አርሲ ዞኖች፣ ምስራቅና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ድሬዳዋና ሐረሪ፣ ሁሉም የጋምቤላ ዞኖች፣ ሲቲ እና የፋፈን ዞኖች ከሚኖራቸው እርጥበት አዘል አየር ጋር ተያይዞ በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ የዝናብ መጠን ያገኛሉ ያለው ኢንስቲትዩቱ፤ የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች አልፎ አልፎ ከሚኖራቸው የደመና ሽፋን መጨመር በስተቀር በአብዛኛው ደረቅ ሆነው እንደሚቆዩ ትንበያዎች ማመላከታቸውን አስታውቋል፡፡

የነሐሴ ወር በአብዛኛው የመኸር አብቃይ አካባቢዎች ከእርጥበታማ እስከ በጣም እርጥበታማ ሁኔታ የሚያመዝንበት መሆኑን ያስታወሰው ኢንስትቲዩቱ በመግለጫው፤ የሰሜን ምስራቅ የአርብቶ አደር አካባቢዎች የተሻለ እርጥበት የሚኖራቸው ጊዜ ቢሆንም አልፎ አልፎ የሚከሰት በረዶ አዘል ዝናብና ጎርፍ በእርሻ ሥራ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያድር የሚችልበት ጊዜ መሆኑንም ጠቁሟል፡፡

በመሆኑም የሚጠበቀው ከባድ ዝናብ በረዷማ፣ ውሃ ገብና በወንዝ ዳርቻ ባሉ ማሳዎች ላይ በሰብሎች፣ በእንስሳትና በንብረት ላይ ጉዳት እንዳያስከትል አስፈላጊውን የክትትልና ቅድመ መከላከል እርምጃዎች መውሰድ እንደሚገባም ኢንስትቲዩቱ ጨምሮ አሳስቧል፡፡

# "ሕወሓት ለሰላማዊ ንግግሩ ቅድመ ሁኔታ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

እየተዘጋጀ ነው ብለዋል። በመንግሥት በኩል ያለፈው ስህተት እንዳይደገም የቡድኑን ባህርይ ግምት ውስጥ ያስገባ ዝግጅት ማድረግ ይኖርበታል ሲሉም አሳስበዋል።

በሕወሓት በኩል የመጣው ቅድመ ሁኔታ ዓላማው ሰላማዊ ንግግር ማካሄድ ሳይሆን የሚፈልጉትን ነገር ማግኘት ነው። ድርድሩ የማይሳካ ከሆነ ወዴት ሊሄዱ እንደሚችሉ መታወቅ አለበት። ከዚህ በፊት ተመሳሳይ በሆነ መንገድ "በፍቅር እንደመር በይቅርታ እንሻገር" በሚል የተጀመረው በጎ ተግባር በቡድኑ እምቢተኝነት ምክንያት ፍሬ ሳያፈራ ቀርቷል። አሁንም ቡድኑ ቅድመ ሁኔታ በማስቀመጡ ዲፕሎማሲያዊ ኪሳራ ደርሶበታል ሲሉም ተናግረዋል።

እንደ አቶ አንዳርጋቸው ገለጻ፤ የሕወሓት ቡድን አባላት ሁልጊዜም የለመዱት የራሳቸውን ፍላጎትና ጥቅም በሌላ ኃይል ኪሳራ ማስፈጸም ነው። በመሠረታዊነት ሰላም፣ ሰጥቶ መቀበልና በሰላም መነጋገር የሚባል ነገር የላቸውም፤ ለራሳቸውና ለትግራይ ሕዝብ ሰላም ሲሉ እንኳን ጉዳዩን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ይመጣሉ ብሎ ማሰብ አይቻልም።

አሁን መንግሥት መዘጋጀት ያለበት ንግግሩ ከከሸፈ የባለፈው አይነት ጭፍጨፋ እንዳይፈጠር እንደሆነና በአሁኑ ወቅት መከላከያው የተጠናከረ በመሆኑ የሚያሰጋ ነገር አለመኖሩንም አስረድተዋል።

መንግሥት የተሻለ አቅምና ዝግጅት ቢኖረውም፤ በሕዝባዊ ማዕበል መልክ በአማራና በአፋር ክልሎች በኩል ውጊያ ለማድረግ ሙከራ ሊያደርጉ ስለሚችሉ፤ ለዚህ ዝግጁ ከሆነ በኋላ የሰላም ውይይቱን ማስኬድ እንደሚቻልም አመላክተዋል። የሰላም ውይይቱን አልፈው ወደ ጦርነት ከመጡ ምላሽ ለመስጠት በበቂ መዘጋጀት ያስፈልጋል።

ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መነጋገር ምንም ችግር የለውም፤ ምክንያቱም በውይይቱ ወቅት የትኛውንም ሀሳብ ማቅረብ ስለሚቻል። እነሱም ያለቅድመ ሁኔታ ብለው መጥተው ቅድመ ሁኔታ ያስቀመጡትን ሀሳብ በጠረጴዛ ማቅረብ ይችላሉ ነው ያሉት።

ምዕራባውያን ምዕራብ ትግራይ ብለው የሚጠሩትን ወልቃይት ለራሳቸው እንዲመቻቸው ኮሪደሩን በሕወሓት እጅ እንዲገባ ይፈልጋሉ ያሉት ፖለቲከኛው፤ የማይቻል መሆኑን ከአወቁ በምስራቅ አፍሪካ ሰፊው ሕዝብና መንግሥት ጋር ላለመጣላት ተላላኪውን ወያኔ መክዳት አማራጫቸው መሆኑን ተናግረተዋል።

አቶ አንዳርጋቸው፤ የሕወሓትና የመንግሥት ጉዳይ ሊቋጭ የሚችለው ቡድኑ በሚገባ ሲሸነፍ እና ከትግራይ ሕዝብ ጫንቃ ላይ ሲነሳ ነው፤ የውጭ ጣልቃ ገብነት ሳይኖር ሕዝቡ በሂደት የሚያምፅበትን ሁኔታ መፍጠር የሚጠይቅ በመሆኑ መደረግ ያለበትን ነገር በሙሉ መንግሥት ማድረግ አለበት ሲሉም አስገንዝበዋል።

# አለርት ሆስፒታል ሦስት...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ቢኖሩም የሕክምናው ነገር አሳሳቢ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባትም አለርት ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የላንቃና የከንፈር መሰንጠቅ ያለባቸውን ሕፃናትን ወረፋ ሳይጠብቁ የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ እየተሠራ መሆኑን ነው፡፡

በሆስፒታሉ የተደረገው የግንባታ እና ማስፋፊያ ሥራ የላንቃና የከንፈር ክፍተት ያለባቸው ሕሙማን ያለወረፋ አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችል ነው ያሉት ዶክተር ኢስማኤል፤ አሁን ወረፋ እየጠበቁ ያሉ በርካታ ሕፃናት መኖራቸውን ገልፀው በቅርብ ጊዜያት ውስጥ ዜሮ ለማድረግ እየሠራን ነው ብለዋል፡፡

የሕፃናት የከንፈርና የላንቃ ክፍተት ሕፃናት በጊዜ አፋቸውን እንዳይፈቱ ከማድረጉም ባሻገር፤ ምግብ የመብላት፣ የመተንፈስ የመሳሰሉ ችግሮች ያስከትልባቸዋል፡፡ የትምህርት አቀባበላቸው ላይም ተፅዕኖ ስለሚያመጣ ብዙ የሀገር መሪዎችና ባለሙያዎች ሀገሪቱ እያጣች መሆኑን ዋና ሥራ አስኪያጁ ገልፀው ይህ ችግር በቶሎ እንዲፈታ ሆስፒታሉ የሥራ ሰዓትን ከማሻሻል ጀምሮ ያደረገው ማስተካከያ ከተገነቡት የቀዶ ሕክምና ክፍሎች ጋር ተዳምሮ ውጤታማ ይሆናል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በተጨማሪም ሆስፒታሉ ለሕሙማኑ ተደራሽነቱን ለማስፋት ቀለል ያሉ ቀዶ ሕክምናዎችን በከፊል ሰመመን የማከም ፕሮግራም ይዞ እየሠራ መሆኑንና በዚህም ብዙ ታካሚዎችን እየደረሰ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

የሚሰጠው የሕክምና አገልግሎትም በስማይል ትሬይን ድርጅት ድጋፍ አማካኝነት በነፃ መሆኑን አክለው ገልፀዋል፡፡

በተለይ ለላንቃና ከንፈር ክፍተት ታማሚ ሕፃናት እና ቤተሰቦች እፎይታ ይፈጥራሉ የተባለላቸውን የኦፕራሲዮን ክፍሎች ኪድስ ኦ.አር እና ስማይል ትሬይን የተባሉ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እንዲሁም ጤና ሚኒስቴርና አለርት ሆስፒታል ተባብረው የሠሯቸው መሆኑን ኃላፊው አብራርተዋል፡፡

የስማይል ትሬይን ድርጅት የምሥራቅ አፍሪካ ማኔጀር ወይዘሮ ሰስኒ ዘሚካኤል በበኩላቸው፤ ድርጅቱ በኢትዮጵያ ሥራውን የጀመረው በ2006 ጀምሮ መሆኑን ገልፀው፤ አሁን የተሠራው የቀዶ ሕክምና ክፍል በሆስፒታሉ እና በስማይል ትሬይን መካከል ያለ ጠንካራ ወዳጅነት ማሳያ ነው ብለዋል፡፡

ድርጅቱ በኦፕራሲዮን ክፍሎች ብቻ ሲሳተፍ አልነበረም ያሉት ወይዘሮ ሰስኒ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ በአቅም ግንባታ እና ተመሳሳይ ሥራዎችን ሲሠራ መቆየቱን



እና ባለፉት ዓመታት በኢትዮጵያ ከ33 ሺህ በላይ ሕፃናት የከንፈርና የላንቃ ሕክምና መስጠቱን ገልፀዋል፡፡

ዶክተር ይገረሙ ከበደ በአለርት ኮንፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የፕላስቲክና ኮነስትራክቲቭ ሰርጀሪ ባለሙያ ናቸው፡፡ እንደርሳቸው ገለፃ የተገነቡት የቀዶ ሕክምና ክፍሎች በተለይ በከንፈር እና ላንቃ መሰንጠቅ ለተጎዱ ሕፃናት ተደራሽነትን ለማስፋት የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለሰላም የተዘረጋው እጅ በሕወሓት የቅድመ ሁኔታ እንቅፋት እንዳይደናቀፍ!

የመልካም አስተዳደር፣ ኢኮኖሚያዊና መሰል ኢፍትሃዊነት፣ የከፋ የሰብዓዊ ጥሰትና አፈናን የመሳሰሉ የሰው ልጅ ሊታገሳቸው የማይችላቸውን ግፎች ለ27 ዓመታት ተሸክሞ የኖረው የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ለሁሉም ልክ አለው እንዲሉ ግፍና መከራው ሲከፋበት፣ ጭቆናና ስቃዩ ጫንቃው ላይ ተጭኖ አላላውስ ሲለው "በቃኝ" ብሎ ከዳር ዳር ተነሳ:: እናም የግፉን ቀንበር ጫኞች፣ የአፈናውን መረብ ጣዮች ከመንበረ ስልጣናቸው አሽቀንጥሮ በመጣል፤ በለውጥ ትግሉ ውስጥም የራሳቸውን አሻራ ያሳረፉ የለውጥ አመራሮችን በቦታቸው ተካ::

ይህ ሁነት ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ከፍ ያለ የደስታ ስሜት፤ የእፎይታ ድባብ የፈጠረ ቢሆንም፤ ለሕወሓት እና ከውጭ ሆነው ሕወሓትን በስልጣኑ ዘመን ለሚጋልቡት ኃይሎች ግን የሚዋጥላቸው አልሆነም:: ለምን ቢሉ፤ ኢትዮጵያውያን አንድ ከሆኑና በጋራ ቆመው ሕወሓት በተልዕኮ በትረ መንግሥትነቱን ጨብጦ ሲሠራ ከነበረው የመከፋፈልና የተዳከመች አገር የመፍጠር ተልዕኮው በተቃራኒ ስለነጋቸው የተሻለን ነገር ማለም ከጀመሩ እንደ ቀድሞው የማይንበረከኩና ለማንም የማትታዘዝ አገርን እውን ያደርጋሉና ነው::

ይሄን የተረዱ የውጭ ኃይሎች እና አሸባሪው ሕወሓት ታዲያ፤ እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል ዓይነት ነገር ሆኖባቸው ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን ማመስና እረፍት መንሳት ጀመሩ:: ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ እንደ ጋሻ ተጠቅመው ሲያንሳቁሉት የነበረውን የትግራይ ክልል ሕዝብም ለዚህ እኩይ ዓላማቸው እንደ ማስያዣ ተጠቀሙት:: ከወንድም ሕዝቦች ጋር እንዲዋጋ ፈረዱበት:: እምቢ ሲልም በርሃብና በበሽታ እንዲንሳቆል የቀደመ የሴራ አካሄዳቸውን ዳግም ተገበሩበት:: እናም የሰብዓዊ ድጋፍን እንደ መሣሪያ ተጠቅመው ሕዝቡ ሳይፈልግ ወደ እሳት እንዲማገድ፤ ከእነርሱ ውጪ ሌላ አማራጭ እንደሌለው እንዲያስብ ለማድረግ ተረባረቡ:: ለዚህ ደግሞ የውጭ ግብረአበሮቻቸው በእጅጉ ተባባሪዎቻቸው ነበሩ::

በአንጻሩ የኢትዮጵያ መንግሥት ይሄ የሽብር ቡድን አደብ እንዲይዝ ከሚወስደው የሕግ ማስከበር ርምጃ በተጓዳኝ፤ ለትግራይ ሕዝብ ሰብዓዊ ድጋፍ እንዲደርስ እና ሕዝቡ የሰላም አየር እንዲተነፍስ ለማስቻል ተደጋጋሚ የሰላም አማራጮችን እያቀረበ ቢሆንም፤ የሽብር ቡድኑ ሕልውናው የተመሰረተው የትግራይ ሕዝብን እንደራሱ ንብረት ይዞ በጦርነት ውስጥ ሲኖር እንደመሆኑ ይሄን የሰላም አማራጭ ሲገፋና ሲያመክን ቆይቷል::

ከዚሁ ጋር በተያያዘ አንድ አፈ-ታሪክ ማስታወሱ ተገቢ ነው:: ነገሩ እንዲህ ነው፤ አንድ ጎልማሳ ሰው አንድ አዋቂን ሊፈትን ይቀርባል:: ጎልማሳው አንዲት ወፍ በመዳፉ ውስጥ ይዞ ነበር:: እናም በመዳፌ ያለችው ወፍ በሕይወት አለች ወይስ ሞታለች? ሲል በጥያቄ ፈተናውን ይጀምራል:: አዋቂው ሰውም አካሄዱን ቀድመው ተረድተው ነበርና፤ ሞቷም፣ ሕይወቷም በአንተው እጅ ነው፣ ብለው ይመልሱለታል:: ይሄን ያለምክንያት አልነበረም ያሉት፤ በሕይወት አለች ቢሉት ጨፍልቆ እንደሚገድላት ያውቃሉ፤ ሞታለች ቢሉትም የተጨበጠ መዳፉን ከፍቶ በሕይወት መኖሯን እንደሚያሳይና አላዋቂ ናቸው ለማለት እንደተዘጋጀ ተረድተው ነበር:: የትግራይ ሕዝብም እስካሁን በእንዲህ ዓይነት መልኩ በሽብር ቡድኑ መዳፍ ውስጥ ወድቆ ነበር ለፍርድ የተቸገረ ሆኖ የቆየው::

አሁን ግን ይሄ ታሪክ ተቀይሯል:: በፌዴራል መንግሥቱ ከፍ ያለ ትዕግስትና ተጋድሎ፤ በኢትዮጵያውያን ይቅር ባይነትና ሆደ ሰፊነት የሕወሓትን መዳፍ መፈልቀቅ ተችሏል:: ቀሪው የቤት ሥራ የሚሆነው የራሱ የትግራይ ሕዝብ፣ የዓለምአቀፍ ተቋማትና አጋሮች፣ እንዲሁም የሕወሓት አካሄድ ጭምር ነው:: ምክንያቱም የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ ለሰላም በከፈሉት ዋጋ የሽብር ቡድኑ እንዲዳከምና ቆም ብሎ እንዲያስብ ማድረግ፤ የትግራይ ሕዝብም በቡድኑ ከታፈነበት መዳፍ እንዲላቀቅ የሚያስችለውን ምቹ መንገድ ጠርገዋል:: አሁን ቡድኑ መዳፍ ላይ ቆይቶ ዳግም ለመጨበጥ ራስን ማስገዛት፤ አልያም የተከፈተው መዳፍ ዳግም ሳይጨበጥ ከመዳፉ ላይ መነሳት? የሚለው የትግራይ ሕዝብ ሊመልሰው የሚገባው ጉዳይ ነው:: በሌላ በኩል፣ ዓለምአቀፍ ተቋማትና መንግሥታት ይህ ለዘመናት በቡድኑ ሲሰቃይ የኖረው ሕዝብ ለቡድኑና ለእኩይ ኃይሎች ዓላማ ሲባል ዳግም ወደስቃይ እንዲመለስ ይፈርዱበታል፤ ወይስ ከዚህ የጭቆናና ሰቆቃ መዳፍ እንዲላቀቅ ከፌዴራል መንግሥቱ ጎን ሆነው ያግዙታል? የሚለው ተጠባቂ ጉዳይ ነው::

ከዚህ አንጻር የትግራይ ሕዝብ የሽብር ቡድኑ ግፍና አፈና በቃኝ እያለ በተለያየ መልኩ ተቃውሞና እንቢታውን እያሰማ ይገኛል:: ይህ ከሕዝቡ የሚጠበቅ መልካም የለውጥ ርምጃ ነው:: ይህ ሕዝባዊ ፍላጎትና የለውጥ በራሱ በጎ ምላሽ ቢሆንም፤ በሌሎች ካልታገዘ ግን የሚፈለገውን ውጤት ሊያመጣ እንደማይችል እሙን ነው:: ምክንያቱም የሕዝቡ ጩኸትና ተቃውሞ ህልውናውን በጦርነት ውስጥ ለመሠረተው የሕወሓት ቡድን የሚዋጥ አይደለም። እናም ስለ ሰብዓዊነት ግድ ይለናል ከሚል አፋዊ ዲስኩር በዘለለ በሕወሓት አደናጋሪና አደናቃፊ የሴራ ቅድመ ሁኔታ ለሰላም በትእግስት የተዘረጋው የመንግሥት እጅ ዳግም እንዳይታጠፍ እና ሕዝቡ ለሌላ ሰቆቃ እንዳይዳረግ የበኩላቸውን ድጋፍ ማድረግ፤ ለሰላም ንግግሩ መሳካት አዎንታዊ ሚናን መወጣት ከሁሉም ይጠበቃል!

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# በሲቪል ሰርቫንቱ የተዘነጋው የሕዝብ አገልጋይነት

ልዑል መርዕድ

በመንግሥት መስሪያ ቤቶች ውስጥ የሚሠሩ ማናቸውም ሠራተኞች ኅብረተሰቡን የማገልገል ግዴታ አለባቸው። በተጨማሪም መንግሥትና ሕዝብን የሚያገናኙ ድልድዮች ናቸው። ይህን ሁኔታ ተረድቶ ኃላፊነቱን የሚወጣ ሠራተኛ ምን ያክሉ ነው ቢባል መልሱ እንደየአከባቢው የተለያየ መሆኑ እሙን ነው። በአሁኑ ወቅት በመንግሥት መስሪያ ቤቶች ቢኬድ ተገልጋይ ሲንገላታና አስታዋሽ አጥቶ በየጥጋጥጉ መመልከት የተለመደ ነው። ለምን ቢባል አገልጋይ ሠራተኛ በማጣቱ መሆኑን ሀቅ ነው።

ወደ ዋናው ጉዳይ ከመገባቱ በፊት ግን የመንግሥት ሠራተኛ ማለት ምን ማለት ነው? የሚለውን እንመልከት። በፌዴራል የመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 2(1) ስር እንደተደነገገው የመንግሥት ሠራተኛ ማለት በፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤት ውስጥ በቋሚነት ተቀጥሮ የሚሠራ ሰው ነው። ከዚህ ትርጉም የምንረዳው አንድ ሰው የመንግሥት ሠራተኛ ነው የሚባለው በመንግሥት መስሪያ ቤት ማለትም ራሱን ችሎ በአዋጅ ወይም በደንብ የተቋቋመ እና ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል ከመንግሥት በሚመደብለት በጀት የሚተዳደር ሆኖ በሚኒስቴሮች ምክር ቤት በሚወጣው የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ዝርዝር ውስጥ የተካተተ የፌዴራል የመንግሥት መስሪያ ቤት ሲሠራ ነው። በተጨማሪ በየክልሉ ባሉ የመንግሥት መስሪያ ቤት ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩ ሠራተኞችም የመንግሥት ሠራተኛ ይባላሉ።

ታዲያ በፌዴራልም ሆነ በክልል የመንግሥት ሥራ አስፈፃሚዎችና ሠራተኞች ዋነኛ አገልግሎት የሚሰጡት ለሕዝቡ ነው። ሠራተኞቹ ሕዝቡ የሚፈልገውን አገልግሎት ከመስጠት ባለፈ የኅብረተሰቡን ችግር የሚቀርፉ ሀሳቦችን የማመንጨትና የመተግበር ግዴታ ተጥሎባቸዋል። ለምሳሌ ያክል በአንድ ወረዳ የሚኖር ግለሰብ ከመኖሪያ ቤት፣ ከመፀዳጃ እና ከማብሰያ ቤት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ሲኖሩት የሚኖርበት ወረዳ የሚመለከተው ሠራተኛ በአግባቡ ጥያቄውን ተመልክቶ የመፍታት ግዴታ አለበት። በሌላ በኩል ደግሞ ማንኛውም ሰው በሚኖርበት አካባቢ ሰላም የማግኘትና ሠርቶ የመግባት መብቱ እንዲጠበቅ በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ያሉ የፀጥታ አካላት ኃላፊነት አለባቸው።

ሆኖም እነዚህ ነገሮች በሚፈለገው ልክ በተግባር አይታዩም። ለምን ቢባል የተሰጠውን ኃላፊነት የሚወጣ ሠራተኛ እየጠፋ በመምጣቱ ነው። በተለይ የሕዝብ አገልግሎት በሚበዛባቸው አካባቢዎች የሚገኙ ሠራተኞች ሕዝቡን ለማልገል ሳይሆን በወር የሚከፈላቸው ገንዘብ እንዳይቆረጥ ቢሮ የሚገቡ የሚመስሉም ተበራክተዋል። በዚህም ለሕዝቡ አገልግሎት ለመስጠት «ጉቦ» እንደ ግዴታ እየተቆጠረ ይገኛል። ገንዘብ ያልሰጠ ተገልጋይ መብቱን ማግኘት እንደማይችልም በአደባባይ እስከመታወጅ ደርሷል። ለዚህ ማሳያ ደግሞ የነዋሪነት መታወቂያ ለማደስም ሆነ ለማውጣት ያለውን ውጣ ውረድ መመልከት በቂ ነው። አንድ ነዋሪ ከተሰጡት መብቶች አንዱ የነዋሪነት መታውቂያ ማግኘት ነው። ነገር ግን ይሄን መብት ለማግኘት የግድ ገንዘብ መክፈል ይጠበቅበታል። እዚህ ላይ መስተዋል ያለበት ጉዳይ መታወቂያውን ለማግኘት የሚከፈለውን የአገልግሎት ክፍያ አያጠቃልልም።

ሌላው የምንመለከተው ከከተማ እስከ ወረዳ የሚገኙ የመንግሥት ሠራተኞች ቢሮ ውስጥ ወንበር ከማሞቅ በዘለለ ምን እየሠሩ እንደሚገኙ የሚከታተልና የሚቆጣጠረው አካል ማን እንደሆነ አለመለየቱ ነው። በየመስሪያቤቶች ቢኬድ ቁጥሩ የማይናቅ ሠራተኛ ለሥራ ተቀምጦ ኢንተርኔት ሲጠቀም፣ በቡድን ሲወራ ወይም ከቢሮ ውጪ በረንዳ ላይ ተሰብስቦ ነው የሚታየው። በነዚህ ወቅት ተገልጋይ ሲመጣ ትኩረት ሰጥቶ የሚያዳምጠውም፤ ችግሩን የሚፈታለት ሰው አያገኝም። ሠራተኛው የሚከፈለኝ ደመወዝ አነስተኛ ነው በሚል ተገልጋይ ማጉላላቱን እንደ መፍትሄ ይዞታል። የሚያስገርመው ደግሞ ተገልጋይ ሆኖ የሚመጣው ሰው በተገላቢጦሽ በሚሠራበት መስሪያ ቤት ተገልጋይ የሚያጉላላ መሆኑን ሲታይ ነው። አንድ ሰው በመንግሥት መስሪያ ቤት ሲቀጠር ለቦታው የሚከፈለውን ደመወዝ ተቀብሎ ነው። የሚከፈለው አነሰም በዛም የተቀመጠበትን ኃላፊነት የመወጣት ግዴታ አለበት።

ሆኖም ሁሉም ሰው አማራሪ፣ ተቺ እና መፍትሄ ከሰው የሚጠበቅ በመሆኑ መሠረታዊ ለውጥ ማምጣት አልተቻለም። በመንግሥት መስሪያቤት የሚሠራ ሰው እራሱ መንግሥት መሆኑን ስለማይረዳ መሥራት የሚችለውን ወይም መፍትሄ መስጠት የሚገባውን ነገር ሌላ አካል እንዲሠራለት ይጠብቃል።

የሲቪል ሰርቪስ አስተዳደርም ሠራተኛን በአግባቡ ይዞ ከማሠራት ይልቅ የሰዓት ፊርማ ላይ ያተኮረ በመሆኑ ሠራተኛው ለፊርማ ሲል እንጂ ሥራውን ለመሥራት ወደ ቢሮ እንዲገባ እያደረገው አይመስልም። ከዚህ በዘለለም ሠራተኛው ለመንግሥት ሥራ ከመልፋት ይልቅ ከቢሮው ወይም ከወንበሩ አለመጥፋትን እንደ ልማድ እየወሰደው ይመስላል። በዚህ የተሳሳተ እሳቤም በመንግሥት መስሪያ ቤት ውስጥ ከሥራ ይልቅ የሰዓት ፊርማ ትኩረት ተሰጥቶታል። ኅብረተሰቡም የትኛውንም አገልግሎት ለማግኘት መመላለሱን እንደ በጎ ቆጥሮ እየተንቀሳቀሰ ነው።

በዚህ ረገድ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት መንግሥት በተደጋጋሚ ቃል እየገባ ወደ ትግበራ ቢገባም የተለወጠ ሲቪል ሰርቫንት ማግኘት ባለመቻሉ የሕዝቡን ጥያቄ መመለስ አዳጋች እንደሆነበት ይታያል። ከዚህም ባለፈ ስታንዳርዱን የጠበቀ የአገልግሎት አሰጣጥ ለመፍጠር የመጡ ጥናቶች ለውጥ ሳያመጡ እየተረሱ ይገኛሉ። ሠራተኞችን የመመዘን ሥራውም ከሥራ ይልቅ ግለሰብ ጥላቻ ላይ ያተኮሩ በመሆናቸው ለውጥ አምጪ ሠራተኛ ከመፍጠር ይልቅ የመበቃቀያ መንገድ ሆነው እያገለገሉ ናቸው።

በየመስሪያቤቱ የሚገኙ ሠራተኞች የሕዝቡን ችግር የሚፈታ መፍትሄ ከመስጠት ከተገልጋዩ የሚመጣላቸውን ጥያቄ አይሆንም፤ አያስኬድም በሚል የሚመልሱ ሆነዋል። ሠራተኞቹ «ሰጪም ነሺም» በሚመስል መልኩ ሥራቸውን እያከናወኑ ሲሆን፤ በተለይ ይሄ ጉዳይ በክፍለከተማና ወረዳዎች ላይ ይስተዋላል። አገልግሎት ለማግኘትም ገንዘብ መክፈል ግዴታ እንደሆነ መዘንጋት የለበትም። ለዚህ እንደማሳያ ብዙ ነገር መጥቀስ ቢቻልም፣ በመንግሥት መስሪያ ቤቶች ውስጥ እየተከናወነ ያለውን ሁኔታ ለማስቆምም ሆነ ለማስተካከል ጊዜው አልረፈደም።

በተለይ በአገልግሎት መስጫ ተቋማት ውስጥ ያለውን ብልሹ አሠራር ለማስተካከል የሚጠይቀው ቁርጠኝነት እንደመሆኑ ማስተካከል ይቻላል። ለዚህ ደግሞ አስፈፃሚ አካላት በተለያዩ ጊዜያት ስለ ጉዳዩ ብዙ መፍትሄ ሀሳቦች አቅርበው ውይይት አድርገዋል። ብልሹ ሥነ ምግባር ያላቸውን ሠራተኞች ላይም እርምጃ መውሰድ ጀምረዋል። ይሄው ርምጃ በተጠናከረ መልኩ መቀጠል አለበት። አገልግሎት የሚያገኘው ኅብረተሰብም ብልሹ አሠራሮችን በሚመለከትበት ወቅት ተባባሪ ከመሆን በመቆጠብ ለሚመለከተው ጥቆማ መስጠትን እንደ ግዴታው መቁጠር ይኖርበታል። ከሕግ አካላት ለሚቀርብለትም የትብብር ሥራ ቀና የሆነ ምላሽ መስጠት አለበት። የሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር አዋጆችም ሆኑ መመሪያዎች በአግባቡ ተግባራዊ እንዲሆኑ እንዲሁም እስካሁን ያለው አሠራር የሚፈተሽበት ሁኔታ መፈጠር አለበት። በየመስሪያቤቱ የሚገኙ ሠራተኞች ከፊርማ ይልቅ በሥራ የሚመዘኑበት ሁኔታ ላይ መስራት ይኖርባቸዋል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።



**በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)**
fenote1971@gmail.com

## ከክሽፈት ወደ ከፍ ያለ ልዕልና

የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ መንግሥት፣ በታሪካዊ ጠላቶቻችንና በቡችሎቻቸው በየአቅጣጫው እንደ ቆዳ ተወጥሮ እያለ፤ የኢትዮጵያ ታላቁ የሕዳሴ ግድብ በሙስና፣ በብልሹ አሠራርና በኮንትራት አስተዳደርና አመራር ድክመት ተደቅኖበት ከነበረ የለየለት ክሽፈት ታድጎ ኃይል ማመንጨት መጀመሩ እና ለ3ኛ ዙር ውኃ ሙሊት ማብቃቱ፤ የሁለተኛው ተርባይን ፍተሻም እያገባደደ መሆኑ እጅግ የሚደነቅ አፈጻጸም ከመሆኑ ባሻገር ከክሽፈት ወደ ከፍ ያለ ልዕልና እምርታ የተደረገበት ሽግግር ነው ማለት ይቻላል። ከዚህ ጎን ለጎን የአገራችንን ጨምሮ የዓለም ኢኮኖሚ በኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ጫና ስር ወድቆ እያለ ሜጋ ፕሮጀክቶች ሳይስተጓጎሉ ማስቀጠል መቻሉ በልኩ እውቅና ሊቸረው ይገባል። ለመጀመሪያ ጊዜ 375 ሜጋ ዋት ኃይል ማመንጨት ከጀመረ በርካታ ወራት ያለፉት የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሰሞኑን ደግሞ የሦስተኛ ዙር ውሃ ሙሌት ወደ መጠናቀቁ ነው። ሙሌቱ በተጀመረበት 2012 ዓ.ም የግድቡ ቁመት (ከባህር ወለል በላይ) 565 ሜትር ሆኖ 4ነጥብ9 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ውኃ ይዟል። በቀጣዩ ዓመት የግድቡ ቁመት(ከባህር ወለል በላይ) 595 ሜትር ደርሶ 13ነጥብ5 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ውኃ ተያዘ። በዚህም ግድቡ የያዘው የውኃ መጠን 18.4 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ደረሰ። በሦስተኛው ዓመት ላይ የግድቡን ቁመት(ከባህር ወለል በላይ) 608 ሜትር ከፍታ ላይ በማድረስ 10ነጥብ5 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር ውኃ የመሙላት እና አጠቃላዩን የውኃ መጠን 28ነጥብ9 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር የማድረስ ግብ ተጥሎ ሌት ተቀን የተሠራው ሥራ ግድቡን ወደ አዲስ ምዕራፍ አሸጋግሮታል።

ከፍ ብዬ ለመግለጽ እንደሞከርሁት በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ አመራር ግድቡ ገጥመውት የነበሩ ስር የሰደዱ ብልሹ አሠራሮች፣ ሙስናና ደካማ የኮንትራት አስተዳደር ተለይተው የእርምት እርምጃዎች ባይወሰዱ ኖሮ ታላቁን የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ከክሽፈትና ከለየለት ውድቀት መታደግ ስለማይቻል ኢትዮጵያውያን ለዚች ታሪካዊ ቀን አይበቁም ነበር። በመጪው ትውልድ ዘንድም ተወቃሽ ይሆኑ ነበር። በሴራ ፖለቲካ፣ በተላላኪውና በባንዳው በጣት በሚቆጠር የትህነግ ገዢ ቡድንና ተባባሪዎች ደባ በየዕለቱ ቅርጹንና ይዘቱ እየቀያየረ በሚቀፈቀፍ ቀውስ ውስጥ ኢትዮጵያውያን ተስፋ የሚያሰንቅ መልካም ዜና በናፈቃቸው በዚህ ቀውጢ ወቅት የ3ኛ ዙር ግድቡን ውኃ የማስያዝ ጥረት በስኬት የመጠናቀቁን ብስራት ለመስማት ከጫፍ መድረስ ምንኛ ተስፋን ያለመልማል።

በብዙ እየተፈተነ ላለው ዜጋም ትልቁን የኢትዮጵያን ስዕል እየተመለከተ ብልፅግናዋን እውን ለማድረግ አቅም ይሆነዋል፡፡ ቅኝ ካለመገዛት ጋር ብቻ ተያይዞ የነበረውን ነፃነትና ሉዓላዊነት በኢኮኖሚያዊ ነፃነትና ብልፅግና ለመድገምም መስፈንጠሪያ ሰሌዳ (ስፕሪንግቦርድ) በመሆን በድህነትና በተመፅዋችነት አንገታቸውን ደፍተው የነበሩ ዜጎች አንገታቸውን ቀና አድርገው በኩራት እንዲራመዱ የሚያደርግ ብሔራዊ (ፍላግሺፕ) ፕሮጀክት ነው። ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ እንዳሉት በድህነትና በኋላ ቀርነት የሚማቅቅ ሕዝብ የተሟላ ሉዓላዊት ሊኖረው አይችልምና፡፡ ስንዴ እየለመኑ፣ እየተመጸወቱ ሉዓላዊነቷን ያላስደፈረች፤ በነፃነት ታፍራና ተከብራ የኖረች አገር ብሎ መመጻደቅን ምሉዕ አያደርገውም፡፡ ከድህነትና ከኋላቀርነት ለመውጣት ከሚያበረክተው የላቀ አስተዋጽኦ ባሻገር አገራችን በቀጣናው የሚኖራትን ጂኦፖለቲካዊ ስፍራ በእጅጉ እየለወጠው ይገኛል። ኢትዮጵያ ኤርትራንና ቀይ ባህርን ካጣች በኋላ በቀጣናው የነበራት ስፍራ ፍጹም እንደተቀየረው ሁሉ፤ የኢትዮጵያ ታላቁ የሕዳሴ ግድብም በቀጣናው የሚኖራትን ጂኦፖለቲካዊ ስፍራ በእጅጉ ከፍ አድርጎታል።

**ከዚህ በኋላ የአገራችን ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታና ጂኦ ፖለቲካዊ ስፍራ ከ1983 ዓ.ም በፊት ወደነበረው ከመመለሱ ባሻገር፤ ከግብፅ የሚተናነስ አይደለም፡፡ ታዋቂው የግሪክ የታሪክ ሰው ሔሮዶተስ እንዳለው ግብፅ የአባይ (የኢትዮጵያ) ስጦታ ሆነች፡፡ በተላላኪዋና በአስካሪሷ ትህነግ የተነጠቅነውን አንድነት ደግሞ በአጭር ጊዜ መልሰን ወደ ቀደመው ገናና ክፍታችን በኩራት እንመለሳለን**

የአረቡ ዓለም የነዳጅ ባለቤት መሆኑ ከተረጋገጠ እኤአ በ1948 ዓ.ም እሥራኤል የአይሁዶች መንግሥት ሆና ከቆመች፣ ከ1993 ዓ.ም የመስከረም 1 ቀን የሽብር ጥቃት በኋላ የአሜሪካ የምዕራባውያንና የዓለምአቀፍ ተቋማት የውጭ ግንኙነትና ዲፕሎማሲ ማጠንጠኛ ነዳጅ፣ የእሥራኤል ደህንነት እና የጸረ ሽብር ዘመቻ ሆነ፡፡ ለእነዚህ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች ተግባራዊነት ዳግም ከአረቡ ዓለም ግብፅ ቀዳሚዋ ስትራቴጂካዊ አጋር ሆና ተመርጣለች። ግብፅን ተመራጭ ያደረጋት ለምዕራባውያን የጡት ልጅ እሥራኤል ጎረቤት መሆኗ፤ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጧ በተለይ የስዊዝ ቦይ ባለቤት መሆኗ፤ የእስላማዊ ትምህርት ማዕከል እና የአረብ ብሔርተኝነት አቀንቃኝ መሆኗ፤ ዜጎቿ ከሌላው የአረብ ዓለም ጋር ሲነጻጸር በዓለማዊም ሆነ በእስላማዊ ትምህርት የገፉ በመሆናቸው በምዕራባውያንም ሆነ በእስላማዊው ዓለም ዘንድ ሞገስ አግኝታለች፡፡ ይህን ሞገሷን የአረቡን ዓለም ጨምሮ የአረብ ሊግን እንዳሻት ለማሽከርከር ትጠቀምበታለች፡፡

በልዩነትና በክፍፍል የሚንጠራወዘው የአረቡ ዓለም ግብፅ ከፍ ብላ እንድትታይ ረድቷታል፡፡ ይህን መከፋፈል እሥራኤልን ጨምሮ አሜሪካውያን ሆኑ ምዕራባውያን ይፋ ባያወጡትም የሚደግፉት ስለሆነ ግብፅ ሽብልቅ ሆና እንድታገለግል አሞሌ እያላሱ (ብድርና እርዳታ እየሰጡ) በአናቱ የጦር መሣሪያ እያስታጠቁና ወታደራዊ ስልጠና እየሰጡ ይንከባከቧታል፡፡ አሜሪካ ብቻ በየአመቱ በቢሊዮኖች የሚገመት የጦር መሣሪያ እርዳታ፣ ወታደራዊ ድጋፍና የልማት ድጋፍ ታደርግላታለች፡፡

ግብፅ በአጸፋው ይህን ውለታ ከግምት ያስገባ እና እኤአ በ1979 በአንዋር ሳዳትና በእሥራኤል መካከል የተፈረመውን የሰላም ስምምነት መሠረት ያደረገ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ቀርጻለች፡፡ የአገሪቱን ኢኮኖሚ፣ ደህንነትና ፖለቲካ በመዳፉ የጠቀለለው የግብፅ ጦርና ደህንነት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲን ተግባራዊነት ያረጋግጣል፤ በዓይነ ቁራኛም ይከታተላል፡፡ ከአረቡ አብዮት በኋላ በምርጫ የፈርኦኖችን በትረ ስልጣን ጨብጠው የነበሩ የመጀመሪያው የእስላም ወንድማማቾቹ አባል ፕሬዚዳንት ሞሐመድ ሙርሲ እንኳ የድርጅታቸውንም ሆነ አክራሪ እስላሞች ግፊት ተቋቁመው የግብፅና እሥራኤልን የሰላም ስምምነት ማክበር ችለዋል። መጀመሪያ በመፈንቅለ መንግሥት በኋላ በምርጫ ወደ መንበሩ የመጡት ፕሬዚዳንት አብዱልፈታህ አልሲሲም ከሳዳት፣ ከሙባረክና ከሙርሲ በላይ የሰላም ስምምነቱን እያስፈጸሙ ነው። የእሥራኤል ጉዳይ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲያቸው ቀኖና ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከእሥራኤል ጀርባ ደግሞ አሜሪካ አለች፡፡ ግብፅ ናይል የህልውናዬ ጉዳይ ነው ብላ በሕገ መንግሥቷ ብታካትተውም በውስጠ ታዋቂ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲዋ የማዕዘን ራስ ቢሆንም በግላጭ ትኩረቱ እሥራኤል፣ ፍልስጤምና አሜሪካ ላይ ነው፡፡

ግብፅ ዓባይን ከምንጩ ለመቆጣጠር፣ አገራችንን ቅኝ ለመግዛት እና ጠንካራ ሉዓላዊ አገር ሆና እንዳትወጣና ይህ ቀን (ዓባይ የተገደበበት ቀን) እውን እንዳይሆን ከ11 ጊዜ በላይ ለወረራ መጥታብናለች፡፡ በስውር ደግሞ ምን አልባት ለሺህ ወይም ለሚሊዮን አመታት አሢራለች፡፡ በተለይ ከ20ኛው ክ/ዘ ወዲህ ደግሞ በእነ ሶማሊያ፣ ሱዳን፣ ጀብሀ፣ ሻዕቢያ፣ ትህነግ ፣ ኦነግና የኦጋዴን ነፃ አውጭ በመጠቀም የውክልና (proxy) ጦርነት በማካሄድ አገራችንን ስታዳክም ኖራለች። አሁንም አልሻባብን ፣ ሕወሓትን ፣ ኦነግ ሸኔንና የተለያዩ ታጣቂዎችን ተጠቅማ አገራችንን ለማተራመስ ሌት ተቀን እየማሰነች ነው። በምሥራቁ የአገራችን ክፍል አልሻባብ ድንበር ተሻግሮ የከፈተብን ጥቃት በግብጽ ቡራኬና ስፖንሰር አድራጊነት መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው። የቀደመ እኩይ አላማዋ ከሞላ ጎደል በመሳካቱ የቤት ሥራዋን በማጠናቀቋ ዝቅ አድርጋ ስታየን ኖራለች፡፡ ከታሪካዊዋ ሐምሌ 15 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ ግን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሁኔታዎች ተቀይረዋል፡፡ ይቺ ታሪካዊ ቀን የሕዳሴው የመጀመሪያ ዙር ሙሊት የተካሄደባት መሆኑን ልብ ይሏል። በሴራና በደባ በቀጣናውም ሆነ በዓለምአቀፍ መድረክ ያሳጣችን ጂኦ ፖለቲካዊ እና ስትራቴጂካዊ ስፍራ ከ30 ዓመታት በኋላ መልሰን ተረክበናል፡፡ ምርኳችንም ተመልሷል፡፡

የቀጣናው ጂኦ ፖለቲካዊ አሰላለፍ በታላቁ የህዳሴ ግድብ እንደ አዲስ ተበይኗል የምለው ለዚህ ነው። ከዚህ በኋላ የአገራችን ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታና ጂኦ ፖለቲካዊ ስፍራ ከ1983 ዓ.ም በፊት ወደነበረው ከመመለሱ ባሻገር፤ ከግብፅ የሚተናነስ አይደለም። ታዋቂው የግሪክ የታሪክ ሰው ሔሮዶተስ እንዳለው ግብፅ የአባይ (የኢትዮጵያ) ስጦታ ሆነች፡፡ በተላላኪዋና በአስካሪሷ ትህነግ የተነጠቅነውን አንድነት ደግሞ በአጭር ጊዜ መልሰን ወደ ቀደመው ገናና ክፍታችን በኩራት እንመለሳለን፡፡

ከፍ ብሎ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለውጡ ማግስት የኢትዮጵያ ታላቁ የሕዳሴ ግድብ ገጥሞት ከነበር ውስብስበ ሙስናና ብልሹ አሠራር ተላቆ ከክሽፈት መዳኑ ሲረጋገጥ፤ ግብጽ ያለ የሌለ ኃይሏን አቀናጅታና አሟጣ አገራችን ላይ የዲፕሎማሲ፣ የሚዲያና እንደ ሕወሓትና ኦነግ ሸኔ ያሉ ቡችሎቿን በመጠቀም የእርስ በርስ ግጭት ለመቀስቀስና አገራችንን ለማተራመስ ያልፈነቀለችው ድንጋይ የለም። ከሕወሓት የሰሜን ዕዝ ጥቃትና ከቀሰቀሰው ጦርነት፤ ከሸኔና ከጀሌዎቹ የንጹሐን ጭፍጨፋ፤ ከጅግጅጋው ጭፍጨፋ፤ ከኦሮሚያና ከሱማሌ ግጭት፤ ከአፋርና ከኢሳ ግጭት፤ በየዩኒቨርሲቲዎች ይቀሰቀሱ ከነበሩ ግጭቶች፤ ከድምጻዊ ሀጫሉ ግድያና እሱን ተከትሎ ከተፈጸመው ግፍና ሰቆቃ፤ ከኢኮኖሚ አሻጥሩ፤ ከምዕራባውያን የተቀናጀና የተናበበ ጸረ ኢትዮጵያ ዘመቻ፤ ከእነ አምነስቲና ሒውማን ራይትስ ዋች የስማ በለው ሪፖርት፤ ከሀሰተኛና መርዘኛ መረጃዎች፤ ወዘተረፈ ጀርባ የግብጽና የተላላኪ ባንዳዎች እጅ አለበት።

ሰሞኑን በተላላኪዋ አልሻባብ በሱማሌ ክልል በተቃጣው ተደጋጋሚ ትንኮሳም ሆነ በሌላው ተላላኪዋ ሸኔ በምዕራብና ቄለም ወለጋ እንዲሁም በጋምቤላ በተፈጸሙ ግፎችም እጇ አለበት። ከሳውዲ አረቢያ የዜጎቻችን ግፍ ጀርባም የግብጽ ረጅም እጅ አለበት። በዚህ አራት አመት እንደአገርና ሕዝብ የገጠመን ፈተና በታሪክ ታይቶም ሆነ ተሰምቶ አያውቅም። በአንድም በሌላ በኩል ጎልቶ መሳፍርት የሌለው ሰቆቃ የሁሉንም ቤት አንኳኩቷል። ሁሉም ዋጋ ከፍሏል። ይሄን ሁሉ ዋጋ እየከፈልን ያለነው አባቶቻችን ያቆዩንን ነፃነትና ሉዓላዊነት ለማስከበርና ለማስቀጠል ነው። የተፈጥሮ ሀብታችንን አልምቶ ለመጠቀም ነው። በድህነትና በኋላቀርነት እየማቀቁ ነፃነትና ሉዓላዊነት ሙሉዕ ስለማይሆን ነው ይሄን ሁሉ መከራ የተቀበልነው። ወደፊትም የትኛውንም ፈተና ለመጋፈጥ ዝግጁ የሆነው። በአንድ መጣጥፌ የሕዳሴው ግድብ እየሆንለት ያለው ነገር ሁሉ ይገባዋል (worth it) የምለው ለዚህ ነው ።

**እንደጀመርን እንጨርሰዋለን !**

# ወቅታዊ

# ‹‹በዓለም አቀፍ ደረጃ የሳይበር ዲፕሎማሲ አንገብጋቢ አጀንዳ ሆኗል››

**- አቶ ሰለሞን ሶካ**

*የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ምክትል ዋና ዳይሬክተር*

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

**በዛሬው ዕትማችን የወቅታዊ አምድ ዋነኛ ማጠንጠኛ የሳይበር ደህንነት እና የሳይበር ጥቃቶችን ማዕከል ያደረገ ነው። በዚህም ከአገር እስከ ዓለም ሁኔታዎችን ስመዳሰስ ሙከራ አድርገናል፡፡ በጉዳዩ ዙሪያም የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ምክትል ዋና ዳይሬክተር ከሆኑት ከአቶ ሰለሞን ሶካ ጋር ቆይታ አድርገናል፡፡**

**አዲስ ዘመን፡- የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር (ኢመደአ) እንደ አገር ከተቋቋመበት ዓላማ አኳያ ምን ተግባራትን እያከናወነ ነው?**

**አቶ ሰለሞን፡-** የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር (ኢመደአ) የአገሪቱን የኢንፎርሜሽን እና ኢንፎርሜሽን መሠረተ ልማት ከሳይበር ጥቃት ለመከላከል የተቋቋመ ነው።ለመከላከል ደግሞ አገራዊ አቅምን በመፍጠር በዓለም አቀፍ ምህዳር ኢ-ተገማችና ተለዋዋጭ ከመሆኑ አንፃራዊ ዘርፉን የሚመጥን የሰው ኃይል ልማት፣ ተቋማዊ አደራጃጀትና በርካታ ተግባራትን ለመከወን በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከ15 ዓመት በፊት ራዕይ ተሰንቆ የተቋቋመ እና ዓላማውንም እየፈጸመ ያለ ተቋም ነው።በተለይም ከለውጡ በኋላ የተለያዩ ማሻሻያዎች በማድረግ ሕዝብ፣ አገርና መንግሥትን የሚያገለግል ተቋም ሆኗል።ከዚህ በፊት ለአንድ ፓርቲ ብቻ የሚያገለግል ነበር።አሁን ግን ተቋሙ ብዙ የኢትዮጵያ ምሁራን የአገር መሪዎች የፈሩበትም ተቋም ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እንደ አገር የሪፎርም ሥራዎች ከተጀመሩ ወዲህ የተገኙ ውጤቶች ምን ነበሩ፤ በአሁኑ ወቅትስ ምን ደረጃ ላይ ይገኛል?**

**አቶ ሰለሞን፡-** ኢመደአ ከተቋቋመለት ዓላማ አንፃር የአገሪቱን የኢንፎርሜሽን እና ኢንፎርሜሽን መሠረተ ልማትን ከሳይበር ጥቃት በመጠበቅ የኢንፎርሜሽን የበላይነትን የማረጋገጥ ሥራ ያከናውናል።ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ የቴክኖሎጂ ባለቤትነትን ከማረጋገጥ አንፃር ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን አከናውኗል።አገሪቷም ብዙ ክልከላዎች ያሉበት ቴክኖሎጂዎች ላይ ትኩረት አድርጎ በመሥራት የቴክኖሎጂ ባለቤት እንድትሆን አድርጓል።ባለፈው ሥርዓትም የአንድ ፓርቲ መዘወሪያ ሆኖ ነው የቆየው።ምንም እንኳን ጥሩ የሚባሉ ሥራዎችን ይሠራ የነበረ ቢሆንም አንዳንድ ከሕግ ወጣ ያሉና ዜጎችን የማስፈራራት ነገሮች ይታዩበት ነበር።የሪፎርሙ አንዱ ዓላማ ይህ ተቋም ኢትዮጵያን እንዲመስል ማድረግ ነው።ይህም ማለት የአንድ ፓርቲ መዘወሪያ ሳይሆን ሁሉም ኢትዮጵያውያን ገብተውበት ባላቸው እውቀትና የአገር ፍቅር ለአገራቸው የሚያገለግሉበት ተቋም መሆን አለበት በሚል የአደረጃጀት ለውጥ ተደርጓል፡፡

በዚህም የሙያተኞች ድልድል ተደርጓል።አንድ ፓርቲ ተኮር ከመሆንና ሁሉም ኢትዮጵያውያን እንደ ሁለተኛ ዜጋ ሳይሆን ቀጥታ ማገልገል እንዲችሉ ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል።ሪፎርሙን የሚመጥን ስትራቴጂካል ፕላንም ተዘጋጅቷል።ተቋሙ አሁናዊና መፃዒ ችግሮችን እንዲቋቋም ተደርጎ ተሠርቷል።በዚህ ረገድ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተቋማዊ ለውጥን ሪፎርም በማድረግ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል የተከሰተውን የሕግ ማስከበርና የሕልውና ዘመቻ ተቋሙ በጣም በአጭር ጊዜ ራሱን ሪፎርም በማድረግ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል።በዚህ ረገድ ለሕዝብና ለአገር ኩራት መሆን ችሏል።ሌላው ለውጥ አመጣን የነገውንም ትውልድ ታሳቢ ያደረገ ጉዞ ነው የምንለው የሳይበር ታለንት ማዕከል ተቋቁሟል።በዚህ ማዕከል ውስጥ የተለያዩ ልጆችና ታዳጊ ወጣቶች ባላቸው ልዩ ተሰጥዖ ተቋሙ ዘንድ መጥተውና ተሰጧቸው ለምቶ የተለያዩ የቴክኖሎጂ ምርቶችና የሥራ ውጤቶች እንዲወጡና የአገሪቱ ሳይበር እና ዲጂታል ሉዓላዊነቷ የተጠበቀ እንዲሆን ከወዲሁ የሳይበር ሰራዊት እያለማን እንገኛለን።

ሌላው ከታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የውሃ ሙሌት፤ የህልውና ዘመቻ እና ሌሎች የኢትዮጵያን ዕድገት በማይፈልጉ ታሪካዊ ጠላቶች ባላቸው ፍላጎት ከፍተኛ ቁጥር ያለው የሳይበር ጥቃት ደርሶብናል።ባለፈው ዓመት የነበረው 2ሺ897 የሳይበር ጥቃት ሲሆን በዚህ ዓመት በሦስት እጥፍ አድጎ ወደ 8ሺ845 ደርሷል።በ2012 ዓ.ም ከነበረው አሁን ያለው ልዩነቱን ብንመለከት በአምስት እጥፍ አድጓል።ስለዚህ የጥቃቱ ሂደት ሲታይ በጣም እያደገ ነው።በመሆኑም ጥቃቱን የሚመጥን ተቋማዊ መዋቅር ሊኖረን ይገባል።በተጨማሪም በየጊዜው ተለዋዋጭ፣ ኢ-ተገማች የሆነና በማንኛውም ሰዓት ምን ጥቃት እንደሚደርስ በማይታወቅበት ሁኔታ በጣም ንቁ ሆኖ የአገሪቱን ኢንፎርሜሽንና ኢንፎርሜሽን መሠረተ ልማት ከሳይበር ጥቃት የሚከላከል የሰው ኃይል ዝግጁነትና አቅም ማጎልበት መሠረታዊ ሥራ መሆኑ ታምኖበታል። በአጠቃላይ በሪፎርሙ እነዚህን ውጤቶችና ድሎች አግኝተናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ላይ የደረሱ የሳይበር ጥቃቶች በማን፣ መቼ እና ከየት እንደሆነ በትክክል ማወቅ ይቻላል?**

**አቶ ሰለሞን፡-** በሳይበሩ ዓለም ልክ እንደ ኮንቬንሽናል ጦርነት እንደሚደረገው አይደለም።‹‹ኮንቬንሽናል ጦርነት ፊት ለፊት የሚደረግ ጦርነት ነው።የት እንደምትዋጋ፣ ከማን ጋር ውጊያው እንደሚካሄድ፣ መቼ እንደምትዋጋ ይታወቃል።በሳይበር ዓለም እንደዚህ የለም።ከአሜሪካ ጥቃቱን ወርውሮ ከግብጽ የተደረገ ማስመሰል ይቻላል።ስለዚህ ከዚህ ነው ማለት አይቻልም።ነገር ግን ትኩረት ከሚያደርጉበትና ከሚደርሰው አቅጣጫ ወይንም ጥቃት አንፃር ትንተና ተደርጎ ይህ ሊሆን ይችላል ይባላል፤ እንጂ ከዚህ ነው ሊባል አይችልም፡፡››

ለማንኛውም ኢትዮጵያ ላይ ከደረሱት ጥቃቶች መካከል የታላቁን ህዳሴ ግድብን የውሃ ሙሌት በሚመለከት ‹‹ብላክ ፒራሚድ ዋር›› የሚባል ጥቃት ደርሶብናል።ይሄ የግድቡን የውሃ ሙሌት ለማስተጓጎል የተደረገ ሙከራ ነው።37 ሺ እርስ በእርሳቸው የተሳሰሩ ኮምፒዩተሮች ላይ አደጋ ለማድረስ የተቃጣ ቢሆንም በሳይበር ሰራዊታችን ማክሸፍ ተችሏል።ከዚህ ባሻገር በርካታ ጥቃቶች ተፈፅመዋል።ከ8ሺ845 ጥቃቶች ውስጥ 45 ከመቶ የሚሆኑት ቁልፍ መሰረተ ልማት ወይንም የኢንፎርሜሽን እና ኢንፎርሜሽን መሠረተ ልማት ቅኝት ወይንም ስለላ ላይ ያነጣጠሩ ናቸው።ከጥቃቶች 20 ከመቶ የሚሸፍኑት ደግሞ የድረ ገፅ ጥቃቶች ናቸው።ከእነዚህም አብዛኞቹ መክነዋል።ሆኖም የተወሰኑ ጥቃት ደርሰዋል።18 ከመቶ የሚሆነው የሳይበር ጥቃት ደግሞ ‹‹ራን ሰምዌር አታክ›› ነው።በአጠቃላይ ሲታይ ተቋማት የሳይበር መከላከል አቅም በዚህ ዓመት 97 ከመቶ መድረስ ተችሏል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ውስጥ በሳይበር ጥቃት ማዕከል የተደረጉ ተቋማት እነማን ናቸው?**

**አቶ ሰለሞን፡-** ዒላማ የተደረጉ ተቋማትን መንገር እንችላለን።ጥቃት አድራሻቹንም ፍላጎትና የሚመጣው ተፅዕኖ ማየትም ተገቢ ነው።የአገሪቱ ቁልፍ መሰረተ ልማትና በኔትወርክ የተሳሰሩትን ያማከለ ነው።ለአብነት የኢትዮ-ቴሌኮም መሰረተ ልማት፣ የህዳሴው ግድብና ሌሎች የኃይል ማመንጫ እና ማስተላለፊያ መስመሮች የጥቃቱ ዒላማዎች ነበሩ።የአገሪቱ የመወዳደሪያ አቅም የምንላቸው የኢትዮጵያ አየር መንገድ የመሳሰሉትም በዚህ የሚታዩ ናቸው፡፡

ቁልፍ መሰረተ ልማት ላይ ጥቃት ሲደርስ በርካታ ኢንዱስትሪዎችና የሕዝብ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን ማናጋት ነው።በዚህም 45 ከመቶ የሚደርሰው ጥቃት ቁልፍ መሰረተ ልማትን ዒላማ ያደረገ ነበር።በመቀጠል የፋይናንስ ተቋማት ዒላማ ነበሩ።ዓላማው ገንዘብ ለማግኘት ነው።በዚህም ሲስተሙን በመያዝና በማመሳጠር ብሎም በማገት ገንዘብ እንዲከፈል የመደራደር ጥቃት ነው።ሦስተኛው የሳይበር ጥቃት ዒላማ የገቡት መገናኛ ብዙኃን አውታሮች ናቸው።ይህ ከህልውና ዘመቻው ‹‹ግራጫ ጦርነት የተባለው›› ጋር የሚያያዝ ነው።የመንግሥት የፖለቲካ አደረጃጀቶችን ከፌዴራል እስከ ክልል የደረሰ ነው።ዩኒቨርሲቲዎችና የጤና ተቋማትም የሳይበር ጥቃቱ ዒላማዎች ሆነው ተገኝተዋል።ይህን ጥቃት የሚያደርጉትም የግለሰቦችን መረጃ ጭምር ለመመንተፍ አሲረው የሚሠሩ ናቸው፡፡



ፎቶ፡ ኤዮብ ተፈሪ

**አዲስ ዘመን፡- ከሳይበር ጥቃቶቹ በስተጀርባ በአገር ውስጥ ተባባሪዎች ወይንም ባንዳዎች ይኖሩ ይሆን?**

**አቶ ሰለሞን፡-** በቴክኖሎጂ ላይ ይብሳል።በሠራተኞችና በዜጎች የሚከሰተውን በሦስት ከፍለን ማየት እንችላለን።አንደኛው ስለጉዳዩ ጥልቅ እውቀትና ግንዛቤ ባለመኖሩ፤ ሁለተኛው ለሳይበር ጥቃት አጋላጭ የሚያደርገውና ስለጉዳዩ እያወቁ ትኩረት አለመስጠት ወይንም ንዝህላል መሆን ሲሆን ሦስተኛው ሆን ተብሎ ከውስጥ ጉዳት የሚያደርሱና ለአጥቂዎቹ መረጃ አሳልፈው የሚሰጡ ባንዳዎችና ጥቃት እንዲደረስ የሚያደርጉ ናቸው።ከጥቃቶች 65 ከመቶ በላይ በዚህ ሳቢያ የሚፈጠሩ ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ ከሳይበር ጥቃቶቹ በስተጀርባ ያሉ ተባባሪዎችን ለመለየት የተደረገ ሙከራ አለ?**

**አቶ ሰለሞን፡-** ይህ 65 ከመቶ የሳይበር ጥቃት በኢትዮጵያ ብቻ ያለ ለሕዝብ ሳይሆን አጠቃላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ በሳይበር አግባብ ጥናት ሲካሄድ ባለማወቅ፣ እያወቁ ትኩረት አለመስጠትና በውስጥ ባንዳዎች ከ65 እስከ 90 ከመቶ የሚደርሱ የሳይበር ጥቃቶችን አሀዝ ያመለክታል።በአገራችን ሲታይ በሳይበር ጥቃት ወይንም ደህንነት የመከላከል አቅምን በሚመለከት በርካታ ተቋማት ራሳቸው ግንዛቤ የሌላቸው ናቸው።ጉዳዩን እያወቁም ዝም ያሉ አሉ።ሁኔታውን ተረድተው እየሠሩ የሚገኙም አሉ።

እኛ ግን እንደተቋም የሳይበር ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ ሥራዎች አሉን።የሳይበር ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ አሠራርና መስፈርት አለ።በዚህ ዓመት ብቻ ስድስት ሰነዶችን ቀጥታ ለቀናል።በመሆኑም ተቋማት እነዚህን ሰነዶች ወስደው በተቋማቸው መተግበር አለባቸው።በትግበራ ሂደት ውስጥ ስልጠና እንሠጣለን፤ እናማክራለን፤ እንደግፋለን።በዚህም የተጠቀሙ በርካታ ተቋማት አሉ።ተቋማት የሳይበር ደህንነት አስተዳደር ሥርዓት መተግበር አለባቸው።ይህ አንደኛው ሥራ ነው።ሁለተኛው የሳይበር ደህንነት ፍተሻ እና ግምገማ ወይንም ኦዲት የሚባል ሥራ አለ።ይህን አውቀው ከተቋማችን ጋር የሚሠሩ አሉ።በተለይም በፋይናንስ ዘርፍ ያሉ የመንግሥትና የግል ቁልፍ መሠረተ ልማቶችን የያዙ ተቋማት ከተቋማችን ጋር በቅርበት እየሠሩ ነው።ምክንያቱም በአንድ ጊዜ የሚመጣ ክስተት ወይንም ጥቃት ከፍተኛ ጉዳት ስለሚያደርስ በትኩረት እየሠራን ነው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ተቋማት የኦዲትና ግምገማ ሥራ ማሠራት ይኖርባቸዋል።ሦስተኛው ተቋማት በተከታታይ በዓመት ሁለት ጊዜ ለሠራተኞቻቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ

# ወቅታዊ

መስጠት አለባቸው።በዓመት አንድ ጊዜ ደግሞ የኦዲትና ግምገማ ሥራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል።የሚሰጣቸውን ምክረ ሐሳብ በመመርኮዝ የሳይበር ደህንነት ፖሊሲያቸውን፣ ስታንዳርዳቸውንና መመሪያቸውን ጊዜውን በጠበቀ፣ ቴክኖሎጂውን በሚመጥን አግባብ ማሻሻል ይኖርባቸዋል።በዚህ ረገድ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር (ኢመደአ) በቂ የሆነ የአሠራር ሥርዓትና የአገልግሎት ሥርዓትን ዘርግቶ እያገለገለ ይገኛል።በሁሉም ተቋማት ተደራሽ ለመሆንና በአካል ሄዶ ስልጠና መስጠት ከፍተኛ የሆነ የሰው ኃይል አቅም ስለሚጠይቅ፤ በሚቀጥለው ዓመት በዲጂታል ቴክኖሎጂ በመታገዝ ተግባራዊ እናደርጋለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ተቋማትን ለሳይበር ጥቃት ተጋላጭ ያደረጉና ተባባሪ የሆኑትን የመለየት ሥራ ተከናውኗል?**

**አቶ ሰለሞን፡-** አሁን በነገርኩህ የአሠራር ሥርዓት ተቋማት ሲተገብሩ የራሳቸው የሆነ የደህንነት ኦፕሬሽን ማዕከል ይኖራቸዋል።ቀጥታ በኦዲትና ፎረንሲክ ለማግኘት የሚሰጡ አገልግሎቶች በፖሊስ መረጃ ሲመጣ የምንሰጠው አገልግሎት ነው።አሁን ግን እየተናገርኩ ያለሁት ተቋማት ውስጥ ጉዳዮችን ለመጠበቅ ማድረግ የሚጠበቅባቸውን ነው።ተቋማት የሳይበር አስተዳደር መተግበር ብሎም በተከታታይ ግምገማ እና ኦዲት ማስደረግ አለባቸው።መሰል አሠራር ሲኖር ማን ምን እንዳደረገ በግልጽ ይታያል ማለት ነው።ይህ በሌለበት ግን ሌላ አገልግሎትም እንሰጣለን፡፡

ለምሳሌ በቅርቡ በአዲስ አበባ የጋራ መኖሪያ ቤቶች (ኮንዶሚኒየም) ዕጣ አወጣጥ የተደረገው የቴክኖሎጂ ውንብድና ከተከሠተ በኋላ ልክ እንደፖሊስ ወንጀል ምርመራና ኦዲት ይደረጋል።በተጨማሪም የዲጂታል ፎረንሲክ ምርመራ ይደረጋል።በዚህም ድርጊቱን ማን ፈፀመ የሚለውን መለየትና ጉዳዩ ለሚመለከተው የሕግ አካል፣ ለፖሊስ ወይንም ለፍርድ ቤት ተቋሙ መረጃ ያቀርባል።እነዚህን መሰል አገልግሎቶችንም እንሰጣለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የ99 ተቋማትን የሳይበር ኦዲት ማድረጉ ይታወቃል።በኦዲት ምን ክፍተቶች አገኙ?**

**አቶ ሰለሞን፡-** ያየናቸው ክፍተቶች ኢንፎርሜሽን መሠረተ ልማት ሲዘረጉ የሳይበር ደህንነትን ታሳቢ አለማድረግ ወይንም የመዘናጋት ጉዳይ መኖሩን ነው።አንድ ሶፍትዌር ሲበለፅግ ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን የራሱ የሆነ ሥርዓት አለው።ይህን ከዌብ ሳይታችን ላይ (secure software development cycle) የሚል ጋይድላይን ማግኘት ይቻላል።በተጨማሪም ደህንነቱ የተጠበቀ ስለመሆኑ እኛ ዘንድ ኦዲት ቢያስደርጉ ወይንም የደህንነት ሰርተፍኬት ቢያገኙ ደህንነታቸው የተጠበቀ ይሆናል፡፡

የዳታ ማዕከል፣ ኔትወርክና የመሳሰሉትን መሠረተ ልማቶች ሲዘረጉ፤ ከመዘርጋታቸው በፊት ከፍተኛውንና ዝቅተኛ ደረጃ ዲዛይን ቢያስመረምሩ በተቋማችን አማካይነት ደህንነቱን ቢያስመረምሩ እንዲሁም ከዘረጉም በኋላ ‹‹ሪስክ አሰስ›› ኦዲት ቢደረግላቸውና የደህንነት ሰርተፍኬት ቢያገኙ ቢያንስ ለአንድ ዓመት ደህንነታቸው የተጠበቀ ይሆንላቸዋል።ይህ በየዓመቱም መቀጠል ይኖርበታል።ቴክኖሎጂዎችን ገዝቶ መጠቀም እንጂ ደህንነቱ የተጠበቀ ነው ወይ የሚለው ላይ መዘናጋት አለ።በተለይም ‹‹ኦን ፕሪሚስ›› እና ‹‹ክላውድ›› ላይ ነው፤ የራሴ ተቋም ስለሆነ ማን ያጠቃኛል በሚል በርካታ ጥፋቶች ይኖራሉ፡፡

ሌላው በዘርፉ የተሰማሩ የአይ.ቲ ተቋማት ራሳቸው ደህንነቱን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል።ሶፍት ዌር የሚያለማ የአይ.ቲ ተቋም የአገሪቱን ደህንነቱ የተጠበቀ ሶፍትዌር ደረጃን ያሟላ ስለመሆኑ የእኛን የደህንነት ሰርተፍኬት ቢያገኝ ገበያው ላይ ተቀባይነትም ይኖረዋል።የዳታ ማዕከል የሚገነባ ተቋም የደህንነት ሰርተፍኬት ወይንም የአይ.ኤስ.ኦ እውቅና ቢኖረው ኢንዱስትሪው ላይ ትልቅ ጥቅም ያገኛል።ይህ ካልሆነ ዝም ብሎ አገልግሎት የሚሰጥ ሶፍት ዌር መጠቀምና የተቋማትን ምስጢር የማይጠብቅ ከሆነ አደጋው የከፋ ነው።መረጃዎቹም በመንታፊዎች እጅ ይገባል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ሶፍትዌሮችን በማልማትና በመጠቀም ረገድ ሩቅ ባለመጓዛችን በነፃ ከጎገል በማውረድ የሚጠቀሙ በርካታ የአገራችን ተቋማት አሉ።ኢትዮጵያን ይህን መሰናክል አልፋ ቴክኖሎጂ ወደ ውጭ የመላክ ውጥን አሳት ይሆን?**

**አቶ ሰለሞን፡-** በጣም ቁልፍ ጥያቄ ነው ያነሳኸው።ተቋማትን ለሳይበር ጥቃት ተጋላጭ ከሚያደርጉ ምክንያቶች አንዱ የተበተነ ሶፍት ዌር መጠቀም ነው።መሰል ሶፍት ዌር መጠቀም ነፃ ቢመስልም ነፃ ግን አይደለም።መረጃዎች በእጃቸው ያስገባሉ።ይህ የመላ አፍሪካውያን ችግር ነው።ይህ ቴክኖሎጂን ከመግዛት አቅም ጋር ይያያዛል።ይህን ለማቃለልና የሳይበር ጥቃት ተጋላጭነትን ለመጠበቅ የተቋማችን ፍልስፍና የቴክኖሎጂ ባለቤትነትን ማረጋገጥ ነው።ይህ ማለት አንድ አካል



ራሱ የፈጠረውና የሠራውን ሥራ በራስ ቁጥጥር ሥር ማድረግ ነው።በመሆኑም የሳይበር ጥቃትን ለመከላከል በተቋማችን ሆነ በሌሎች ተቋማት ወይንም በግል ድርጅቶች የሚለሙትንና አገር በቀል የሆኑ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በጣም እናበረታታለን።

አገር በቀል ቴክኖሎጂዎችን የመጠቀም ባህሪ መዳበር አለበት።ተቋማት የተበተነ ወይንም የተሰረቀ ሶፍትዌር ከሚጠቀሙ የግል ድርጅቶች አልምተው በእኛ ደህንነቱን ያረጋገጠ ሶፍትዌር ቢጠቀሙ ይመከራል።የሌላን አገር ሶፍት ዌር በዶላር ከመግዛት በአገር ቢዝነስ በቂ የሆነ እና አዳጊ የሚሆን ሶፍት ዌር መጠቀምና የግሉን ዘርፍ ማገዝም ይገባል።በእኛ ረገድ የኢንተርፕራይዝ አፕሊኬሽኖች በቴክኖሎጂ ባለቤትነት ብለን በርካታ ምርቶችን አምርተናል።ይህንን ወደ ግሉ ዘርፍ እንለቃለን።የግሉ ዘርፍ በአገር ደረጃ የሥራ ዕድል ችግር አለ ይባላል።ይህም በዲጂታል ኢኮኖሚ ከፍተኛ የሥራ ዕድል ይፈጥራል።እነዚህን ምርቶች ለእነርሱ አሳልፈን ብንሰጥ አገር ተጠቃሚ ትሆናለች፡፡

በአገሪቱ ዩኒቨርሲቲዎች የተመረቁ በርካታ የኮምፒዩተር ኢንጂነሪንግ ባለሙያዎች አሉን፤ በርካታ ተቋማትም አሉን።ከዚህም በተጨማሪ ዘርፉ ድንበር የለሽ ነው።በመሆኑም በሥራ ዕድል ፈጠራው በርካታ ቁጥር ያለው የሰው ኃይል ማፍራት ይቻላል።ለምሳሌ በእኛ አቅም የለማ እና የተተገበረ ኢ.አር.ፒ አለ።ይህ ብዙ የሥራ ዕድል ይፈጥሯል።አንድ የሕንድ ኩባንያ ኢ.አር.ፒ በማልማቱ ብቻ በ90 አገራት ላይ የኢንተርፕርይዝ ሲስተሞችን በመተግበሩ ለ120ሺ ሰዎች የሥራ ዕድል ፈጥሯል።በመቶ ሺዎች የሥራ ዕድል የሚፈጥርም ነው።በኢትዮጵያ ውስጥ በተሳካ ሁኔታ የምናደረገው ነገር በሌሎች ተቀባይነት ለማግኘት ይረዳል።አፍሪካን መያዝ እንችላለን።አንድ ምርት ማለት በጣም ትልቅ ነው።አብዛኛዎቹ የአፍሪካ አገራት ከእኛ የበለጠ ሥርዓት የላቸውም።በመሆኑም ጠንክረን ከሠራን ብዙ የውጭ ምንዛሪ የምናገኝበት ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ የተመረቱና ለአብነት የሚነሱና የተሞከሩ የደህንነት ቴክኖሎጂዎች አሉ?**

**አቶ ሰለሞን፡-** እንደ ኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የደህንነት ምርቶች የሞከርናቸው አሉ።ግብረ መልሱም በጣም ጥሩ ነው።ይቻላል የሚለው ነገር አይተናል።እኛ የምንጠቀመውን ምርት ለሌላ የአፍሪካ አገር ሸጠን ጥሩ ግብረ-መልስ አግኝተናል።እኛም እነርሱም እየተጠቀምን ነው፡፡

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ቀጣይ ዕይታ ሁለት ነው።በመሆኑም ኢትዮጵያ በ2023 ዓ.ም ስትራቴጂ ቀርፃ እየሠራች ነው።በዚህም ተቋሙ ላለፉት 15 ዓመታት ያረጋገጣቸውን የቴክኖሎጂ ባለቤትነት ይቀጥላል፤ የተወሰኑትን ደግሞ ወደግሉ ዘርፍ በማዞር የዲጂታል ትራንስፎርሜሽኑ እንዲሳለጥ ሚናውን ይወጣል፡፡

የዲጂታል ትራንስፎርሜሽኑን የሚመጥኑ ቴክኖሎጂዎች ላይ በተለይም ተራማጅና ነገን ታሳቢ ያደረጉ ቴክኖሎጂዎችን የምርምርና የልማት ሥራዎች ይቀጥላል።ይህ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽኑን ከማገዝ አኳያ እንደአንድ ሳይበር ደህንነት ተቋም የምናደረገው የትኩረት መስክ ነው፡፡

ሁለተኛው ኢትዮጵያ በ2023 ዓ.ም ዲጂታል ትሆናለች ሲባል፤ የዲጂታል ሉዓላዊነት የሚባል ጥያቄ ምላሽ ሊኖረው ይገባል።ዲጂታል በሆነን ቁጥር የዜጎቻችን ሕይወት በጣም እየቀለለ፣ የተሳለጠ እና ብልፅግና የምንለው ነገር ቀላል ይሆናል።እንደሌላው ዓለም ዜጎቻችንም ቴክኖሎጂን እንደቅንጦት ሳይሆን እንደ ዕለት ተዕለት ኑሯቸው የሚጠቀሙበት፤ መልካም አስተዳደርንና ግልጽነትን የሚያሰፍን፣ ሕይወትን የሚያሳልጥ ይሆናል።በዚያው ልክ ደግሞ ተጋላጭ መሆንም ይኖራል።ተጋላጭነት ደግሞ ከዲጂታል ሉዓላዊነት ጋር ይያያዛል።በመሆኑም ተቋሙ የዲጂታል ሉዓላዊነትን ለማረጋገጥ ከወዲሁ በስትራቴጂ የተደገፈ አብሮ የሚሄድና የሚያድግ የሳይበር ደህንነት እየተገበረ ነው፡፡

በሂደት ደግሞ ሳይበር ታለንት ወይንም የነገ ትውልድ መሆንና መፈጠር አለበት።ይህ ተቋም የዛሬ 15 ዓመት በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ተቋቋመ።በአሁኑ ወቅት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጎች በዚህ ተቋም ውስጥ ይሠራሉ።በአገር ህልውና ላይ የተጋረጠውን ጦርነትም መመከት የቻለና የራሱን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረገ ተቋም ተገንብቷል።በወቅቱ ጥቂቶች ባለሙያዎች ነበሩ፤ አሁን ላይ እየሠሩ ያሉት ባለሙያዎች ትናንት ከነበሩት ይለያሉ።ለነገው ደግሞ ከአሁኑ እንሠራለን፤ መልካም ዘርም እንዘራለን።ታለንት ማዕከል ዓላማው ይህ ነው።ነገ ላይ ኢትዮጵያን የሚጠብቁና ሊከላከሉ የሚችሉ እንዲሁም በሳይበር ደህንነት ከተከታይነት ወደ መግራት ወይንም መሪነት ሊያሸጋግር የሚችል ትውልድ የመቅረጽና ማፍራት አደራ ስላለብን ከወዲሁ በትኩረት እየሠራን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በሳይበር ደህንነት በአገራትና ተቋማት መካከል ትብብር ይጠይቃል።ኢትዮጵያ በዚህ ረገድ ምን እየሠራች ነው?**

**አቶ ሰለሞን፡-** ይህ በጣም ቁልፍና ወሣኝ ጥያቄ ነው።የሳይበር ደህንነት በባህሪው ተለዋዋጭና ድንበር የለሽ ነው።አሁን የሳይበር ደህንነት አጥቂዎች ተበራክተዋል።አገራትም በሳይበር ደህንነት የመወዳደሪያ አቅም አድርገው ይሠራሉ።ስፖንሠር የሚያደርጉ አታከሮች አሉ።ነገር ግን ግለሰቦች ደግሞ በጣም ልቀዋል።በመሆኑም በሳይበር ደህንነት የአንድ አገር ጉዳይ መሆኑ ቀርቶ የዓለም ጉዳይ ሆኗል።በመሆኑም በትብብር መሥራት የህልውና ጉዳይ ነው፡፡

በመሆኑም የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ከሁሉም የፀጥታ ተቋማት ጋር ይሠራል።ዒላማ የተደረጉ ቁልፍ መሠረተ ልማት ከሚያስተዳድሩ አካላት ጋር፣ ከመገናኛ ብዙኃን ተቋማት፣ ከፋይናንስ፣ ከትምህርትና ጤና ተቋማት ጋር እየሠራን ነው።እንዲሁም ከዜጎች ጋር መሥራት አለብን ብለን አቅደን ዜጎቻችን የሳይበር ወታደር መሆን አለባቸው በሚል በ2015 ዓ.ም የምናስተዋውቀው ዜጎች የራሳቸውን ሳይበር ደህንነት ተጋላጭነት የሚፈትሹበት፣ ስልጠና የሚወስዱበት፣ በመወዳደር ለአገራቸው የሳይበር ሰራዊት የሚቀላቀሉበትን ሥርዓት ገንብተናል።የሳይበር ደህንነት የሁሉም ድርሻ መሆን አለበት በሚል እየሠራን ነው።በዓለም አቀፍ ደረጃ ደግሞ የሳይበር ዲፕሎማሲ አንገብጋቢ አጀንዳ ሆኗል።አብዛኞቹ አገራት በዚህ ላይ የሰው ሀብት እያለሙ ይገኛሉ፤ እኛም እየሠራንበት ነው፡፡

በቅርቡ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን ወደ ሳውዲአረቢያ ጉብኝት አድርገው ነበር።አንዱ የመወያያ ነጥባቸው የነበረው የሳይበር ደህንነት ጉዳይ ነው።የሳይበር ደህንነት ይህ ዓለምን ስላስተሳሰረ አንድ ቦታ የተፈጠረ ችግር ወደ ሌላ ቦታ የመዛመት ዕድሉ ሰፊ ነው።ስለዚህ አገራት፣ ተቋማትና ዜጎች የየራሳቸውን ሚና እንዲወጡ አብሮ የመሥራቱ ጉዳይ በጣም ወሳኝ ነው።እኛም እንደተቋም በዚህ ላይ ከሌሎች አገራት ጋር እየሠራን ነው።በዓለም አቀፍ ደረጃ የተደራጁ ማህበራት አሉ፤ አባል ለመሆንም ሂደት ላይ ነን።በአገራትና ተቋማት መካከል የ‹‹ሳይበር ኢንተለጀንስ ሼሪንግ›› መኖር አለበት።ምክንያቱም የሳይበር አጥቂዎች ከተቋማት የመከላከል አቅም በላይ እየሆነ በመምጣቱ በጋራና በትብብር መሥራት ብሎም ዲፕሎማሲው ላይ መሥራት ይገባል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ያለችበት የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና ሽብርተኝነት አንዱ ሥጋት ነው።የሳይበር ቴክኖሎጂን በመጠቀም ኢትዮጵያን ለማተራመስ የሚደረገውን ሴራ በማክሸፍ የሚኖረው ሚና እና ቀጣይ ሥጋቶችን በተመለከተ የተቋማችሁ ትንተና ምን ይመስላል?**

**አቶ ሰለሞን፡-** አንደኛው የሳይበር ደህንነት የአገሪቱን የኢንፎርሜሽን እና ኢንፎርሜሽን መሠረተ ልማት ከሳይበር ጥቃት ለመከላከል ነው።ሌላው የኢንፎርሜሽን እና ኢንፎርሜሽን መሠረተ ልማት በመጠቀም ለዕኩይ ዓላማ የሚያውሉትን አካላት የመቆጣጠር ሥራ እንሠራለን።ሽብርተኞች ለመገናኘት የሚጠቀሙት ሌላ ሳይሆን፤ የሳይበር ቴክኖሎጂን ነው፡፡

ዋናው ዓላማ የአገሪቷን ሠላም ማረጋገጥ ነው።ከፀጥታ አካላት ጋር እንሠራለን ሲባል የአገር መከላከያ የሚፈለገውን መረጃ እንደግፋለን ማለት ነው።‹‹በሳይበሩ ዓለም የምናገኛቸውን የሽብርተኞች መረብ፣ የጂኦ-ፖለቲካውን ፍላጎትና ኢኮኖሚውን ባገናዘበ መልኩ ትንተናዎች ይደረጋሉ››።አስፈላጊ መረጃ ተተንትኖ ለሚመለከተው የውሳኔ ሰጪ አካል ይቀርባል።ይህም አስፈላጊውን እርምጃ ለመውሰድ ዕድል ይፈጥራል።መሬት ላይ ከአሸባሪዎቹ ጋር የሚዋጉት ይህን መረጃ በማድረግ ነው።ዝም ተብሎ ስልክ በመደዋወል ብቻ የሚሆን ሳይሆን ትልቅ እገዛ ያስፈልጋል።ኢትዮጵያን ይህንን የማድረግ አቅምና ዝግጁ ነበራት፣ አላት ለወደፊትም ትኩረት ሰጥታ ትሠራለች፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ተቋማችሁ 2014 በጀት ዓመት የተሠሩ አንኳር ተግባራት ምንድን ናቸው፤ ቀጣይ ትኩረታችሁስ?**

**አቶ ሰለሞን፡-** በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት ብቻ 8ሺ845 ሳይበር ጥቃት ደርሶብናል።ከእነዚህ ውስጥ 96ነጥብ7 ከመቶ የሚሆነውን መመከት ተችሏል።በዘጠኝ ወራት ተጽዕኖው ተገምግሞ 5ሺ864 ጥቃት ነበር።በዚህም 1ነጥብ4 ቢሊዮን ብር ማዳን ተችሏል።29 ሚሊዮን ብር የሚገመት ደግሞ ኢትዮጵያ አጥታለች።ይህ እንደአገር በጣም ትልቅ ስኬት ነው።ሌሎች አገራት ይህን የመሰለ የመከላከል አቅም ሲገነቡ በጣም ያጩኹታል።ይሁንና ጉዳዩ ኢ-ተገማችና ተለዋዋጭ በመሆኑ የምንኩራራበት አይደለም።ነገ የሚሆነውን አናውቅም፤ ሁልጊዜም ለቀጣይ ስጋት ራሳችንን ዝግጁ እናደርጋለን፡፡

በሳይበር ደህንነት ላይ በአሁኑ ወቅት እንደልምድና ስጋት የመጣው ግለሰቦች በጣም ጎልተው የወጡበት የዲጂታል ሀብትን በመያዝና በማገት ገንዘብ እየጠየቁ ሲሆን ይሄ ለዓለም ሥጋት ነው።ስለዚህ ለመከላከል ዜጎችን የማንቃት ሥራ መሥራት አለበት።ተቋማት የሳይበር ኦዲት ማስደረግ ላይ መሥራት አለባቸው።መፍትሄዎች ላይ እየሠራን ነው።አገራትን እያፈረሰ ያለው ሌላው ሶሻል ምህንድስና ነው።የማህበራዊ ምህንድስና ጥቃት ዓይነት ቴክኒካልና (የኮዲንግ እውቀት ሳያስፈልግ የሰውን ልጅ ማህበራዊና ሥነ-ልቦናዊ ማሳመኛ ዘዴዎችን በመጠቀም የሚፈጸም የሳይበር ጥቃት ዓይነት ነው። የኢንፎርሜሽን የበላይነት በመያዝም አደጋ እየፈጠረ ነው።ሊቢያ እና ሌሎች አገራትም የፈረሱት በዚህ ነው።

ጥቃት አድራሾች የጥቃታቸው ዒላማ ያደረጉትን አካል በቀላሉ በማሳመን የሚፈልጉትን ነገር በቀላሉ ካለ ግለሰቡ ፈቃድና እውቅና ውጪ ምስጢራዊ የሆኑ መረጃዎችን የማግኘትና ጥቃት የመፈፀም ዘዴ ነው።መረጃዎች እንደሚያሳዩት፤ በዓለማችን ከተከሰቱ የሳይበር ጥቃቶች ውስጥ ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዘው በሰው ልጅ ንቃተ ህሊና ማነስና የሰውን ልጅ ደካማ ጎን ተከትለው የሚፈጠሩ ስህተቶች ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- የማህበራዊ ሚዲያዎች ተፅዕኖን ለመቋቋም፤ በራሳችን ለመዘወርና ባለቤትነት ለማረጋገጥ ብሎም የአገር ደህንነትን ለማስጠበቅ ምን እየተሠራ ነው?**

**አቶ ሰለሞን፡-** ሶሻል ሚዲያን በሚመለከት አቅሙ አለ።ዋትስአፕን የሚተካ፤ ‹‹ስርኩን›› የሚባል ኢትዮጵያዊ ምርት አለን።‹‹ደቦ›› የሚባለው ደግሞ ዙም ይተካል።ያሆ፣ ጂሜልን፣ ኢሜል የሚተካ ደግሞ ‹‹ኤርጋ›› የሚባል አለን።እነዚህ በትክክል በመጠቀም አገርን የታደጉ ምርቶች ናቸው። ቴክኖሎጂው አለን።ግን ይህን በስፋት ለማልማት እጅግ ከፍተኛ ሀብት ይጠይቃል።መንግሥት ብቻውን አያለማም።ሶፍት ዌር አለን።ባለሀብቶች ተሰባስበው ዳታ ማዕከሉን ካለሙ እንሰጣቸዋለን፤ የሕዝብ ሀብት ይሆናል።ሁሉንም ነገር መንግሥት ላይ አይተውም።በተጨማሪም ተቋማት ጋር የሶሻል ሚዲያን ‹‹ሬጉሌት›› ማድረግ ላይ ትኩረት አድርገን እየሠራን ነው።ይህም በሕጋዊ መንገድ የሚሠሩትን ለማበረታታት ጥፋት ውስጥ የገቡትን ለማረም ይጠቅማል።

**አዲስ ዘመን፡- ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ላደረጉት ቆይታና ለሰጡን ሙያዊ ማብራሪያ እናመሰግናለን።ተጨማሪ መልዕክት አለዎት?**

**አቶ ሰለሞን፡- እኔም** አመሰግናለሁ።ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያለኝ መልዕክት የሳይበር ደህንነት የሁላችን ኃላፊነት ነው።እያንዳንዱ ሰው ስማርት ስልክ ካለው ለሳይበር ጥቃት ተጋላጭ ነው። ስለዚህ ንቃተ-ህሊናቸውን ማሳደግ አለባቸው።ተቋማችን ይህንኑ አስመልክቶ በተለያዩ ሚዲያዎች የሚተላለፉ መልዕክቶችን እንዲጠቀሙ በአክብሮት እጠይቃለሁ።የአገራችን ምጣኔ ሀብት ስለሚያሳድግና ብዙ የሥራ ዕድል ስለሚፈጥር ወጣቶችንም የዲጂታል ቴክኖሎጂን በጎ ጎኑን እንዲጠቀሙ በትህትህና አሳስባለሁ።ተቋማችን በዘርፉ ጠንካራ ለሆኑ የሥራ ዕድል ይፈጥራል፤ ቢዝነስ መሥራት ለሚፈልጉት ወይንም የራሳቸው ምርት ያላቸውን በታለንት ማዕከላችን ከሳይበር ደህንነት ጋር በተያያዘ ሙያዊ እገዛ እናደርግላቸዋለን።በተረፈ ለአገራችን ልማት፣ ሠላምና የጋራ ዓላማ እንድንቆም ጥሪ አቀርባለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## የአገር ውስጥ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ተሳትፎና ተግዳሮቶች

አንተነህ ቸሬ

ዛሬ በምጣኔ ሀብታቸውና በፖለቲካ ተፅዕኗቸው የዓለም ኃያላን የሆኑት አገራት የአገር ውስጥ ባለሀብቶቻቸውን በመደገፍ ረገድ ትልቅ ተሞክሮ አላቸው:: እንዲያውም ለአሁኑ የምጣኔ ሀብት ኃያልነታቸው መሠረት የሆናቸው ከውጭ ጥገኛነት ያላቀቃቸው የአምራችነት አቅማቸው ማደግ እንደሆነ ይታወቃል::

ኢትዮጵያውያን የአገር ውስጥ ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት ዘርፍ ያላቸው ተሳትፎና ድርሻ በየጊዜው እየተሻሻለ እንደመጣ ባይካድም በቂ የሚባል ግን አይደለም:: የአገር ውስጥ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ተሳትፎና ድርሻ እንዲሁም ተወዳዳሪነት ላቅ ያለ እንዳይሆን የሚጠቀሱት ምክንያቶች ዓይነተ ብዙ ናቸው::

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ባዘጋጀው የድሬዳዋው፣ ሁለተኛው፣ ‹‹ስለኢትዮጵያ›› የውይይት መርሃ ግብር ላይ የግሉ ባለሀብት በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ስላለው ተሳትፎ፣ ስላበረከተው አስተዋፅዖ እና ስላሉበት ችግሮች ገለፃ ያቀረቡት የሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ጀማል አህመድ፣ ለአንድ አገር ዘላቂ እድገት የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ያላቸው ሚና የማይተካ እንደሆነ ጠቅሰው፤ የውጭ ባለሀብቶች ለውድድር እና ተሞክሮዎች እጅግ አስፈላጊ ቢሆኑም ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ቅድሚያ ሊሰጣቸው እንደሚገባም አብራርተዋል።

ዋና ሥራ አስፈፃሚው መንግሥት ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች የሚያደርገውን ድጋፍ ማሳደግ እንዳለበት ጠቁመው፤ ‹‹የአገር ውስጥ አምራቹ ከውጭ አገራት ግብይት ከሚያገኘው የንግድ ሥራ ያገኛትን የውጭ ምንዛሪ ለተጨማሪ ኢንቨስትመንት የማዋል ፍላጎት አለው:: ችግሮች በአንድ ጊዜ አይፈቱም፤ ቢሆንም ግን ለውጭ አገር ባለሀብቶች የሚሰጠውን ያህል ትኩረት ሊሠጠን ይገባል›› ብለዋል። የውጭ ምንዛሬ እጥረትና የአጠቃቀም ፍትሃዊነት መጓደል፣ የሥራ ባህል ደካማነት እንዲሁም ዘርፉን ለማበረታታት የሚወጡ ፖሊሲዎችና መመሪያዎች በአግባቡ አለመተግበር የዘርፉ ባለሀብቶች ዋና ዋና ችግሮች መሆናቸውን አቶ ጀማል አስረድተዋል። አምራች ኢንዱስትሪው ለዘላቂ ልማት ዋነኛ ሞተር በመሆኑ በዘርፉ ያለውን እምቅ ሀብት ለመጠቀም የባለሀብቱ ችግሮች ተለይተው ሊታወቁና መፍትሄ ሊፈለግላቸው እንደሚገባም አሳስበዋል።

‹‹ሁሉም ችግሮቻችን በአንድ ጊዜ ይፈቱልን አንልም፤ አንጠብቅምም›› ያሉት አቶ ጀማል፤ መንግሥት ከባለሀብቱ ጋር ተቀራርቦ በመሥራት ችግሮቹን መፍታት እንደሚገባውም ተናግረዋል። መንግሥት የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን ለመደገፍ የሚያደርገው ጥረት የሚበረታታ ቢሆንም በውጭ ምንዛሬ ጉዳይ ላይ ያለውን ችግር የአቅርቦትና የፍትሐዊነት ችግር ማስተካከል ይገባል›› ብለዋል::

አቶ ጀማል መንግሥት የአገር ውስጥ አምራቾች እንዲበረታቱ ለዓመታት ያከናወነው ሥራ በተለያዩ ዘርፎች የግል ባለሀብቱ እንዲጠናከር አቅም መፍጠሩን ተናግረው፣ በሕዝቡም ሆነ በመንግሥት በኩል የአገር ውስጥ ምርት በመጠቀም ረገድ ያሉ ክፍተቶችን ማስተካከል እንደሚገባ ገልጸዋል። ለዚህም ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› የተሰኘው ንቅናቄ ትኩረት ተሰጥቶት በትክክል ከተተገበረ ትልቅ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ጠቁመዋል::

የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን የመደገፍ ጥረት በብዙ መልኮች ሊገለፅ ይችላል:: የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን የሚያበረታቱ ምቹ የኢንቨስትመንት ፖሊሲዎችን በመቅረፅ፣ ፋይናንስን ጨምሮ ግብዓቶችን በማቅረብ፣ የመሠረተ ልማት አቅርቦትን በማሟላት እንዲሁም ቢሮክራሲያዊ የአሠራር ውጣ ውረዶችን በማቃለል ለባለሀብቶቹ ድጋፍ ማድረግ ይቻላል::

በጂግጂጋ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህር እና የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ ጥናትና ምርምር ዘርፍ ኃላፊ ረዳት ፕሮፌሰር ሀብታሙ ግርማ፣ ኢኮኖሚያዊ የሆኑትን አብዛኞቹን አስፈላጊ የኢንቨስትመንት ግብዓቶች ባለሀብቶቹ በራሳቸው ለማሟላት ጥረት እንደሚያደርጉ አመልክተው፣ መንግሥት ቢሮክራሲያዊ የአሠራር ውጣ ውረዶችን በማቃለል ረገድ ትልቅ ሚና ሊኖረው እንደሚገባ ይናገራሉ::

> **አምራችነቱን ያላሳደገ እና ፍላጎቱንና አቅርቦቱን በራሱ የማምረት አቅም ላይ ያልመሠረተ ምጣኔ ሀብት፣ ዘላቂ እድገትን ሊያስመዘግብ አይችልም:: የአምራችነት አቅምን ለማሳደግና ፍላጎትን በማሟላት ከንግድ ሚዛን ጉድለትም ሆነ ጉድለቱ ከሚያስከትላቸው ምጣኔ ሀብት ጫናዎች ለመላቀቅ አገራዊ አምራችነትን ማሳደግ ያስፈልጋል። አገራዊ የማምረት አቅምን በማሳደግ ምጣኔ ሀብታዊ እድገትን ዘላቂና አስተማማኝ ለማድረግ ደግሞ ሁነኛው መፍትሄ የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን በመደገፍ የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴው ዋነኛ ተዋንያን እንዲሆኑ ማድረግ ነው**

ለአብነት ያህልም መንግሥት አሰልቺ የሆኑ የአሠራር ሰንሰለቶችን በማሳጠርና አገልግሎትን በማቀላጠፍ እንዲሁም የንብረት ጥበቃ በማድረግ ለባለሀብቶቹ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል:: በተጨማሪም ባለሀብቶቹ በኢንቨስትመንት ላይ የሚኖራቸው ተሳትፎ ዘላቂ እንዲሆን መንግሥት የኃይል አቅርቦትን፣ የመንገድና የሎጂስቲክስ አገልግሎቶችን ጨምሮ ለሌሎች የመሠረተ ልማት ችግሮችም መፍትሄዎችን ማበጀት ይጠበቅበታል:: የውጭ ምንዛሬን በፍትሐዊነት ማቅረብም የመንግሥት ኃላፊነት ነው::

‹‹የኢንቨስትመንት ዘርፍ የመንግሥት ድጋፍ እንደሚያስፈልገው ሁሉ፣ ነፃነትም ይሻል›› የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰር ሐብታሙ፣ መንግሥት አላስፈላጊ የሆኑ ጣልቃ ገብነቶችን ላለማድረግ የሚያሳየው ቁርጠኝነትም እንደድጋፍ ሊቆጠር እንደሚችል ይገልፃሉ:: ‹‹መንግሥት በምጣኔ ሀብት ውስጥ የሚኖረው ጣልቃ ገብነት የተጠናና በጥንቃቄ የሚመራ ሊሆን ይገባል:: አላስፈላጊ የሆነ መንግሥታዊ ተፅዕኖና ጣልቃ ገብነት ባለሀብቶችንና ኩባንያዎችን የሚያዳክምና በጥቅል አገራዊ የምጣኔ ሀብት እድገት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድር በመሆኑ የተገደበ ጣልቃ ገብነት መኖር አለበት:: መንግሥት ኢኮኖሚውን ነፃ አድርጎ ችግሮች ሲያጋጥሙ ድጋፍ/ድጎማ በማድረግ ባለሀብቶችን ማገዝ ይኖርበታል። የግሉ ዘርፍ የኢኮኖሚው ዋነኛ አንቀሳቃሽ ሞተር በመሆኑ ይህን ዘርፍ በተደራጀና ተቋማዊ በሆነ መልኩ መምራትና መደገፍ ይገባል›› ይላሉ::

መንግሥት ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ከሚያደርጋቸው ድጋፎች መካከል አንዱ ባለሀብቶቹን የፋይናንስ አቅምና የሥራ ልምድ ባላቸው የውጭ ባለሀብቶች ጫና እንዳይደርስባቸው መጠበቅ እንደሆነ ይታወቃል:: በእርግጥ ይህ እርምጃ አወንታዊ አበርክቶዎች እንዳስገኘ ባይካድም እርምጃው ከምጣኔ ሀብት መርሆችና ከነባራዊ የዜጎችና የአገር ተጠቃሚነት አንፃር ዳግም ፍተሻ እንደሚያስፈልገው ይገለፃል::

በዚህ ረገድ ረዳት ፕሮፌሰር ሐብታሙ ‹‹መንግሥት የአገር ውስጥ ባለሀብቶች አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ እንዲሁም አቅም ባላቸው የውጭ ኩባንያዎችና ባለሀብቶች ጫና እንዳይደርስባቸው ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ያደረጋቸው ጥበቃዎችና የሰጣቸው ማበረታቻዎች ምን ውጤት እንዳስገኙ ማጥናትና መገምገም ያስፈልጋል:: ‹‹በማበረታቻዎቹ ምክንያት አገርና ዜጎች ምን አተረፉ?›› የሚለው ጉዳይ ጥልቅ ምልከታ ይፈልጋል:: የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን ከውጭ ኩባንያዎች ጫና ለመጠበቅ የሚደረግ ማበረታቻ ከነፃ ኢኮኖሚ የውድድር መርህ የሚገኘውን ማኅበረ-ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳ እንዳይጎዳው ማድረግ ተገቢ ነው:: ለባለሀብቶቹ ጥበቃ የሚደረግበት አሠራርም እስከመቼ እንደሚዘልቅ በጊዜ ገደብ ሊታሰር ይገባል:: የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ከውጭ ባለሀብቶች ጋር ተወዳዳሪ የሚሆኑበት አሠራር በተጨባጭ የተግባርና የጊዜ ማዕቀፍ መመዘን አለበት::

በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህርና በ‹‹ፍሮንቲየርአይ (Frontieri)›› ጥናትና አማካሪ ድርጅት ከፍተኛ ተመራማሪ የሆኑት ዶክተር ሞላ አለማየሁ በበኩላቸው፤ የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን መደገፍ ጥያቄ ሊነሳበት የማይገባ ጉዳይ እንደሆነና ተጨማጭ ምጣኔ ሀብታዊ ለውጥ እንደሚያመጣ ይናገራሉ:: ባለሀብቶቹ ምርቶችንና አገልግሎቶችን በማቅረብ ከሚኖራቸው ሚና ባሻገር ለዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ ገቢ ምርቶችን በመተካት እና የወጪ ንግድን በመጨመር ትልቅ አስተዋፅዖ ስለሚኖራቸው ይህን ሚናቸውን የበለጠ እንዲያሳድጉ በመንግሥት ድጋፍ ሊደረግላቸው እንደሚገባ ያስረዳሉ::

እንደዶክተር ሞላ ገለፃ፣ በተለይ ኢትዮጵያ በሥራ አጥነትና በዋጋ ንረት እየተፈተነች ባለችበት በአሁኑ ወቅት የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን መደገፍ እጅግ አስፈላጊ ተግባር ነው:: የመንግሥት ድጋፍ ምጣኔ ሀብቱን በማነቃቃት፣ የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ የገቢ ንግድ ዕቃዎችን በመተካት፣ የወጪ ንግድን በማሳደግ ጥቅል አገራዊ ምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴው ዘርፈ ብዙ ለውጥ እንዲኖረው ያደርጋል::

የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ከሚጋጥሟቸው ችግሮች መካከል የግብዓቶች (መሠረተ ልማቶች) አለመሟላት፣ የፋይናንስ አቅርቦት ችግር እና የውጭ ምንዛሬ እጥረት ዋናዎቹ እንደሆኑ ጠቁመው፤ መንግሥት የአጭር ጊዜ መፍትሄዎችን ጨምሮ የባለሀብቶቹን ችግሮች ለማቃለል የሚረዱ የፖሊሲና የመዋቅር እርምጃዎችን መውሰድ እንደሚኖርበት ይመክራሉ:: ከዚህ በተጨማሪም መንግሥት ለባለሀብቶቹ የሚያደርገውን ድጋፍ በየጊዜው መገምገምና ማሻሻል እንዳለበትም ይገልፃሉ::

የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን መደገፍ አገር በራሷ አምራቾች ላይ እንድትተማመን ያስችላል። ተለዋዋጭ በሆነው የዓለም ፖለቲካ ምክንያት በሚፈጠሩ ችግሮች ከሚከሰት አደጋ ለመዳንም ይረዳል:: በዚህ ረገድ ዶክተር ሞላ ‹‹የአገር ውስጥ ባለሀብቶች በፋይናንስና በቴክኖሎጂ አቅም ከውጭ ኩባንያዎች ጋር ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማድረግ ምጣኔ ሀብታዊ ስብራትና ክፍተት እንዳይፈጠር ለማድረግ ያግዛል:: ቁጥራቸው ጥቂት የማይባሉት የውጭ ኩባንያዎች በአገር ውስጥ የሚቆዩት የአገር ውስጥ ፖለቲካው እስከተመቻቸው ድረስ ነው:: ፖለቲካው ሳይመቻቸው ቀርቶ ኩባንያዎቹ ከአገር ቢወጡ አገሪቱ በርካታ ዓመታት ወደኋላ እንድትመለስ የሚያደርግ አደጋ ይከሰታል። ስለሆነም ይህን ስጋት ለማስወገድ የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን በመደገፍ አቅማቸውን እንዲጎለብቱ ማድረግ ያስፈልጋል›› ይላሉ::

መንግሥት የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ችግሮችን ለማቃለል እየተገበራቸው ከሚገኙ የመፍትሄ እርምጃዎች መካከል የ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› አገራዊ ንቅናቄ ተጠቃሽ ነው:: የማምረት አቅምን ማሳደግ፣ ለዜጎች ተጨማሪ የሥራ ዕድል መፍጠር፣ የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ማሳደግ እና ገቢ ምርቶችን በአገር ውስጥ በመተካት የውጭ ምንዛሬን ማዳን ከ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› መርሃ ግብር የሚጠበቁ ውጤቶች ናቸው::

የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል ንቅናቄው የአገር ውስጥ ባለሀብቶች የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በማቃለል ረገድ አወንታዊ ሚና እንደሚኖረው ገልፀዋል:: የማምረት አቅም በማሳደግ የወጪ ንግድን ለመጨመርና ገቢ ምርቶችን ለመተካት ለሚደረገው ጥረት አወንታዊ አስተዋፅዖ እያበረከተ እንደሆነም ተናግረዋል:: አቶ መላኩ ከንቅናቄው ምሰሶዎች መካከል አንዱ የአገር በቀል ምርቶችንና አመራረትን ማሳደግ መሆኑን ጠቅሰው፣ የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን ሳይደግፉ ይህን ማሳካት እንደማይቻል አስረድተዋል::

‹‹መንግሥት የጀመረው ‹ኢትዮጵያ ታምርት› ንቅናቄ አገራዊ የማምረት አቅምን በማሳደግ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በአገር ውስጥ ምርቶች የመተካት ተግባርን ከማጠናከር እርምጃ ጋር ትስስር አለው›› የሚሉት ዶክተር ሞላ፣ ‹‹ለማምረት ምን ያስፈልጋል?›› ለሚለው ጉዳይ ትኩረት ከተሰጠና ንቅናቄው በተገቢው የፖሊሲ ማዕቀፍ እና በተቀናጀ ጥረት ከታገዘ የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን ችግሮች ለማቃለል አማራጭ መፍትሄ መሆን እንደሚችል ይጠቅሳሉ::

በአሁኑ ወቅት በኢኮኖሚያቸው የበለጸጉት አገራት የአገር ውስጥ ባለሀብቶቻቸውን በመደገፍ ረገድ በርካታ ተግባራትን አከናውነዋል::እነዚህ አገራት ባለሀብቶቻቸውን በማገዝና በመጠበቅ የሠሩት ሥራ የአምራችነት አቅማቸውን አሳድጎ የምጣኔ ሀብት እድገታቸው ዘላቂ እንዲሆን አስችሏቸዋል::

ረዳት ፕሮፌሰር ሐብታሙ እነዚህ አገራት ለአገር ውስጥ አምራቾቻቸው ጥበቃ በማድረግ ትልቅ ሥራ መስራታቸውንና ድጋፋቸውም አሁንም ድረስ የዘለቀ መሆኑን ይጠቁማሉ:: ‹‹አገራቱ የየአገሮቻቸው ምልክት አድርገው የሚቆጥሯቸውን ተቋሞቻቸውን የማበረታታትና የመጠበቅ ሰፊ ልምድ አላቸው:: እነዚህን ተቋሞቻቸውን ደግፈውና ጠብቀው በዓለም አቀፍ ደረጃ ግዙፍና ተፅዕኖ ፈጣሪ ኩባንያዎች እንዲሆኑ አስችለዋቸዋል፤ ዓለም አቀፍ ተቋማት ከሆኑ በኋላም ይንከባከቧቸዋል›› በማለት:: ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች ድጋፍና ጥበቃ ማድረግ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተለመደ አሠራር መሆኑን ያስረዳሉ::

በምጣኔ ሀብታቸው የበለፀጉት የዓለም አገራት የአገር ውስጥ ባለሀብቶቻቸውን ቀደም ባሉት ጊዜያት ብቻም ሳይሆን አሁንም ከፍተኛ ድጋፍና ጥበቃ እንደሚያደርጉላቸው የሚናገሩት ዶክተር ሞላ፣ አገራቱ በፋይናንስ አቅርቦትም ሆነ በሌሎች ዘርፎች ለባለሀብቶቻቸው የተለየ የድጋፍ መርሃ ግብር እንዳላቸው ያስረዳሉ:: ‹‹የበለጸጉት አገራት ለአገር ውስጥ ባለሀብቶቻቸው የሚያደርጉት ድጋፍ፣ ገና በማደግ ላይ ያሉ አገራት ከሚያደርጉት ድጋፍ ቢበልጥ እንጂ አያንስም›› ይላሉ::

ኢትዮጵያ ዘላቂ የምጣኔ ሀብት እንድታስመዘግብ የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን መደገፍና ተወዳዳሪ ማድረግ ይገባል:: ‹‹የአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ›› እንዲሉ የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን መደገፍ ዘርፍ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት:: የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን የመደገፍና ተወዳዳሪ የማድረግ ጉዳይ በምጣኔ ሀብት ትብብርና በእርዳታ ስም የሚደረግን የሀብታም አገራትንና ተቋሞቻቸውን ጣልቃ ገብነት በማስቀረት ሉዓላዊነትን እስከማስከበር ድረስ የዘለቀ ትርጉምና ፋይዳ አለው::

አምራችነቱን ያላሳደገ እና ፍላጎቱንና አቅርቦቱን በራሱ የማምረት አቅም ላይ ያልመሠረተ ምጣኔ ሀብት፣ ዘላቂ እድገትን ሊያስመዘግብ አይችልም። የአምራችነት አቅምን ለማሳደግና ፍላጎትን በማሟላት ከንግድ ሚዛን ጉድለትም ሆነ ጉድለቱ ከሚያስከትላቸው ምጣኔ ሀብት ጫናዎች ለመላቀቅ አገራዊ አምራችነትን ማሳደግ ያስፈልጋል:: አገራዊ የማምረት አቅምን በማሳደግ ምጣኔ ሀብታዊ እድገትን ዘላቂና አስተማማኝ ለማድረግ ደግሞ ሁነኛው መፍትሄ የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን በመደገፍ የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴው ዋነኛ ተዋንያን እንዲሆኑ ማድረግ ነው::

## ጎሜ

# ሲሞላ ይፈሳል፤ ሲከር ይበጠሳል

**ምሕረት ሞገስ**

ዛሬም እንደወትሮ መጠጥ ቤቱ በሰው ታጭቋል።የክረምቱ ቅዝቃዜ ውስጥ ከታጨቀው ሰው ትንፋሽ ጋር ተያይዞ  መስተዋቱ አልቦታል። ተሰማ መንግስቴ እና ዘውዴ መታፈሪያ ከአሜሪካን ከመጣው አቶ ተገኝ ጋር በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ተሰባስበው እየጠጡ ያወራሉ።አቶ ተገኝ ‹‹ ሰው ያላገር መሬት ያለዘር ምንም ትርፍ የለውም›› አለ።ዘውዴ ከተገኝ አፍ ከተል አድርጎ ‹‹ትክክል ብለሃል። ምንም ቢሆን በአገር መኖር ብቻውን ትልቅ ትርፍ ነው።ይህንኑ አውቀን ብንራብም ፤ ብንጠማም ነፃነታችን ቢነፈግም፤ በገዛ አገራችን ብንገፋም ከአገራችን አንወጣም ብለን ሙጭጭ ያልነው በአገር መኖር ያተርፋል ብለን ነው።ትርፉ ትልቅ መሆኑን ስላወቅን ነው›› ሲል ተሰማ መንግስቴ በሁለቱም ሃሳብ ባለመስማማት ኮስተር ብሎ ያዳምጣል።

ተሰማ ፊቱን እንዳጨፈገገ ‹‹የእኛ ችግር ሁሉንም ነገር አጠቃለን በአንድ ቅርጫት ውስጥ መከተታችን ነው።በአንድ ቅርጫት ውስጥ አንድ እንቁላል ከገማ ሁሉንም ያበላሻል።ነጥለን ማስቀመጥ ነጣጥለን ማሰብ ይጠበቅብናል።ከአገር ወጥቶ መኖር ሙሉ ለሙሉ ኪሳራ እና ውድቀት ነው ማለት አይቻልም።በአገር ውስጥም መኖር ብቻውን ትርፋማ ወይም ተጠቃሚ አያደርግም።ውጪ በመኖርም ብዙ ትርፍ አለ። ኢትያጵያ ውስጥ ሁላችንም ማለት ባይቻልም ብዙዎቻችን ለሥራ የምንሰጠው ቦታ ዝቅተኛ ነው።እንደሚታወቀው ደግሞ የተለየ ታታሪ ሰው ካልሆነ በስተቀር በሰነፍ ሰው የተከበበ ‹ሰነፍ ያሰንፋል› እንደሚባለው መስነፉ አይቀርም።የውጪዎቹ ደግሞ ጎበዞች ታታሪ ሰራተኞች ስለሆኑ ኢትዮጵያዊው አገሩ ላይ ሰነፍ ሆኖ ቢኖርም ውጪ ሔዶ ይጎብዛል›› አለ።ተገኝ በሰማው  ቢቃወማቸውም በሃሳቡ እንደሚስማማ ጭንቅላቱን እያንቀሳቀሰ አሳየ።

ዘውዴ ግን መከራከር ፈለገ።አንተ ስትሆን ሁሉም ነገር ትክክል ነው።ሌላው ሰው የሚናገረውም ሆነ የሚሠራው ትክክል አይደለም።‹‹ሁሉንም ለምን ጨፍልቃችሁ ታያላችሁ? ›› እያልክ ትጠይቃለህ።በተመሣሣይ መልኩ በድጋሚ ራስህ ሁሉንም ትጨፈልቃለህ።አንተስ ልክ ነህ ? ሲል ጥያቄ አቀረበ።ተሰማ በበኩሉ ፊቱን ‹‹ምናጠፋሁ›› በሚል መልክ አኮሳትሮ የዘውዴ ጥያቄ እንዳልገባው አስመሰለ፡፡

‹‹ ኢትዮጵያውያን ሰነፍ ናቸው እያልክ ነው።ይህ ተገቢ አይደለም።እኛ የቸገረን የሚያሠራ ከባቢ ነው።የሚያሠራ ከባቢ ካለ ማንም ቢሆን መሥራቱ አይቀርም።የሚያሠራ ከባቢ ሳይፈጥሩ ሰነፍ ብሎ መሳደብ በበኩሌ ትክክል አይደለም፡፡›› እያለ ደረቱን እየገፋ መደንፋት ፈለገ።ተገኝ በመሃል ሆኖ ‹‹ሁለታችሁም ትክክል ናችሁ›› አለ።ዘውዴ በበኩሉ ‹‹ ተገኝ አሁን አንተም ተሳስተሃል።ተቃራኒ ሃሳብ እየተናገርን ሁለታችንም ትክክል መሆን አንችልም፡፡›› አለ።

ተሰማ የተገኝ ሃሳብ ላይ ምንም ተቃውሞ ሳያሰማ፤ ከዘውዴ ቀበል አድርጎ ‹‹የሚያሠራ ከባቢ የለም ምን ማለት ነው ? በቅድሚያ ይህን አብራራልኝ›› ሲል ለዘውዴ ጥያቄ አቀረበ።ለምሳሌ የእኔ ወንድም አመሸ ንግድ ፈቃድ አውጥቶ የሆነ ሥራ ለመሥራት ፈለገ።ነገር ግን በዚህ ንግድ ፈቃድ ይህንን መሥራት አትችልም ተብሎ ተከለከለ።በተቃራኒው ሌላ ሰው በተመሳሳይ መልኩ የንግድ ፈቃድ አውጥቶ እንደአመሸ መሥራት ፈልጎ አልተከለከለም።ስለዚህ አንዱ በብሔሩ ወይም በሃይማኖቱ እየተገፋ ሌላው እየተጠቀመ ይኖራል።ይሔ ማለት ምቹ ከባቢን አለመፍጠር ነው ሲል ምላሽ ሰጠ።

ተሰማ በበኩሉ ‹‹ለሁሉም ነገር የብሔር ታርጋ ባትሰጡ ይሻላል።ምናልባት ወንድምህ አመሸ ያላሟላው ያ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ደግሞ ያሟላው ነገር ሊኖር ይችላል።የተከለከለው በህግ ይሆናል።›› ሲል ግምቱን ገለፀ።ዘውዴ ተበሳጨ

**የኢትዮጵያ ችግር ለዘመናት የተጠራቀመ በመሆኑ በአንድ ጊዜ ልንወጣው እንደማንችል መረዳት አለብን፡፡ ዋነኛው ችግራችን ድህነት ነው። ለድህነታችን መፍትሔው ሥራ ነው፡፡ ከሠራን በረከት እናገኛለን፡፡  በረከት ሲኖር ስግብግብነት ይቀንሳል**

‹‹ሕጉ ለሁሉም እኩል ይስራ!›› አሁን በየቦታው ያለው አንዱ ላይ ተግባራዊ የሚደረገው ሕግ ሌላው ላይ ተግባራዊ አለመደረጉ ነው።መድሎ ከበዛ ሕዝብ ይቀየማል።ማንም ቢሆን ሊቋቋመው የማይችለው የሕዝብ መአበል ደግሞ አገር ያፈርሳል፤ የኔ ስጋት ይህ ነው ሲል በረዥሙ እየተነፈሰ ሃሳቡን ገለፀ፡፡

‹‹ዛሬ ላይ ቆሞ ነገን ከመሥራት ይልቅ፤ ዛሬ ላይ ሆኖ ነገን ለማፍረስ መዳዳት ለማንም አይበጅም።በየምክንያቱ ብሶት እየፈጠሩ ሰዎች እሳት ውስጥ እንዲገቡ ከመቀስቀስ ይልቅ መንግስትን ተረድቶ የጋራ ህልም ይዞ በጋራ ትግል አገር መገንባት ሲገባ ምክንያት እየፈጠሩ ነገሮችን በአግባቡ ሳይረዱ ሕዝብ ቅራኔ ውስጥ እንዲገባ ማድረግ የታሪክ ተወቃሽነትን ያስከትላል፤ ችግር ካለ ብሔር ሳይሆን የግለሰብ ስም ተነስቶ ይወቀስ አስፈላጊም ከሆነ ይከሰስ፡፡›› ሲል ተሰማ በተከታታይ ሃሳቡን ተናገረ።

ተገኝ ጉሮሮውን ለንግግር እየጠራረገ ቀጠለ  ‹‹ በየትኛውም አጋጣሚ በሰዎች መካከል አለመግባባት ሊፈጠር ይችላል።ነገር ግን አለመግባባቱ የሚፈታበት መንገድ በደንብ የታሰበበት ሊሆን ይገባል።እፈታለሁ ብሎ ይበልጥ ማወሳሰብም ያጋጥማል።ሆነ ብሎ ሲመቸው ብሔርን፤ ብሔር ካልተመቸው ደግሞ ሃይማኖትን መሸሸጊያ እያደረገ እና ተከታዮችን እንደአሸን እያፈላ የሚንጎማለል ኢትዮጵያዊ ነኝ ባይ አሜሪካንም አለ።ይህ ሥራው ሱስ ሆኖበት ኢትዮጵያን ለማፍረስ የሚፈልጉ የውጪም ሆነ የአገር ውስጥ ሃይሎችን እየደገፈ መሆኑን አይረዳም።እርሱ ሳይገባው የተናገረውን ተከታዮቹም አምነው አብረውት ይጮሃሉ፤ ዓላማው ለእርሱም ግልፅ አይደለም።ተከታዮቹም አይገባቸውም።በዚህ አጋጣሚ ችግር ለመፍታት በሚል ሰበብ ነገር ማራጋብ ይታያል›› አለ።

ዘውዴ ይህንን ሃሳብ ቢደግፍም ሊታይ ይገባል ብሎ የሚያምንበትን መናገር ጀመረ ‹‹የሰው ልጅን የወደፊት ሕይወት ለማቃናት በሚል ሰበብ መፍትሔ አፋላልጎ ሰዎችን ከድህነት ከማውጣት ይልቅ፤ በየአጋጣሚው በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ሰዎች በግፍ ሲገደሉ ማየት ያሳምማል፤ ሰው እንዲናገር፤ ሰው ተናጋሪውን እንዲደግፍ ያስገድዳል።መቀራረብ በእኩልነት በወዳጅነት በጋራ መረዳዳት እና በጎ ግንኙነትን ይበልጥ በማጠናከር ወንድማማችነትን ማሳደግ ሲገባ አጉል ነፃነትን እና ልቅነትን ባልለየ መልኩ አንዱ ሌላው ላይ ሲባልግ አንዱ ሌላውን ሲገድል ሲታይ ምንም እንኳን ግልፅ አላማ ባይኖርም ይህ ብዙሃንን ያስቆጣል።ያለ ዓላማ አንዱ ሌላውን እንዲቃወም እና እንዲደግፍ ያስገድዳል፤ ይህን ጉዳይ በቀላሉ መዝጋት ‹ኢግኖር› ማድረግ አይገባም›› አለ።

‹‹የኢትዮጵያ ችግር ለዘመናት የተጠራቀመ በመሆኑ በአንድ ጊዜ ልንወጣው እንደማንችል መረዳት አለብን።ዋነኛው ችግራችን ድህነት ነው።ለድህነታችን መፍትሔው ሥራ ነው።ከሠራን በረከት እናገኛለን። በረከት ሲኖር ስግብግብነት ይቀንሳል።ስግብግብነት ከቀነሰ ደግሞ በብሔርም ሆነ በሃይማኖት ስም ተከታይ እየፈለፈለ የሚግበሰብሰው አካል አደብ ይገዛል።ማንም በስግብግብነት ማንንም አያፈናቅልም፤ ወይም አያሳድድም›› በማለት የተናገረው ተሰማ፤ እርሱ በዋናነት ለኢትዮጵያ መፍትሔው ሥራ እና ገቢን ማሳደግ ነው።ይህ ሲሆን ችግሮች በሂደት ይቃለላሉ የሚል እምነት እንዳለው ገለፀ።

ዘውዴ ግን በበኩሉ ‹‹ስጋ ወድቆ ያለትቢያ አይነሳም›› እንደሚባለው ሁሉ አንድ ስህተት መፈፀም ችግር ሊያስከትል ስለሚችል ቀድሞ መጠንቀቅ ይገባል።ሥራ ብቻውን ሳይሆን አንዳንዶች ሃላፊነት እያለባቸው የሚፈጥሩት ስህተት ቆሻሻውን ከስጋው ለመለየት እንዳይቻል ያደርጋል።ከቆሸሸ ደግሞ ስጋም ቢሆን ላይበላ ስለሚችል ቀድሞ ማሰብ ይገባል ሲል የውስጡን ገለፀ።አክሎም ‹‹ሲሞላ ይፈሳል፤ ሲከር ይበጠሳል›› ዛሬ ላይ ሰዎች ሁሉንም ነገር እየታዘቡ ቢያልፉም ነገ ሲበዛባቸው መነሳታቸው አይቀርም።ብሔር ብሔር እያሉ እያከረሩ ያሉ ሰዎችም ሲያከሩ ተበጥሰው የሚወድቁበት አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል።ስለዚህ አክራሪ ብሔርተኞች ራሳቸውን ከማጥፋት መቆጠብ ይኖርባቸዋል ።ሲል ተሠማ በበኩሉ ብድግ ብሎ አጨበጨበ።ቀድሞም ቢሆን እኔም ያልኩት ይህንን ነበር በማለት ሲናገር ተገኝ ግራ ተጋባ።

ተሰማ ‹‹በሕዝብ መሃል ያሉ ቅራኔዎችን ለመፍታት ከማክረር ይልቅ ማላላት፤ ሰጥቶ መቀበል ወይም እኔ ብቻ ወይም ለእኔ ብቻ ከማለት ይልቅ ፤ የመደብ ትግል ንቅናቄ እያሉ ራስን ነጥሎ ተበዳይ ከማስመሰል መላቀቅ ያስፈልጋል፡፡›› አለ።አሁን ደግሞ ዘውዴ በበኩሉ ቆሞ አጨበጨበ።በመጠጥ ቤት ውስጥ ያለው ሰው ዘውዴ እና ተሰማ ተራ በተራ እየተነሱ ማጨብጨባቸው ግራ አጋብቷቸዋል።ዘውዴ እየሳቀ ተቀምጦ ንግግሩን ቀጠለ።

‹‹ማጣትን እና ጥይትን ተኝቶ ማሳለፍ ነው›› ብሎ ለጥ ያለውን ሕዝብ ቀስቅሳችሁ ማዕበል አስነስታችሁ ትልቅ ለውጥ ውስጥ ካስገባችሁን በኋላ፤ ስትፈጭር የነበረች ማንኳለል አቃታት እንደሚባለው ከባዱን ሥራ ተወጥታችሁ ትንሿ ሥራ እያስማጠች ወገባችሁን ልትይዛችሁ አይገባም አለ።ተገኝ ግራ ተጋባ ተሰማ እና ዘውዴ የተስማሙ መስለዋል።ነገር ግን ጠያቂ ማን ነው? ለጥያቄው ምላሽ መስጠት ያለበት ማን ነው? ሁለቱም ጠያቂ መሆናቸው ግር አሰኝቶታል።ተሰማ የትልቁ ስልጣን ባለቤት ነው።ዘውዴም ቢሆን አንድ ወረዳን በመምራት ላይ እንደሚገኝ ያውቃል።ነገር ግን ሁለቱም የሚናገሩት ሌላ ሰው እንዲሠራላቸው ነው።

ተገኝ ‹‹ እስኪ መናገሩን ተናገራችሁ።እናንተ በየስልጣናችሁ የተናገራችሁትን ትተገብራላችሁ? በእርግጥ በህግ ፊት ሁሉንም እኩል ታስቀምጣላችሁ? ›› ሲል ሁለቱንም ጠየቀ።ዘውዴ ፈጠን ብሎ ዋናው ችግር ያለው እነተሰማ አካባቢ ነው።እኔ በበኩሌ ከምንም በፊት አገሬን ስለማስቀድም የምሰራው በጥንቃቄ ነው።ያለ ልዩነት ሕዝቡን እያገለገልኩ ነው።በዚህ ልክ ካልተጠነቀቅኩ እና ሕዝብ ከተማረረ ችግሩ ተደምሮ አገር ላይ ይደርሳል የሚል ስጋት ስላለብኝ የምሠራው እንደምናገረው ነው።እምነቴ ይኸው ነው ሲል ምላሽ ሰጠ።

ተሰማ በበኩሉ በእርግጥም ያለልዩነት ለመሥራት ጥረት አደርጋለሁ።ነገር ግን ፍፁም ነኝ ለማለት እቸገራለሁ።የሚሠራ ሠው ይሳሳታል።ስህተቱን ብሔር ላይ መለጠፍ አይገባም።በእኔ በኩል አላሠራ ያሉኝ ሰዎች ሁሉ ጥፋቴንም ልማቴንም ብሔር ላይ በመለጠፋቸው ነው።ሰዎች የሰዎችን ብሔር ሳይሆን ግለሰቦችን ብቻ ማየት እያለባቸው በተቃራኒው መሆናቸው ቢያስከፋኝም ለአገሬ የአቅሜን እየሠራሁ ነው ሲል ተናገረ።

ተገኝ በበኩሉ ሁለታችሁም በትክክል እየሠራችሁ ከሆነ መልካም ነው።ነገር ግን ሥራችሁ ላይ በቸልታ የሚታለፉ ነገሮች የሚያስከፍሉት ዋጋ ቀላል አይደለም።ለሁሉም እኩል ነፃነትን መስጠት፤ ልቅነትን መከላከል፤ የአገርን አንድነት ማረጋገጥ የግድ ነው።ከንግግራችሁ ጀምሮ የብሔረሰቦችን ጉዳይ በማራገብ አንዱ እንደተበደለ ወይም እየተበደለ እንዳ ለ፤ አንዱ እየተጠቀመ እንዳለ ከመናገር ጀምሮ ተጨባጭ መረጃ ሳይኖራችሁ ሃሳቡን ማራመድ ከቀጠላችሁ የአገርን አንድነት ከማናጋት አይተናነስም።

የብዝበዛ ሃሳብ መኖር የለበትም።የብዝበዛ ሃሳብ ከነበረም ማክተም አለበት።በዚህ በኩል አሁንም ስህተት ካለ ችግር ይፈጠራል።ግለሰብም ሆነ ብሔር መበዝበዝ የለበትም።ግለሰብም ሆነ ብሔር በዝባዥ መሆን የለበትም።ያለበለዚያ  ቀድሞም እንደታየው የመበዝበዝ ስህተት የፈፀመ እንደወደቀ ስጋ በትቢያ ስለሚለወስ ቆሻሻ ነው ተብሎ ስለሚጣል ቀድሞ መጠንቀቅ ያሻል በማለት በብርጭቆ የተቀዳውን መጠጥ ጨርሶ ጨለጠ፡

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## የተቀዛቀዘው የፊልም ስራና የቴሌቪዥን ድራማዎች ትንሳኤ

ተገኝ ብሩ

### የፊልሙ ዘርፍ ትሩፋት

ፊልም የአንድ አገር በጎ ገፅታን ከመገንባትና ባህልን ከማስተዋወቅ ባለፈ የአገር ኢኮኖሚን በማሳደግ በኩል ያለው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ለዚህም ነው ያደጉ አገራት ለዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የሚሰሩት፡፡ አገራቱ በፊልሞቻቸው ሁለንተናዊ ለውጣቸውን፣ ስልጣኔና ባህላቸውን፣ በቴክኖሎጂ ዘርፍ የደረሱበትን ደረጃ ማሳያ መሳሪያቸው አድርገው ይጠቀሙበታል፡፡ በተጨማሪም ኢኮኖሚያቸው በዚሁ ዘርፍ በመደገፍ ትልቅ ጥቅም ተቀዳጅተዋል፡፡

ሆሊውድ የተሰኘው እውቁ የአሜሪካ የፊልም ኩባንያ ከሶስት ፊልም ሰሪ ድርጅቶች ማለትም ከዲስኒ፣ ኔትፍሊክስና ዋርነር ሚዲያ ከተሰኙ የፊልም ስራ ድርጅቶች ብቻ እኤአ በ2019 ከ41.1 ቢሊዮን ዶላር በላይ አመታዊ ገቢ መሰብሰብ ችሏል፡፡ ይህን በኢትዮጵያ ብር ዓይን ካየነው ደግሞ 2 ትሪሊዮን አካባቢ ማለት ነው፡፡ በሶስት የፊልም ኩባንያዎች ብቻ ይህን ያህል አመታዊ ገቢ ያገኘችው አሜሪካን፤ አጠቃላይ አመታዊ የፊልም ገቢዋ ምን ያህል ከፍተኛ እንደሆነ መገመት አይከብድም ፡፡

ይህ የፊልሙ ዘርፍ በትኩረት ከተሰራበት የሚያስ ገኘውን ከፍተኛ ኢኮኖያዊ ጠቀሜታ ማሳያ ተደርጎ ሊቀርብ ይችላል፡፡ ከሁሉም የኪነጥበብ ዘርፎች ታላቅና በትርፋማነቱ የሚጠቀሰው የፊልም ኢንዱስሪ፤ አገራዊ ገጽታን ከመገንባትና የማህበረሰብን አመለካከት በበጎ መልኩ ከመቅረፅ ባሻገር የሚያበረክተው ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ቀላል አይደለም፡፡ ይህን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው ዘርፍ በአገራችን ያለበት አሁናዊ ሁኔታ በወፍ በረር ለመዳሰስ አስበን ብዕራችንን አነሳን፡፡

### የፊልሞቻችን አሁናዊ ሁኔታ

የብዙ ጥበባት መፍለቂያና የጠቢባን አገር የሆነችው ኢትዮጵያ አገራዊ ገፅታዋ መገንባት፣ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን ማሳደግና የማህበረሰቡን አስተሳሰብ ጥበባዊ በሆነ መልኩ መቅረፅ የሚያስችለውን የፊልም ጥበብን የመጠቀም ሰፊ ዕድል አላት፡፡ ነገር ግን ዘርፉ የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ በመሆኑ እድገት ማሳየትና የሚጠበቅበትን አስተዋፅዖ ማበርከት አልቻለም፤ በዚህም ምክንያት በተደጋጋሚ ሲወቀስ ቆይቷል፡፡

ፊልም አገርን መገንባት የሚችል ታላቅ ጥበብ መሆኑን የሚናገረው የፊልም ባለሙያው ደራሲና አዘጋጅ ግዛቸው ገብሬ ነው፡፡ ይህን የተረዱ አገራት ልዩ ትኩረት ሰጥተው በፊልማቸው አለምን መድረስ እንደቻሉ ያስረዳል፡፡ ፊልም አገራዊ ኢኮኖሚን ከማሳደግ ባለፈ ኢትዮጵያ ያላትን ውብ ተፈጥሯዊ ገፅታ፣ ባህልና ልዩ ልዩ እሴቶቿን ለሌላው ዓለም ለማሳወቅ ልትጠቀምበት እንደምትችልም ያነሳል፡፡

በእርግጥ ይህ ኢንዱስትሪ በኢትዮጵያ ደረጃ እድገቱ ጅማሮው ላይ እንደመሆኑ፤ በአገር ደረጃ ከፊልሙ ዘርፍ የሚገኘው አጠቃላይ አገራዊ ገቢ አመርቂ ነው ሊባል አይችልም፡፡ ይህንን ለማወቅ ብዙ ጥናቶች ማድርግ ቢጠይቅም፤ በዚህ ዘርፍ የተሰማሩ አያሌ የፊልም ስራ ድርጅቶችና ባለሙያዎች በመኖራቸው የተፈጠረው የስራ ዕድል ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው ባለፈ በግልፅ መመልከት ያስችላል፡፡

ደራሲ፣ ዳይሬክተርና ፕሮዲዩሰር ግዛቸው ገብሬ በድርሰት ከ40 በላይ ፊልሞች በዝግጅትና በፕሮዲዩሰርነት ደግሞ 10 ፊልሞች በማዘጋጀት ለህዝብ አቅርቧል፡፡ ከጥቂት አመታት በፊት ጥሩ መነቃቃት መፍጠር ችሎ የነበረው የፊልሙ ኢንዱስትሪ፤ ዛሬ ላይ በብዙ ችግሮች ወደኋላ መንተቱን ባለሙያው ይናገራል፡፡

አሁን ላይ የፊልም ተመልካች ከሲኒማ የጠፋበትና የፊልም ስራው እጅግ የተቀዛቀዘ መሆኑን የሚያስረዳው ግዛቸው፤ በዚህ ከቀጠለ ዘርፉ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱ አያጠያይቅም ብሏል፡፡ በተለያዩ ምክያቶች በፊት ሲኒማ ይመለከት የነበረው ተመልካች አሁን ላይ በኢንተርኔት ፊልሞችን ማየት የጀመረበት ወቅት መሆኑንም ያስረዳል፡ ፡ ይህ መሆኑ ደግሞ ጥሩ ፊልሞች ተሰርተው ለተመልካች እንዳይቀርቡ አድርጓል፡፡

ለኢንተርኔት ተብለው የሚሰሩ ስራዎች የጥራት ደረጃቸው አነስተኛ መሆናቸውን የሚናገረው ግዛቸው፤ ይህ ሙያውን በእጅጉ የሚጎዳው መሆኑን ያነሳል፡፡ ለፊልም ገባያው መቀዛቀዝ ዋነኛ ምክንያት ተደርገው የሚነሱ ሶስት ዋና ዋና የፊልሙ ዘርፍ አገራዊ ችግሮች አሉ፡፡

እንደ ዋነኛ ችግር አድርገው ባለሙያዎች የሚጠቅሷቸው




ጉዳዮች ቢኖሩም በዋናነት የሚነሱት ግን የፊልም ስራ ከጥራት አንፃር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መሄድ፣ ተመልካቹ ከሲኒማ ቤት ይልቅ ወደ ኢንተርኔት ፊልም ማምራቱና በፊልም ስራው ላይ ያሉ የአሰራር ግድፈቶች ይጠቅሳሉ፡፡

ባለሙያው ግዛቸው ቀደም ባሉት ዓመታት ይሰሩ የነበሩት ጥሩ ፊልሞች መሰራት እና ወደ ሲኒማው መቅረብ የቀነሱበት ምክንያትም የተመልካቾች ከሲኒማው መራቅ መሆኑን ያነሳል፡፡ በዚህም ምክንያት ከጥቂት አመታት በፊት እጅግ አመርቂ የነበረው የፊልም ስራ ዛሬ ላይ እጅግ መዳከሙን በማስረጃዎች ይጠቅሳል፡፡

አሁን ላይ አዳዲስ ፊልሞች ተሰርተው ለሲኒማ ቤቶች ለእይታ ቢቀርቡም ተመልካች እስካሁን እንዳልተመለሰ የሚገልፀው የፊልም ፕሮዲዩሰር አማን ደረጀ፤ ዘርፉ ትኩረት እንደሚያሻው ያስረዳል፡፡ ለፊልም ዘርፍ ባለሙያዎችና ድርጅቶች ከሁለት አመት በፊት የተከሰተው የኮሮና ወረርሽኝ ትልቅ ተፅዕኖ ፈጥሮባቸው ማለፉን የሚያስታውሰው አማን፤ ይህ ተፅዕኖ ዛሬም እንዳልተቀረፈ ያስረዳል፡፡

በየሲኒማ ቤቶች ወይም ፊልም ማሳያዎች በር ላይ ተሰልፎና በርከት ብሎ ይታይ የነበረው ተመልካች ዛሬ ላይ ከሲኒማ ቤት ደጃፍ ጠፍቷል ፡፡ ፊልም ማሳያ ቤቶቹ ለሌላ አገልግሎት መዋላቸውም የዘርፉን መቀዛቀዝ ማሳያ ነው፡፡ ከኮሮና ወረርሽኝ በኋላ መልሰው ወደ ስራ የገቡት ሲኒማ ቤቶች ቀድሞ የነበረውን ያህል ተመልካች አላገኙም፡፡

ቀድሞ ከፊልም ያገኙት የነበረ ገቢ ቀርቶባቸዋል፡፡ ሰራተኞቻቸውንም ለመቀነስና ከስራ ለማሰናበት ተገደዋል፡፡ ማቲያስ አለነህ አዲስ አበባ ቦሌ አካባቢ በሚገኝ አንድ ሲኒማ ቤት በፊልም ገምጋሚነትና በሲኒማ ቤቱ አስተባባሪነት ሲሰራ ቆይቷል፡፡ የኮሮና ወረርሽኝ በተከሰተ ጊዜ ሲኒማ ቤቱ መዘጋቱንና ከዓመት በኋላ ቢከፈትም በፊት የነበሩት የፊልም ተመልካቾች ወደ ሲኒማው መመለስ እዳልተቻለ ያስረዳል፡፡

በዚህም የሲኒማ ቤቱ ገቢ መቀነሱንና ሰራተኞችም እንደተቀነሱ ያነሳል፡፡ እንደ ማትያስ የመቀዛቀዙ መነሻ የኮሮና ወረርሽኝ ይሁን እንጂ፤ ከወረርሽኙ በፊትም የፊልም ተመልካች ቁጥር እየቀነሰ እንደነበር ያስታውሳል፡፡ ፊልሞች ከይዘትና ከታሪክ አንፃር ተመሳሳይ ሆነው በተደጋጋሚ መቅረባቸው ለተመልካቹ መራቅ ምክንያት ሊሆን ይችላል የሚል ሀሳብም አለው፡፡

ለሲኒማ ቤቶች ተመልካች ማጣትና ለፊልሙ ገበያ መቀዛቀዝ ምክንያት ተደርጎ በማቲያስ በቀረበው ሀሳብ ሌላኛው የዘርፉ ባለሙያው ግዛቸው ሙሉ በሙሉ ባያምንበትም እንደ አንድ ምክንያት ግን ሊወሰድ እንደሚችል ይናገራል፡፡ ይህንንም ውድቅ የሚያደርግ ማሳያም አለው። ፊልሞች በጥሩ ታሪክና ጥሩ በሆነ ሙያዊ ክህሎት ተሰርተው ለተመልካች ቀርበው የማይታዩበትን አጋጣሚም አያይዞ ያነሳል፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ጥሩ ስራ መሆኑ በተደጋጋሚ የተነገረለትና በአገራችን ከተሰሩ ጥሩ ፊልሞች ተርታ የሚመደበው "ጤዛ" የተሰኘው ፊልም በአገር ውስጥ የነበረው እይታ የፊልሙን ታላቅነት የማይመጥን እንደነበር ያስረዳል፡፡

ፕሮዲዩሰሩ አማን፣ በፊልም ገበያው ላይ መቀዛቀዝ መፈጠሩ በራሱ ጥሩ ፊልም ተሰርቶ ወደእይታ እንዳይቀርብ አድርጓል የሚል ራሱን መከራከሪያ ነጥብ ያስቀምጣል። ይህም ፊልም ሰሪው በቂ በጀት መድቦና ጥሩ ባለሙያዎችን አሳትፎ ከሰራ በኋላ ለፊልሙ ያወጣውን ወጪ የመመለስ ስጋት እንዲጋረጥበት በማድረጉ ደረጃቸውን የጠበቁ ፊልሞች እንዳይሰሩ መሰናክል መሆኑን ያስረዳል፡፡

በኢትዮጵያ በመዝናኛው ዘርፍ እንደ አጠቃላይ ሰፊ ክፍተት ይስተዋላል። እንደ አገር ለፊልም ስራ መነሻ የሚሆን ቱባ ባህልና እሴት ሞልቷል። ኢትዮጵያ ምቹ የሆነ ውብ ተፈጥሯዊ ገፅታና የፊልም ኢንደስትሪው ሰፊ ገበያ እያለው ከአገር አልፈው በአለማቀፍ ደረጃ ተፅዕኖ ፈጣሪ ፊልሞች በብዛት መሰራት አለመቻላቸው ሁሉንም ያስቆጫል፡፡

በእርግጥ ከዘርፉ ካለው ትልቅ ተጽእኖ የመፍጠር አቅም አንፃር እስካሁን የተሰሩ ፊልሞች የፈጠሩትን በጎ ተፅዖኖ ማየት አለመቻል ፊልም በኢትዮጵያ ገና ያልተጀመረ ያህል እንዲቆጠር ቢያደርግ አይገርምም፡፡ ለፊልም ባለሙያውና ለዘርፉ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ልዩ ትኩረት መስጠት ቢቻል ግን በእርግጥም የዘርፉ ብዙ ጠቀሜታ ማረጋገጥ በተቻለ ነበር።

### የዘርፉ አዲስ ክስተቶች

የሲኒማው ዘርፍ መቀዛቀዝ በስፋት በሚወራበት በዚህ ወቅት ለየት ባለ የአቀራረብ ስልትና አዲስ በሆነ መንገድ ብቅ ማለት የጀመሩ የቴሌቪዥን ድራማዎች ለፊልሙ ዓለም ተስፋ የፈነጠቁ ይመስላሉ፡፡ ለዚህም በተመልካቹና በባለሙያዎች የተወደዱና አሁን ላይ ለእይታ እየቀረቡ የሚገኙ ድራማዎችን ለአብነት ማንሳት ይቻላል፡ ፡ በባለሙያዎች ጥምረት እየተሰሩ የሚገኙት እንደ እረኛዬ፣ የእግር እሳት፣ አደይ እና መሰል ድራማዎች በማሳያነት ይጠቀሳሉ። ከእነዚህ የቴሌቬዥን ድራማዎች መረዳት የሚቻለው፤ ባለሙያው ሙያውን አክብሮና ተመልካች በሚመጥን መልኩ ሃላፊነቱን ከተወጣ የፊልሙ ተመልካች አሁንም ፊቱን እንዳላዞረ ነው።

ባለሙያው ግዛቸውም እነዚህ ድራማዎች ለዘርፉ ጥሩ መነቃቃት እንደፈጠሩ ያምናል። በጥንቃቄ የተሰራ ስራ በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት እንደሚችልም ማሳያ መሆናቸውን ያነሳል፡፡ የቴሌቪዥን ድራማዎቹ ከይዘትና ከአሰራር አንፃር አዲስ ነገር ይዘው በመቅረባቸው ተወዳጅ ሆነው በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት እንዳገኙም ይናገራል።

ከተወደዱት የቴሌቪዥን ድራማዎች ውስጥ ዘንድሮ በተካሄዱ የፊልም ሽልማቶች በርካታ ክብሮችኝ በመውሰድ የአመቱ ምርጥ የቴሌቪዥን ድራማ የተሰኘው ‹‹እረኛዬ›› ድራማ በማሳያነት ይጠቅሳል፡፡ ባለሙያዎቹም በህብረት ተቀናጅተው መስራታቸው፣ በፊት ከተለመደው የከተማ ታሪክ ወጣ ብለው ብዙ ሰው ወደሚመለከተው የገጠሩን ህይወት መዳሰሳቸውና በአቀራረብም አዲስ መሆኑ ለመወደድ እንዳበቃው ግዛቸው ይናገራል፡፡

ከዚህም ጋር ተያይዞ የፊልም ስራ ላይ የተሳተፉ ባለሙያዎች በጥምረት መስራታቸው የተሻለ ስራ ይዞ ለመቅረብ ትልቅ አስተዋፅዖ ማበርከቱን ያስረዳል፡፡ የፊልም ስራ በባህሪው የህብረት ስራ በመሆኑ በሙያው የሚሳተፉ ባለሙያዎች በመግባባትና የተሻለ የፈጠራ ሀሳብ በማቅረብ ውጤታማ መሆን የሚቻልበት መስከ መሆኑን የሚናገረው ግዛቸው፤ ድራማዎቹ የተሻሉ የሆኑበትም አንዱ ምክንያት ከዚህ የተለየ እንደማይሆን ያስቀምጣል።

የፊልም ፕሮዲዩሰሩ አማን በበኩሉ፣ የፊልም ስራ ዘርፍ ተስፋ ወደማስቆረጡ ሲቃረብ ብቅ ብለው ትልቅ ተስፋ የጫሩት እነዚህ የቴሌቬዥን ድራማዎች መሆናቸውን ይናገራል። ስራው በቂ ትኩረት ተሰጥቶበት ከተሰራም ተወዳጅ መሆን እንደሚችል የቴሌቪዥን ድራማዎቹ ማሳያ መሆናቸውን ይጠቅሳል፡፡

"የፊልም ስራ በራሱ ነፃነት ይፈልጋል፤ ነፃነቱም በሀሳብ በገንዘብና በሙያ ሊገለፅ ይችላል" የሚለው ግዛቸው፣ ለፊልም ስራ የሚሆን በቂ በጀት፣ ደራሲው በሀሳብ በኩል ሳይገደብ በነፃነት ታሪክ የሚነግርበት ምቹ ሁኔታ ከተፈጠረ ይህም ብቁ በሆነ ሙያዊ ስራ ፊልም ላይ መተግባር ከቻለ ጥራቱን የጠበቀ ፊልም መስራትና ተመልካቹን ወደ ሲኒማ መመለስ ይቻላል የሚል እምነትም አለው።

በአጠቃላይ ይህ ትልቅ ዘርፍ በሚመለከተው ሁሉ ትኩረት ከተሰጠው ለአገር ዘርፈ ብዙ ፋይዳ ሊያበረክት የሚችልበት አቅም አለው። የፊልሙ ኢንደስትሪ ያሉበትን ችግሮች በመቅረፍም ከዘርፉ የሚጠበቀውን በጎ አስተዋፅዖ መመልከት እንደሚቻል ባለሙያዎቹ የሃሳብ ልዩነት የላቸውም።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## አካል ጉዳተኞችና ያልተፈቱት ችግሮች


ሰሳማዊት ውቤ

‹‹ረጅም ርቀት መጓዝ፤በመኖርያ ቤቴ ውስጥ መንቀሳቀስ አልችልም። ደረጃ መውጣትም ይቸግረኛል። በአጠቃላይ እጄን ለመዘርጋት ወይም በጉልበቴ ለመንበርከክ ካለመቻሌም ባሻገር ጣቶቼን ተጠቅሜ የሆነ ነገር እጅግ ያዳግተኛል። ነገር ግን እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ ራሴን ችዬ ባልንቀሳቀስም በመጠኑም ቢሆን ሰውነቴ ይታዘዝልኝ እንደነበር አስታውሳለሁ።

ብዙ ጊዜ ከቤት አልወጣም።ብወጣም በሸክም ነው። ዕድሜዬ እየጨመረ ሲመጣ በሸክምም ቢሆን መውጣቴ ቀረ። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ትምህርት ቤትም መግባት አልቻልኩም ›› በማለት ሃሳቧን ያጋራችን ወጣት የውብ ዳር ታሪኩ ናት፡፡

ወጣቷ ወላጆቿ ትምህርት ቤት ያላስገቧት በአካል ጉዳተኝነት ምክንያት መሆኑን ትናገራለች። እቤት በመዋሏ በመጠኑም ቢሆን ይታዘዝላት የነበረው አካሏ መታዘዝ እየተሳነው መምጣቱን ትጠቅሳለች።አንዳንድ ትምህርት ቤቶች እንደ እኔ ዓይነት አካል ጉዳት ያለባቸውን ተማሪዎች ለማስተማር የሚያስችል ምቹ ቦታና ሁኔታም እንዳልነበራቸው ወላጆቼ ነግረውኛል ብላናለችም።

በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 41 ንዑስ ቁጥር 5 መንግስት አቅም በፈቀደው መጠን ለአእምሮና ለአካል ጉዳተኞች እንክብካቤ ያደርጋል የሚል ሕግ መደንገጉን ወጣት የውብዳር ታስታውሳለች። በዚሁ ሕገ መንግስት አንቀጽ 90 ንዑስ አንቀጽ 1 ያለ ምንም ዓይነት ልዩነት ሁሉም ኢትዮጵያዊ የአገሪቱ የኢኮኖሚ አቅም በፈቀደው መጠን የትምህርት፤ የጤና እና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች ተጠቃሚ መሆን እንደሚችልም መስፈሩን ትገልፃለች። ሆኖም ትምህርትን በተመለከተ እሷን ጨምሮ በርካታ እንደ እሷ የእንቅስቃሴ ችግር ያለባቸውና ሌሎች አካል ጉዳተኞች ለረጅም ዓመታት የትምህርት ዕድል ከማግኘት ተገልለው እንደቆዩ ታወሳለች።20 ዓመት እስኪሞላት ድረስ እሷ የትምህርት ዕድል ሳታገኝ መቆየቷንም እንደ ማሳያ ትገልፃለች።



የአካል ጉዳተኞችን እኩል ተሳትፎና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ መንግስትም ሆነ ሌሎች አካላት እርምጃ መውሰድ አለባቸው

እኛ አካል ጉዳተኞች ተጠቃሚና ተሳታፊ የመሆን መብታችን በሕገ መንግስቱም ሆነ በተለያዩ ሕጎች ቢሰፍርም ከወረቀት በዘለለ መሬት ወርዶ ሳይተገበርልን ለዘመናት ቆይተናል ያሉን ደግሞ አቶ እስጢፋኖስ ይህደጎ ናቸው። በዚህም ምክንያት የአካል ጉዳተኞች በከፋ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ስነልቦናዊ ጫና ውስጥ ለመኖር ተገድደው ይገኛሉም ይላሉ።

መሳለሚያ አካባቢ በሚገኘው ወረዳ 4 ነዋሪ መሆናቸውን እና እግራቸው በተፈጥሮ ምክንያት ከእንቅስቃሴ ውጪ እንደሆነ የሚናገሩት አቶ እስጢፋኖስ እንዲህ ዓይነቱን የጉዳት ሁኔታ ጨምሮ ማህበራዊና ባህላዊ ተፅዕኖ፤ ድህነትና ሌሎች ተደራራቢ ችግሮች የአካል ጉዳተኞች በግልም ሆነ ከሌሎች ሰዎች ጋር ሆነው ችሎታቸውን በመጠቀም ለህብረተሰቡ ልማት አስተዋፅኦ የሚያበረክቱበትን እንዲሁም ራሳቸውን የሚያግዙበትን ዕድል በመንፈግ ተመጽዋችና ሕይወታቸውን በፈተና የተሞላ እንዲሆን እንዳደረገ ይገልጻሉ፡፡

እሳቸው አካል ጉዳተኛ በመሆናቸው አይችልም በሚል የተዛባ አመለካከት ቁጭ ብሎ እንዲለምኑ መዳረጋቸውን ያወሳሉ። እስከ ተወሰነ ጊዜ የተዛባ አመለካከቱ ተላምዷቸው የኔ ቦታ ልመና ነው ብለው ራሳቸውን እስከ ማሳመን የደረሱበት ሁኔታ የነበረ መሆኑንም ያስታውሳሉ ።አሁን በአነስተኛና ዘርፍም ቢሆን የራሳቸውን ሥራ ከመፍጠር ባሻገር ለሌሎችም እየጠቀሙ መገኘታቸውን ሲያዩ ለራሳቸው የነበራቸው ዕምነትና ግምት የተሳሳተ እንደሆነ መረዳታቸውንም ነግረውናል።

አቶ እስጢፋኖስ ይቀጥላሉ፡፡ እኔ ሁለቱም ጀሮዎቼ አይሰሙም።በምኖርበት ማህበረሰብ ውስጥ የተዛባ አመለካከት ነበር። ከእንቅስቃሲያቸው እንደምገነዘበው በአካባቢያችን ያሉ ሰዎች ከአካባቢ ጽዳት ጀምሮ በርካታ በጋራ የሚያከናውኗቸው ሥራዎች አሉ። ሆኖም ከምን አንፃር ተረድተውና አይተውኝ እንደሆነ ባላውቅም በየትኛውም ተግባር አያሳትፉኝም። ግን ጆሮዬ ባይሰማም እጅግሬ ላይ የእንቅስቃሴ ችግር ስለሌለብኝ መሥራት እችላለሁ። ግን እስካሁን ከነዚህ ሰዎች ጋር የምግባባው በእጅ እንቅስቃሴ ነው።ሆኖም በዚህም መግባባት የቻልኩት በልምድ ነው።

አቶ ቱሉ ነገራ ዓይናቸውም ላይ ችግር አለባቸው። በአብዛኛው አጥርተው አያዩም።አንድን ነገር ማየትና መለየት የሚችሉት በጣም ቀርበውና ተጠግተው ነው። እንዲህም ሆኖ አካታችነት ትኩረት ተሰጥቶ ባለመሰራቱ እሳቸውን ጨምሮ በርካታ አካል ጉዳተኞች በአካባቢያቸው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች አሁንም ድረስ ሙሉ በሙሉ ተሳታፊና ተጠቃሚ መሆን አልቻሉም። ግን ሙሉ ለሙሉ መሬት አይውረድና አይተግበር እንጂ አካታችነት በሁሉም መስክ እንዲተገበር የሚገልፅ ሕግ መኖሩን ያውቃሉ።

በኢትዮጵያ ውስጥ ከ20 ሚሊዮን በላይ የአካል ጉዳተኞች እንደሚገኙ ከሴቶችና ማህበራዊ ሚኒስትር ኮሚኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ያገኘነው መረጃ ያመለክታል። ሆኖም የብዛታቸውን ያህል የተለያዩ አገልግሎቶች ተደራሽ ፤ እንዲሁም በሕብረተሰቡ ውስጥ በተገቢውና በሚፈለገው መጠን ተሳታፊና ተጠቃሚ ሆነዋል ማለት የማያስችሉ የተለያዩ ችግሮች አሉባቸው። አንዱና ዋናው በሕብረተሰብ ውስጥ ያለው አመለካከት እንዲሁም በተጠቃሚነታቸው ዙርያ ያሉ ሕጎች በትክክል መሬት ወርደው እየተሰራባቸው አለመሆኑ ከብዙዎቹ ተግዳራቶች ጥቂቶቹ መሆናቸውን ከዳይሬክቶሬቱ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

እንደ መረጃው በአካል ጉዳተኞች ላይ ትልቁን ችግር የሚፈጥሩት የተዛቡ አመለካከቶች፣ የተሳሳቱ እምነቶች እና መድልዎ ናቸው።በኢትዮጵያ ውስጥ አካልጉዳተኝነት እንደ አሳፋሪና አሳዛኝ ክስተት ተደርጐ ስለሚወሰድ መገለልን ወይም ከልክ ያለፈ ከለላ ማድረግን ያስከትላል። አንዳንድ ጊዜም አካል ጉዳተኝነት እንደ እርግማንይቆጠራል፡፡

መድልዎን በመፍራት የአካል ጉዳተኛው ቤተሰቦች ግለሰቡን በቤት ውስጥ ተደብቆ እንዲቀመጥ ሊያደርጉ ይችላሉ።በተለይ በትምህርት፤በጤና፤በውሃ በጥቅሉ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ዙርያ ባለው አካታችነት ላይ በመመሥረት ለውጥ ማምጣትና አካል ጉዳተኛውን የሕብረተሰብ ክፍል እኩል ተጠቃሚና ተሳታፊ ማድረግ ይገባል በማለት ጽሑፋችንን ደመደምን። ፈጣሪ የሳምንት ሰው ይበለን!

# ዓለም አቀፍ

## በቻይና እና በታይዋን መካከል እየተባባሰ ያለው ፍጥጫ

በቻይና እና ታይዋን መካከል ያለው ፍጥጫ ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሰ ይገኛል።ባለፈው የፈረንጆች ዓመት ቻይና በርካታ የጦር አውሮፕላኖችን ወደ ታይዋን የአየር ክልል ማስገቧቷ የሚታወስ ነው።በዚህ ሁሉ ፍጥጫ ውስጥ የሚነሳው ደግሞ የታይዋን ከቻይና ጋር የመዋሃድ ጥያቄ ነው።

የቻይናው ፕሬዚዳንት ሺ ዢን ፒንግ በአንድ ወቅት ታይዋን ከቻይና ጋር የመዋሀዷ ነገር “መሳካት ያለበት ነው” ብለው ነበር። ፕሬዝደንቱ በንግግራቸው ታይዋንን መልሶ የቻይና አካል ለማድረግ ኃይል መጠቀም አማራጭ ሊሆን እንደሚችል ጠቁመዋል።ቻይና በራሷ የምትተዳደረው ታይዋንን እንደ ተገንጣይ ግዛቷ የምትቆጥራት ሲሆን የጊዜ ጉዳይ እንጂ ተመልሳ የቻይና አካል እንደምትሆን ቤይጂንግ ታምናለች።

ታይዋን በሌላ በኩል እራሷን እንደ ሉዓላዊ አገር ነው የምትቆጥረው። የራሷ የሆነ ሕገ-መንግሥት ያላት ሲሆን በዴሞክራሲያዊ መንገድ የተመረጠ መንግሥትም አላት።ታይዋን ከደቡብ ምሥራቅ ቻይና ባሕረ ሰላጤ 100 ማይሎች ርቀት ላይ የምትገኝ ደሴት ነች።

በአካባቢው ከሚገኙና አሜሪካ ጥብቅ ወዳጆች መካከል የመጀመሪያው ተርታ ላይ የምትሰለፈው ታይዋን ከፍተኛ የሆነ አካባቢያዊ ጠቀሜታ እንዳላት ይታመናል።ቻይና ታይዋንን የምትቆጣጠር ከሆነ በምዕራባዊ ፓሲፊክ አካባቢ ትልቅ ውጥረት ሊነግስ እንደሚችል የሚገመት ሲሆን አሜሪካም ብትሆን በጉዋም እና ሃዋይ ያሏት ትልልቅ ወታደራዊ ሰፈሮች ላይ ስጋት ሊፈጥር ይችላል።

ቻይና እና ታይዋን የተለያዩት በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ሲሆን በጊዜው ቻይና እራሷ በአንድነት መንግሥት እና በኮሚዩኒስት ፓርቲ መካከል ለሁለት ተከፍላ ጦርነት ላይ ነበረች።በአውሮፓውያኑ 1949 ኮሚዩኒስት ፓርቲ ድል ሲቀዳጅ የወቅቱ መሪ ማኦ ዜዱንግ ቤይጂንግን መቆጣጠር ቻሉ።ይህ በእንዲህ እንዳለ ሽንፈትን ያስተናገዱት የብሔራዊ ፓርቲው ደጋፊዎችና መሪዎች ወደ ታይዋን ሸሽተው ገቡ። የፓርቲው መሪ ቻንግ ካይ ሼክም ቢሆኑ ታይዋንን መደበቂያቸው አደረጓት።


ትንሽ ቆይተውም ኩሚ ታንግ የተባለውን ፓርቲ እዚያው ታይዋን ውስጥ መሰረቱ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ታዲያ ይህ ፓርቲ ታይዋን ውስጥ ወሳኝ የሚባል የፖለቲካ ክንፍ ሆኖ ቆይቷል።በአሁኑ ጊዜ ቫቲካንን ሳይጨምር 13 አገራት ታይዋንን እንደ ሉዓላዊ አገር የሚቆጥሯት ሲሆን፣ የቻይና ዲፕሎማቶችም ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ አገራት ይህንን እንዳይቀበሉ ይወተውታሉ። ካልሆነ ደግሞ ሀሳቡን ሳይደግፉም ሳይነቅፉም እንዲቆዩ ሐሳብ ያቀርባሉ።

የታይዋኑ የመከላከያ ሚኒስትር አሁን ላይ ከቻይና ጋር የገቡበት ፍጥጫ ከ40 ዓመታት ወዲህ የጋለ ደረጃ ላይ ደርሷል።ቻይና ከታይዋን ጋር ዳግም የመዋሃድ ውጥኗን በተቻለ መጠን ወታደራዊ ባልሆነ መንገድ ለማሳካትና በተለይ ደግሞ ኢኮኖሚያዊ ትስስርን በመፍጠር ነገሮችን ለማሳለጥ ስትሞክር ቆይታለች። ነገር ግን ቻይና ወታደራዊ አማራጭ ለመከተል የምትወስን ከሆነ በምንም አይነት መንገድ ታይዋን እራሷን መከላከል አትችልም።

ቻይና ከአሜሪካ በመቀጠል ትልቁን ወታደራዊ በጀት የምትበጅት አገር ስትሆን በተለያዩ ወታደራዊ መስኮች አስገራሚ የሚባሉ ቴክኖሎጂዎችን ትጠቀማለች።ከባሕር ኃይል እስከ ሚሳኤል እንዲሁም ከአየር ኃይል እስከ ሳይበር ጥቃቶች ድረስ በሁሉም ዘርፎች አስፈላጊውን ውጤታማ ሥራዎችን መከወን ችላለች።

አንዳንድ የዘርፉ ባለሙያዎች እንደሚሉት ከሆነ ቻይና ታይዋንን ከወረረች ታይዋን ማድረግ የምትችለው ምናልባት የቻይና ባሕር ኃይልን ለጥቂት ጊዜያት መግታት አልያም የሽምቅ ውጊያ እያካሄደች ሌሎች አገራት እስኪረዷት መጠበቅ ብቻ ነው።ይህን እርዳታ ደግሞ ከአሜሪካ ውጪ ከየትም እንደማይመጣ ይታመናል። ነገር ግን አሜሪካ አሁንም በጉዳዩ ላይ ግልጽ የሆነ አቋም የላትም።

በሌላ አገላለጽ አሜሪካ ታይዋን ላይ ጥቃት የሚፈጸም ከሆነ በፍጥነት ታይዋንን ለማዳን ወደ ጦርነት ትገባለች ወይስ አትገባም የሚለው በውል አይታወቅም።በዲፕሎማሲው ረገድ አሜሪካ ‘አንድ ቻይና’ የሚለውን ፖሊሲ የምትከተል




ሲሆን፣ ይፋዊ የሆነ ግንኙነት ያላትም ከቤይጂንግ ጋር ብቻ ነው። ነገር ግን አሜሪካ ለታይዋን የተለያዩ አይነት የጦር መሳሪያዎችን ትሸጣለች።

በአውሮፓውያኑ 2021 ቻይና ታይዋን የግሌ ነው በምትለው የአየር ክልል ውስጥ ተዋጊ ጀቶችን መላኳ የሚታወስ ነው። ታይዋንም የቻይና ድርጊት ሉዓላዊነቴን የሚጥስና ደኅንነቴን አደጋ ላይ የሚጥል ነው በማለት ከሳለች። ታይዋን በኤሌክትሮኒክስ ምርት ላይ ትልቅ ሚና ያላት አገር ነች።

ታይዋን ሰሚኮንዳክተር ማኒፋክቸሪን ካምፓኒ (ቲኤስኤምሲ) የተባለው ኩባንያ ከፍተኛ መጠን ያለው ‘ቺፕስ’ በማምረት የዓለማችንን የኤልክትሮኒክስ ገበያ ግማሹን ይቆጣጠራል።ይህ ድርጅት በ2021 በተደረገ ሪፖርት መሠረት አጠቃላይ ዋጋው 100 ቢሊየን ዶላር ይደርሳል። ቻይና ታይዋንን የምትቆጣጠር ከሆነ ደግሞ ዓለም በእጅጉ የምትፈልጋቸውን ነገሮች በዋነኛነት የሚመረትበትን ቦታ በእጇ አስገባች ማለት ነው።

በሌላ በኩል ምንም እንኳን ቻይና እና ታይዋን ከባድ ፍጥጫ ውስጥ ቢሆኑም በርካታ ታይዋናውያን ጉዳዩ ብዙም አያሳስባቸውም ይላል በቅርቡ የተሰራ አንድ ጥናት።ከወራት በፊት አንድ ድርጅት ታይዋናውያን ከቻይና ጋር ጦርነት ቢገጥሙ ምን እንደሚሰማቸው ጠይቋቸው ነበር። ታዲያ 64 በመቶ የሚሆኑት ታይዋናውያን ጦርነት ይነሳል ብለው እምብዛም እንደማያስቡ ነው የተናገሩት። እንደውም ጦርነት ይኖራል ብለው አያምኑም።ነገር ግን አብዛኛው ሕዝብ እራሱን ታይዋናዊ አድርጎ የሚቆጥር ሲሆን ከቻይና በብዙ ነገሮች የተለዩ እንደሆነ እንደሚያምኑ የቢቢሲ ዘገባ ያመለክታል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ሐሙስ ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

## የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴው እጩዎችን ይፋ አደረገ

**ቦጋለ አበበ**

በየአራት አመቱ ውዝግብ የማይጠፋው የኢትዮጵያ እግርኳስ ፌዴሬሽን የፕሬዝዳንትና የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ምርጫ የፊታችን ነሐሴ 21 እና 22 ጎንደር ላይ ይካሄዳል።

ባለፈው ግንቦት 7 /2014 ፌዴሬሽኑ ባካሄደው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ባጸደቀው መመሪያ ደንብ መሠረት የተመረጠው ምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስራውን ቀደም ብሎ የጀመረ ሲሆን ከትናንት በስቲያ አመሻሽም እጩዎችን ይፋ አድርጓል። በዚህም መሰረት ለፕሬዘዳንታዊ ምርጫው ሶስት እጩዎች የሚወዳደሩ ሲሆን ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ምርጫ ሃያ ስድስት እጩዎች ተወዳዳሪ ሆነው ቀርበዋል።

በፕሬዘዳንታዊ ምርጫው አሁን ፌዴሬሽኑን እየመሩ የሚገኙት አቶ ኢሳያስ ጅራ ለተጨማሪ አራት አመታት ለማገልገል ከኦሮሚያ ክልል ተወክለው የሚወዳደሩ እጩ ሆነዋል። ሁለተኛው እጩ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የቀድሞ ዳይሬክተር አቶ መላኩ ፈንታ ቻይ ከአማራ ክልል እጩ ሆነው የቀረቡ ሲሆን፣ የድሬዳዋው ተወካይ አቶ ቶኩቻ አለማየሁ ከተማ ሶስተኛው እጩ ሆነው ቀርበዋል።




ምርጫውን ሰላማዊና ህጋዊ የማድረግ ስልጣኑ በጠቅላላ ጉባኤ የተሰጣቸው የአስመራጭ ኮሚቴው ባለፈው ወር ምርጫውን በተመለከተ መግለጫ መስጠቱ ይታወቃል። የህግ ጠበቃውና የምርጫ አስፈጻሚው ኮሚቴው ሰብሳቢ አቶ ሀይሉ ሞላ ሲሆኑ፣ በኮሚቴው የአዲስ አበባ ከተማን እግር ኳስ በምክትል አመራርነት ለበርካታ አመታት ያገለገሉት አቶ በለጠ ዘውዴ፣ የመድን እግርኳስ ክለብ ከፍተኛ አመራርና የኢትዮጵያ እግርኳስ ፌዴሬሽን የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ መንግስቱ መሃሩ፣ የኢትዮ ኤሌክትሪክ የስፖርት ክለብን ለአመታት የመሩና በሙያቸው የተቋሙ ከፍተኛ አመራር የሆኑት አቶ ኢሳያስ ደንድርና ከድሬዳዋ ወዘሪት ራህማን ያካተተ ነው።

በዚህ የምርጫ ስነስርዓት ህግ መሠረት ይግባኝ ሰሚ ሆነው የተመረጡት በአዲስ አበባ ከተማ እግርኳስ ፌዴሬሽን የማይረሳ ስራ የሰሩትና በአቶ ሳህሉ ገ/ወልድ የአመራርነት ዘመን ፌዴሬሽኑን በምክትል ፕሬዝዳንትነት ያገለገሉት አቶ ብርሀኑ ከበደና በቅርብ አመታት ውስጥ የወጣቶችና ስፖርት ድኤታ ሆነው ያገለገሉትና በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚን በዳይሬክተርነት እየመሩ የሚገኙት አቶ አንበሳው እንየው መሆናቸው ታውቋል።

"ታሪካችንና ስማችንን ጠብቀን ምርጫው ሀቀኛ በሆነ መንገድ እንዲጠናቀቅ እንሰራለን" በማለት ባለፈው መግለጫ ላይ የተናገሩት የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ አቶ ሃይሉ ሞላ ናቸው። በኮሚቴው የስነምግባር መመሪያም መሰረት "እንቀድሞው ምርጫ ማንም እየተነሳ መግለጫ መስጠት አይችልም" ሲሉ አስረድተዋል።

ኮሚቴው የምርጫ ተወዳዳሪዎቹን ይፋ ካደረገ በኋላ ቅሬታ ያለው ወገን ከሐምሌ 26- ነሐሴ 2/2014 ድረስ ይግባኝ የመጠየቅ መብቱ እንደሚከበርም በመግለጫው ተጠቁሞ ነበር።

ኮሚቴው እንዳስረዳው፣ ለፕሬዝዳንትም ይሁን ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልነት የሚወዳደር አንድ ዕጩ የአንድ ክልል ፌዴሬሽንና የአምስት ክለቦችን ድጋፍ ማግኘት አለበት። የክለቦቹንና የክልል ፌዴሬሽን ማህተም የታተመባቸው ስድስት ደብዳቤዎችም ያስፈልጋል። አንድ ክልል ዕጩ ሲልክ ሁለት ወንድና አንድ ሴት የግድ መሆኑን ቁጥሩን መጨመር እንጂ መቀነስ አይቻልም። አለበለዚያ ግን የቀረበው እጩ ከውድድር ውጪ ይደረጋል።

በዚህም መሰረት አስመራጭ ኮሚቴው እጩዎችን ይፋ ሲያደርግ በአቶ ሳህሉ ገ/ወልድ፣ በአቶ ጁነዲን ባሻና በአቶ ኢሳያስ ጅራ የፕሬዝዳንትነት ዘመን ባለፉት 12 አመታት በስራ አስፈጻሚነት የሰሩት የአፋሩ ተወካይ አቶ አሊሚራህ መሀመድ ከምርጫ ውጪ ሆነዋል። ኮሚቴው በተከታታይ ሶስት አመት ይሁን በተለያየ ጊዜ ያገለገለ እጩ በዚህ ምርጫ አይካተትም በሚለው መመሪያ መሰረት አቶ አሊሚራህን ከውድድሩ ውጪ ማድረጉ ታውቋል።

በተጨማሪም ኮሚቴው በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ቡና ስራ አስኪያጅ ሆነው እየሰሩ የሚገኙት አቶ ገዛኸኝ ወልዴ የሀረሪ ክልል የሰጣቸውን ውክልና ማንሳቱን ተቀብሎ ከፕሬዝዳንታዊ ምርጫው ውጪ እንዳደረጋቸው ታውቋል። አቶ ገዛኸኝ "ክልሉ ውክልናዬን ማንሳት አይችልም" ቢሉም ኮሚቴው በተቀመጠው ህግ ክልሉ ውሳኔውን የመሻር መብት አለው ብሎ ውክልናውን ውድቅ አድርጎታል።

ሁለቱም ዕጩዎች ከትናንት ጀምሮ በአቶ አንበሳው እንየውና በአቶ ብርሀኑ ከበደ ለሚመራው ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ይግባኝ የመጠየቅ መብት እንዳላቸው ጠቁሟል።

አቶ ገዛኸኝ የሀረሪ ክልል የሰጣቸውን ውክልና ማንሳቱ ተቀባይነት የሌለውና ህጉን ያልተከተለ በመሆኑ በምርጫው ላይ እንደምሳተፍ ርግጠኛ ነኝ" ሲሉ ከቀናት በፊት ለመገናኛ ብዙሃን ተናግረዋል። እንደ አቶ ገዛኸኝ ገለጻ፣ የምርጫው ቀን የተጨመረው እጩዎችን መላክ ላልቻሉ ክልሎች ዕድል ለመስጠት እንጂ ለሌላ አይደለም፣ "ሐምሌ 7 ውክልና ሰጥተው አጥጋቢ ባልሆነ ምክንያት ሐምሌ 19 ውክልና አንስቻለሁ ማለት አይችሉም፣ ከምርጫ አስፈጻሚው ተገቢ የሆነ ምላሽን እፈልጋለሁ" ሲሉ ተናግረዋል።

አቶ ገዛኸኝ እንዳስረዱት "የዛሬ አራት አመት ትግራይ ክልል አቶ ተስፋዬ ካህሳይን ወክሎ ባለቀ ሰአት ውክልናዬን አንስቻለሁ ሲል በወቅቱ የነበረው አስመራጭ ኮሚቴ አልተቀበለውም አሁን ካለው የምርጫ አስፈጻሚም ተመሳሳይ ምላሽ እጠብቃለሁ" ሲሉም ገልጸዋል።

EFDA
የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን
ETHIOPIAN FOOD & DRUG AUTHORITY

ከኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

## ህገ ወጦች ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ሁሉም የበኩሉን ሊወጣ ይገባል

**ታምራት ተስፋዬ**

የኢትዮጵያ ምግብና መድህኒት ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 1112 /2011 አም በተሰጠው ስልጣን መሰረት አገር ውስጥ የሚመረቱና ከውጭ የሚገቡ ምግብ መድህኒትና የህክምና መሳሪያዎች ጥራት፣ ደህንነት፣ፈዋሽነት ይፈትሻል፣ያረጋግጣል። መስፈርቱን የሚያማሉት ወደ አገር እንዲገቡ ፈቃድ ይሠጣል። የማያማሉት ደግሞ እንዳይገቡ ክልከላ ያደርጋል። በዚህም ህብረተሰቡን ጥራት፣ደህንነትን ብቃቱ ካልተጠበቀ ምግብና መድሃኒት ይከላከላል።

በባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ ያልተመዘገቡና በድብቅና በህገወጥ መንገድ ገበያ ላይ የሚገኙ ምርቶችን ህብረተሰቡ እንዳይጠቀም ማሳወቅን ጨምሮ በህገ ወጥ ተግባሩ ላይ ተሳትፈው የተገኙት ተቋማት ብሎም ግለሰቦች ላይም በየደረጃው የተለያዩ እርምጃዎችን ይወስዳል።

ይሁንና በህገ ወጥ ተግባሩ ላይ ተሰማርተው የሚገኙትን ህግ ፊት ቀርበው ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ በማድረግ ረገድ ወስንነቶች እንደሚስተዋሉ በርካቶች ሲገልፁ ይሰማል። አንዳንዶች‹‹በወንጀለኞቹ ላይ የሚሰጡ የህግ ውሳኔዎች አስተማሪ ናቸው ለማለት አያስደፍርም››ይላሉ። ለዚህ ደግሞ የህግ ክፍተቶችን ምክንያት ያደርጋሉ።

‹‹ለመሆኑ ይህን ቅሬታና የህግ አፈፃፀም ድክመት ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ እንዴት ይመለከተዋል፣ ምንስ መደረግ አለበት››የሚል ጥያቄ በማንሳት ከባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይዘሪት ሄራን ገርባ እና ለማእከላዊ ኢትዮጵያ ቅርንጫፍ ፅህፈት ቤት ሃላፊ አያልሰው መለሰ ጋር ቆይታ አድርገናል።

ዋና ዳይሬክተራ እንደሚገልፁት፤ በተለይ ከጥራትና ደህንነት ጋር የተያያዙ ችግሮች በጤና ላይ ተወስነው የሚቀሩ ብቻ አይደሉም። በማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ ጭምር ጫና የሚፈጥሩ ናቸው። ይህ እንደመሆኑም ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ከምንጊዜውም በተሻለ ሁኔታ ችግሩን በመከላከልና ለመቀነስ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል።


ወይዘሪት ሄራን ገርባ

ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ስጋትን መሰረት ያደረገና ተጠቃሚ ዘንድ ሳይደርስ ማስቀረትን ቀዳሚ ያደረገ የቁጥጥር ስትራቴጂ አለው። በተለያዩ ክትትልና ፍተሻ ስራዎች ህገ ወጥ ተግባር ላይ የተሰማሩ ሲገኙም አስተዳደራዊ እርምጃ የመውሰድ ሃላፊነት የባለስልጣን መስሪያ ቤቱን እና የክልል ተቆጣጣሪ አካላት ነው።

ይሁንና በአሁን ወቅት አስተዳደራዊ እርምጃ ብቻ እያስተማረ አይደለም። በህገ ወጥ ተግባር ላይ የተሰማሩት ቤቶችን ማሸግ ወይም መዝጋት ብቻ እያስተማረ አይደለም። ከመዝጋት ባለፈ ወደ ወንጀል መቀየር ያስፈልጋል። በወንጀለኛ መቅጫ ህግ መቅጣት ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ ክፍተት አለ። ይበልጥ መስራት ይጠይቃል።

ክፍተቱ የህግ አለመኖር አይደለም። ህጎቹ ችግር የለባቸውም። ለአብነትም የምግብና መድህኒት አስተዳደር አዋጅ አለ። የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ አለ። የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አለ። መሰል በርካታ ህጎች አሉ። ችግሩ የህግ አለመኖር አይደለም። ማስረጃ የመሰብሰብና የማግኘት ፤ማስረጃውን በደንብና በአግባቡ አሰናድቶ እና ገምግሞ ወደ ፍርድ የማቅረብ ጉዳይ ነው። ህጎቹን አቀናጅተን በህገ ወጦቹ ላይ ተገቢን ፍርድ የማሰጠትና የማስቀጣት ጉዳይ ነው።

እንደ ዋና ዳይሬክተሯ ገለፃም፤ ጉዳዮች ወደ ህግ አካል በሚቀርቡበት በተለይ አንዳንዶቹ ጉዳዮች በሰው ልጅ ጤና ላይ ምን ጉዳት አስከትሏል የሚል ጥያቄ ይጠየቃል። ይሁንና የምግብ ጉዳይ ምናልባት በተዋሃሲያን የተበከሉና ወይንም ወዲያው ችግር የሚያስከትሉ ነገሮች ሊያጋጥሙ ይችላሉ።


አቶ አያልሰው መለሰ

በተለይም ምግብን ከባእድ ነገሮች ጋር የመቀላቀል ጋር ተያይዞ ለአብነት ቅቤ በሙዝ ሊቀላቀል፣በርበሬ ላይ ቀለም ሊጨመር ይችላል። ይሁንና የተቀላቀለው ባእድ ነገር በአንድ ጊዜ በሰው ልጅ ጤና ላይ ችግር ላያስከትል ይችላል። ሆኖም ግን እየቆየ በሄደ ቁጥር ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች ይዳርጋል። የፈንገስ ቅሪት ወይንም አፍላ ቶክሲንን ብንወስድ የጉበት ካንሰር ከሚያስከትሉት መካከል በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስ ነው።

መሰል ጉዳዮች በመያዝ ወደ ፍርድ ተቋማት በሚኬድበት ጊዜ የላብራቶሪ ውጤት እንደሚጠየቅ የሚጠቁሙት ዋና ዳይሬክተሯ፤ መረጃና ማስረጃ በአግባቡ በማቅረብ በህገ ወጥ ተግባሩ የተሳተፉትን ተጠያቂ ለማድረግ ረገድ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተለይም የላብራቶሪ ስርአቱን ይበልጥ በማደራጀት ላይ እንደሚገኝ ይጠቅሳሉ።

ህገ ወጦችን ህግ ፊት ቀርበው የሚሠጣቸው ፍርድ ቢሆን አስተማሪ ነው ብሎ አፍን ሞልቶ ለመናገር የማይቻል መሆኑን የሚስማሙበት ዋና ዳይሬክተሯ፤ በቀጣይም የፍርድ ውሳኔዎች አስተማሪ በሆነ መልኩ እንዲወሰኑ በተለይ በህገ ወጥ ተግባር ላይ የተሰማሩት ከተግባራቸው እንዲታቀቡ፣ለመሰማራት ፍላጎት ያላቸውም ሃሳባቸውን እንዲሰርዙ ለማድረግ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሰራም ነው አፅእኖት የሠጡት። ህገ ወጦች ተገቢው ቅጣት እንዲያገኙ ለማድረግ ሁሉም ከህብረተሰብ ተሳትፎ ጀምሮ ሁሉም የበኩሉን ሊወጣ እንደሚገባም ሳያስገነዝቡ አላለፉም።

በኢትዮጵያ ምግብና መድህኒት ባለስልጣን የማእከላዊ ኢትዮጵያ ቅርንጫፍ ፅህፈት ቤት ሃላፊ አቶ አያልሰው መለሰ፤ ‹‹በአብዛኛው ምርቶች አምልጠው ገበያ ላይ ሊገኙ የሚችሉት በህገወጥ መልኩ ወደ አገር የሚገቡና የሚመረቱ ሲሆን ነው። በህጋዊ መንገድ የሚገቡት የተመዘገቡና መረጃ ያላቸው ናቸው። ይህ እንደመሆኑም ለመቆጣጠርም ሆነ ችግሮች ሲገኙም ፈጥኖ ለማስተካከል አስቸጋሪ አይደሉም››ይላሉ።

ህገ ወጥን በመከላከል ሂደት በተለይ በቁጥጥር የተያዙና የተከማቹ ምርቶች ከመጋዘን ወጥተው ገበያ ላይ እንዳይገኙ በማድረግ ረገድም የፀጥታ አካላትን እና የአካባቢ የተለያዩ አመራሮችና ሃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት እንዳለባቸው የሚያስገነዝቡት አቶ አያልሰው፤ ወንጀለኞ በቁጥጥር ስር በሚውሉበት እና ለፍርድ በሚቀርቡበት ወቅትም ተገቢና ተመጣጣኝ ቅጣት እንዲያገኙ በማድረግ ረገድ ይበልጥ መስራት እንደሚያስፈልግ፣ለዚህም ህዝብ እና ባለድርሻ አካላት ተቀናጅተው መስራት እንዳለባቸው አጽንኦት ይሰጣሉ።

Tel : +251-11-552-41-22
+251-11-552-41-22
P.o.box. 5681
Free call. 8482
http://www.fmhaca.gov.et/contact/
E-mail contactefda@efda.gov.et
Telegram channel link
https://t.me/ethiopianfoodanddrugauthority/